# እንኳን ደና መጡ


PDF Compressor Free Version

## ማንበብ ለህይወት @worldbook0

pdf መፅሐፍትን በቀላሉ የሚያገኙበት የቴሌግራም ቻናል

እንዲሁም ምርጥ ምርጥ ትረካዎችን ያገኛሉ

ይቀላቀሉን ቤተሰብ እንሁን የሚፈልጉትን መፅሐፍ በቀላሉ ያግኙ



PDF Compressor Free Version



ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ገደማ የጥበቡን መጽሐፍ ጠቢቡ ሐረ በጀርባቸው አዝለው አረጋዊዉን ሊቅ ዐፅቁን በእጃቸው እየደገፉ ወደ ጎንደር ልደታ ማርያም ማዝገም ጀመሩ። በጎንደር ከተማ መብራት ከጠፋ ሦስተኛ ቀኑ ነው። ታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ ጽልመት ለብሳለች። ሁሉቱ ጠቢባን ከበአታ ማርያም ሰፊር ተነሥተው በአባ ጃሌ ተክለ ሃይማኖት በኩል በኩበሉ ውስጥ ለውስጥ ወደ ልደታ ማርያም ሲያልፉ በመንገዱ ጠርዝና ጠርዝ እናት አልባ ቡችሎች ያንኳርፋሉ። ከወደ ኋላ ቀን ጥቂት አርፈው ሌሊቱን አቋቋም በመቀጸል ወደር የለላቸው የደብረ-ጥበብ በአታ ማርያም ሊቃውንት የእጅ ጸናጽል እየጣሉ ወረብ ይወርባሉ። ድምፃቸው ሲስረቀረቅ የወረቡን ጣዕመ-ዜማ ሲሰሙ ሐረ ተመስጠ ውስጥ እልፍ አሉ። አእምሯቸው ሰባቱ ሰማያት ወጣ።

ጠቢቡ ሐረ በጀርባቸው ያዘሉት የጥበብ መጽሐፍ ቀይ ብርሃን የጎንደርን ከተማ ከሁለት ሰነጠቀው። ጎንደር በቀያይ የብርሃን ጨረር ተኳለች። አሮጌ ቤቶቿ የብርሃን መቀነት ታጠቁ። የብርሃን ጨረር ፈነጠቁ።

ጠቢቡ ሐረ ከተመስጠ ሲመለሱ የመጽሐፉ ምሥጢር እየዛ እየገረማቸው ሄደ። አንገረብ ላይ በከፊል ብልጭ ብሎ ድርግም ያለው ቀይ ብርሃን የብስ ላይ ሲታይ ይበልጥ ተጥበረበረ። ምነው አንዲህ ወንዝ እንዲህ ባለ ብርሃን እንደ ሰም ፈትል ተንደግድጎ ነድዶ የሕይወት

ውኃ በተገለጠችና የአበው ጥበብ ለዚህ ውትልፍ ትውልድ ሰትጽበት በተገለጠ ሲሉ ተመኙ።

PDF Compressor Free Version

ሊቅ ዕፅቁም በመጽሐፉ ወጋገን የደከመ ዐይናቸው እይታ የጨመረ መስላቸው።

ሐረም በደመና ከሚሄዱበት የተዋነይ ጥበብ ይልቅ ይኸው ጥበብ በልጦ ታያቸው። ደግነቱ ሁለቱም ጥበባት ከአስማትም ሆነ ከምትሐት ነፃ መሆናቸው ሌላ ፍሥሐ ፈጠረላቸው።

"ከዚያም ሕፃናት ሆነን ከቆሎ ተማሪ ቤት ሳለን ለመምህራችን በሳምንት አንድ ቀን ዐርብ ብቻ እንጨት እንለቅም ነበር። ያን ጊዜ ሌሊት ሌሊት የሚያበራ ግሩም ዕፅ ከዱር ለቅመን እናመጣለን። ቀን እንደማንኛውም ዕፅ ነው። ሌሊት ሌሊት ግን እንደዚህ መጽሐፍ የተለየ ቀይ ብርሃን ይፈነጥቃል። ከዓመታት በፊት ያንን ዕፅ ለምርምር ፈልገ አጣሁት። እንኳን ዕፁ ዱሩ ወድሟል። በዚህ ስቆረቆር እኖር ነበር። ዛሬ ግን ጸጸቴ ተመልሷል። ዓለም ቀይ ምንጣፍ ሠርታ ስትነግድ የእኛ አባቶች ቀይ ብርሃን የሚፈነጥቅ የጥበብ መጽሐፍ ጽፈው ስላወረሱን ጥያቄዬ ተመልሷል።" አሉ ጠቢቡ ሐረ ገርሟቸው።

"ይህ ቀይ ብርሃን ሊያስገርምህ አይገባም። ይህ መጽሐፍ ቀያይ ብርሃን መርጨቱ ብዙ የተለየ አንድምታ ሊሰጠው አይገባም። በትክክል ሊደነቅ የሚገባው ባሕሩን አንድዶ የሕይወትን ውኃ የገለጠልን ቀን ነው። ያን ጊዜ መጽሐፉ በትክክል የጥበብ መጽሐፍ እንደሆነ እናምናለን። በቀር የተለየ ዋጋ የለውም። ቀይ ብርሃን ያለው መጽሐፍ ቀርቶ ዓለም በባሕር ውስጥ የሚበራ ብርሃን ያለው ደልባ ሠርታለች።

PDF Compressor Free Version

ዐይናማ ሴቷውንት እንደሚተርኩት በድሮ ዘመን የባሕር ዘራፊዎች በባሕር ላይ እየሄዱ ውንብድና ይፈጽሙ ነበር። ምን መሰለህ? የባሕር ንጋዲዎች ባሕሩን አቋርጠው፣ የብሱን ረግጠው፣ ሲነግዱ የባሕር ዘራፊዎች ጥሪት ቀሪታቸውን እየነጠቁ አስቸገሯቸው። እንዳያገኟቸው በባሕሩ ውስጥ ውኃ ከሚከለክል፣ ብርሃን ከማይከለክል፣ ቀይ ብርሃን ያለው ጀልባ ሠሩ። ጥቂት ቆይቶ ዘራፊዎችም ተመሳሳይ ጀልባ ሠርተው በባሕሩ ውስጥ ለውስጥ እየተከተሉ ይዘርፏቸው ነበር። የጀልባዋ ስምም ሻምቡቅ ይባላል። እናም ውኃ የሚከለክል፣ ብርሃን የማይከለክል፣ መጽሐፍ መኖሩ ግርምት ሊፈጥርብን አይችልም። የአበውን ጥበብ ማድነቅ የምንጀምረው ባሕሩን እንደ ሰም አቅልጠ ያነደደው ጊዜ ነው! የሕይወት ውኃ ቡልቅ ቡልቅ ስትል ነው ተያይዘን የሕይወት መዝሙር የምንዘምረው። መጽሐፉን ከሌሎች ልዩ የሚደርገው ቀይ ብርሃን መፈንጠቁ ሳይሆን ባሕሩን ማንደዱ ነው። ከዚያም ማየ-ሕይወትን መክሰቱ። ሲቀጥል ሐሽማል ለመሆን ማስቻሉ ነው።" ብለው ጎንደር ቀስቀምን ወደ ቀኝ ትተው ወደ ልደታ ማርያም አለፉ።

ከልደታ ማርያም ጸበል ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው በተለምዶ ፈጨፈጭ የምትባለዋን ወንዝ አገኙ። ሊቅ ዐፅቁ ፈጨፈጭ ላይ ዐይናቸውን ጥለው ጥቂት ተመለከቱና "ፈጨፈጭ ድሮ አንጾኪያ ወንዝ ነበር ስሟ። ፈጨፈጭ በቅርብ ጊዜ የወጣ ስም ነው። አንጾኪያ በጎንደር ወደ ውስጥ ከተቀበሩ አፍላጋት አንዱ ነው። ከዚህ ከፈጨፈጭ ጎን

ፈልቶ ጎንደርን እያረሰረሰ ቀሃ ይገባ ነበር። በጣሊያን ወረራ ጊዜ ወደ
ውስጥ ጥቅም ሳይሰጥ እንኳን የሚያውቀው ጎንደሬ የለም።
PDF Compressor Free Version

ሁለተኛው ደግሞ ሾላጌ ውኃ ይባል ነበር። ሲጠጡት ጣዕሙ ወተት ወተት ይል ነበር። በዚህ የተነሣ ረቡዕና ዐርብን ጨምሮ በጾም ወቀት እንዲይጠጣ የጎንደር ሊቃውንት ከልክለው ነበር። መከልከላቸውም ውኃው ምን አልባት ጾም ሳያስገድፍ አይቀርም ከማለት አሳቤ ነው። ከሾላጌ ቀጥላ ምሥጢራዊ ታሪክ ያላት ይች የልደታ ማርያም ውኃ ናት። በዚች በልደታ ውኃ መሉ ተስፋ አለኝ።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ።

"ከቀሃ፣ ከአንገረብ፣ ከማንኪትና ከሌሎችም የጎንደር አንቅዕት ለይተው በዚች ውኃ ላይ ለምን ተስፋ ሰነቁ?" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"የልደታ ውኃ በአበው አብነት ትርጓሜ ውስጥ ከማየ-ሕይወት ጋር በንጽጽር ተጠቅሳለች።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ።

"እንዴት?" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"በአንድ አብነት ውስጥይህ ተጽፏል፡-

'ዳዊት በታመመ ጊዜ ከቤተ ልሔም ውኃ ሊጠጣ ወደደ። ስለምን ቢሉ? ፈውስ ፈልጎ ነው። ይች የቤተ ልሔም ውኃ እንደ ልደታ ውኃ ሕይወትነት ያላት ውኃ ናት። ፈውስ ትሰጣለች" ሲል የልደታን ውኃ የሕይወት ውኃ ሲል አብነቱ ይገልጣታል። ይህ ትርጓሜ ዝም ብሎ በዘፈቀደ የተቀመጠ አይደለም። የልደታ ውኃ በትክክል ገነት ውስጥ የምትፈልቀዋ የሕይወት ውኃ እንኳ ባትሆን ማየ ሕይወትነት ግን እንዳላት ጥርጥር የለውም። ተዋነይ በጥበቡ እንደ ሰወራት ውኃ ተሰውራን እንጂ ካገኘናት የሕይወት ውኃ መሆኗ አያጠራጥርም።

ይችንን ውኃ የጠሙ ሊቃውንት ዛሬ ድረስ በሰዋሬ እንደሚኖሩ ያምን የግእዝ ሥርዓተ ትምህርት ይጠቅሳሉ። የቅጽል ስማቸው ደግሞ ሐሸማል ይባላል። የሐሸማል ትርጉም ደግሞ ያው የምታውቀው።" አሉ ሊቅ ዐፅቱ ወደ ልደታ ማርያም ውኃ ሊደርሱ።

PDF Compressor Free Version

ከዚያም "በል! መጽሐፉን በደንብ አስተካክለው። ቀለማቱ በቅርጽ በቅርጽ መጠን ከውኃ ላይ ማረፍ አለባቸው!።" ሊቅ ዐፅቁ በፍሥሓ ተበሰከሰኩ።

ጠቢቡ ሐረ ግዙፉን መጽሐፍ በልደታ ማርያም ውኃ ላይ በጣመ ሊደፉት ውኃዋ እንደ ቤንዚን ተንደገደገች። ብርሃኑ እንደ ደመራ አልፎ አልፎ ቦግ ቦግ አለ። ሊቅ ዐፅቁ በደስታ ድንጋጤ ተዝለፍልፈው ወደቁ። ጠቢቡ ሐረ በመዳፋቸው ጨልፈው ከሕይወት ውኃ ፉት ብለው በኮዳቸው ቀድተው መጽሐፉን ከውኃ ላይ ሲያነሡት ተመልሳ ተሰወረች። መጽሐፉን መልሰው ጣሉት። ውኃው ሁለተኛ ተንደገደገ። ሊቅ ዐፅቁ በፈንታቸው ዝቅ ብለው የቻሉትን ያኽል ተንሳፈፉ። ከዚህም "ሐር ወንበር ቤተ አበ'ክ" አሉ ሊቅ ዐፅቁ። ሐሸማል ሁን። እስከ ፈለግህ ዓመት ድረስ በሕይወት ኑር ማለታቸው ነበር። ውኃዋን በድጋሚ ከሰወሩ በኋላ ሊሰያዩ ጥቂት ሲቀራቸው ጠቢቡ ሐረ ለሊቅ ዐፅቁ በደመና የመሄድን ጥበብ ያብራሩ ጀመር።

"በደመና የመሄድ ጥበብ ዛሬም ሆነ ነገ ለማመን የሚከብድ ጥበብ ነው። ሥራውም የሰይጣን ሥራ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን አይደለም። ከመስዕ በኩል የሚመጡ ሦስት ነፋሳት አሉ። ከሰሜን በኩል የሚመጡ

PDF Compressor Free Version

ነፋሳት ናቸው። የአቡሻክሩ ከመታእምር ቀመር እንደሚገልጸው ለንደኛው ክፍል ከመስዕ ተነሥቶ ወደ ንነት ይነፍሳል። ንነትን የረስርሳል። ሁለተኛው ክፍል ከመስዕ ወደዚህ ዓለም ነፍሶ ውኃሥትን ይቀድሳል። ሦስተኛው ክፍል ከመስዕ ወደ የብስ ይነፍሳል። እኒህን ከምስት መዓዝን የመጡ ነፋሳትን ወደ አንድ መስኩት ለማምጣት ይህን ቀመር ይመልከቱ።" ብለው ሦስት ቃል አከታትለው ከአቡሻክሩ ውስጥ የ ከመታእምርን ቀመር በጥንቃቄ ቀመሩት። ከመስዕ አቅጣጫ የመጡ ነፋሳት ክብ ሠሩ። በዚህ ቅጽበት ዐውሎ ነፋስ መጥቶ በመካከላቸው ገባ። ሊቅ ዐፅቂ መጽሐፋቸውን በጀርባቸው አዝለው እንደ ክፍለ ዮሐንስ፦

"እሕኒ በግብረ ቅኔ ዘበሆሣዕና፤

እምእደ ገፋኢ ወተገፋኢ ንትመሠጥ በደመና" እያሉ ወደላይ ተነጠቁ።

"በቅኔያችን ጥበብ በያዝነው ሆሣዕና፤

እንነጠቃለን በግዙፍ ደመና" ማለት ነበር።

ጠቢቡ ሐረም በጎናቸው ከሕይወት ውኃ በጎዳ ሻጥ አድረገው

"ተዋነይ በጣና፤

ይመስላል ደመና"

ተብሎ ተዋነይ በደመና ሲሄድ የተዘመለትን እየዘመሩ ወደ ጎጃም አቀኑ።

PDF Compressor Free Version



ሎረ በደመና ተጭነው ዓለምን ሲዞሩ በፋራስ ቅኔ ቤት ግን መወድስ መዘራረፉ እና ስለ ጥበብ መፈላሰፉ ቀጥሏል። በዚህ ዓመት ደግሞ ጌርማ የሚባል ተማሪ ቅኔ ቤቱን ተቀላቅሏል። ገሞራው ስለ ዲማ ውኃ ቅኔውን ዘርፎ ነግሮ ስለተቱን አሣርሞ ወደ ቅኔ ቤቱ ሲደርስ ከቅኔ ቤቱ መካከል ቁጭ ብለው ግስ የሚያጠኑ ጀማሪ ተማሪዎች ከመቀመጫቸው ተነሥተው በአክብሮት ተቀበሉት። ከመካከላቸው ጌርማ የሚባል እውቅ ደክተር ነበር። ደክተሩ ወደ ቤቱ ገብቶ ኮቸሮ እንዲበላ ጋበዘው። ገሞራው ትንሽ ተግደርድሮ ወደ ጎጆው ገባ። ጌርማ በዘመናዊ ትምህርት ሊተ-ሊቃውንት ነው። ወደ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ የሄደውም በጎንጅ የቅኔ መንገድ ላይ ጥናት ለመሥራት ነበር። ቅኔ ቤት ገብቶ የሊቁ መወድስ፣ የተማሪዎች መንፈሳዊ ሕይወት፣ የቦታው ጸጥታ የቅኔ ዘራፊዎች ፍልስፍና ማረክውና እንደ ወጣ ቀረ። ከኢትዮጵያ እስከ-ደቡብ አፍሪካ አልፎም አሜሪካ ድረስ ዘልቆ ያጠናቸው ምርምሮች የገበሰ ገለባ ሆኑበት። የሀገሩን ቅኔ ተምሮ በዚያ እየተፈላሰፈ ለመኖር ወሰነ። ስልኩን ዘግቶ ዓለምን ለመርሳት ዳገት ሆኖበት ነበር። እያነከሰም ቢሆን የተማሪዎችን ህላዌ ቀስ በቀስ እየተለማመደው መጣ። ሊቁ ፋራስ ቅኔ ሲዘርፉ ለውነቱ ይንቀጠቀጣል። የቅኔ ዘራፊዎች እንደ አውራ በሬ እንቧ እያሉ በመወድስ ቅኔ ሲደነፉ ሰማይ የተቀደደ ቢመስለውም ከሊቁ ወንበር ሥር ቁጭ ብሎ አፉን ከፍቶ ማዳመጥ ያዘ። በአብዛኛው ጊዜ ቅኔ ዘራፊዎች መወድስ ሲዘርፉ ልብ ምቱ ይጨምራል። ዐይኖቹን ያለመልማል። ጩኸ ጩኸ የሚል ስሜት ያድርበታል። እየዋለ እያደረ

PDF Compressor Free Version

ሊሄድ ግን በፈንታው አለሙን የመሆን ሕልም ተጠናወተው። ሊቃውንቱን መስሎ፣ ኮቸሮ ሸምቶ፣ ግስ ገዝቶ "ሐተተ መረመረ፣ ፈለሰፈ ተራቀቀ" እያለ ግስ ማጥናት ቅኔ መቁጠር ጀመረ። ዓመታት ነጎዱ። እንደ ቀዛፅመት ከመንፈቅ አስቆጠረ። ሰጊዜው አልለመደው ብሎ ያስቸገረው በመንፈቀ-ሌሊት በግድ እየተነሣ ቅኔ መተጸል ነበር። ጓደኞቹም በሥነ ሥርዐት በመቀስቀስ ፈንታ ከላዩ ላይ ውኃ እያፈሰሱ ከአንቅልፍ ዓለም ያነቁታል። እንደ ውሻ ቡችላ ዐይኖቹን ሳይከፍት ብድግ ይልና ይነጫነጫል። ቢነጫነጭም ቅሉ የሚያከብረው ግን አላገኘም።

እየቆየ ሲመጣ የቅኔ ዘራፊዎች ሕላዌ ገረመው። ቅኔ ሲቀጽሉ አድረው ሌሊት በስምንት ሰዓት ያንን ሁሉ ውሪ ጎጆ እየዞሩ ጀማሪ ተማሪዎቹን አንድ ጊዜ መደዳ ይቀሰቅሳሉ። ከአንቅልፍ ያነቃሉ። ለቅጸላ ያተጋሉ። ከተቀሰቀሰ በኋላ ሰንፎ ከቅኔ ቅጸላም ሆነ ከቅኔ ዘረፋ የቀረውን ሰነፍ ተማሪ በላዩ ላይ ቀዝቃዛ ውኃ ይቸልሱበታል።

ዶ/ር ኄርማ ከተማሪዎች ጋር በሕገ-ተማሪ ከተቆጠረ በኋላ በቅጸላ ጊዜ የሚያከብረው አጣ። በትርፍ ጊዜ የሚቀልዱት ተማሪዎች ሳይቀር ከቅጸላ ሲቀር ውኃ ይቸልሱበታል። በዚህ ያማርራል። ለቅኔ ተማሪዎች ትርፍ ጊዜ ሲኖራቸው ሒሣብ ያስቆጥራቸዋል። እንግሊዘኛ ቋንቋ ያለማምዳቸዋል። እሱ ቅኔ፣ እነሱ ሒሳብ፣ ሲማሩ ይውላሉ። ተማሪዎች በቃላቸው የሚያውቁት ሒሳብ ወረቀት ላይ ግር ሲላቸው ኄርማ ግርምት ይፈጥርበታል። የሊቁ ተማሪዎች ሒሳብን በቃል እንጂ በወረቀት ተምረውት አያውቁም። በቃል አቡሻክር ድረስ ያሰላሉ። ቀመረ-

PDF Compressor Free Version

ድሜጥሮስን ሐሳበ-ንጉጻንጉዲን ሐሳበ-ቢዘንን ይሸመድዳሉ። ቀመር ይቀምራሉ። ያን ወደ መፅሐፍ ሲያመጡት ይደናገራሉ። ጌርማ ደስ እያለው ከጊዜ ቤት ጀምሮ በልሙጥ ወረቀት እየጻፈ ያሳያቸዋል። ወዲህም ልሣነ-ክልኤ ለመሆን ከዘመናዊ ትምህርት ላይም ትኩረት እንዲሰጡ ቀስ እያለ ይመክራቸዋል። እነሱ ሲማሩ እንደ መምህርነቱ ያክብሩታል። እሱም እንደ መምህርነቱ ተግሣጽ ጣል ያደርጋል። ወደ ማታ በፊንታው ተማሪ ይሆናል። እንቅልፍ ሲይዘው ቀዝቃዛ ውኃ ይቸልሱበታል። በዘመናዊ ትምህርት መምሕራቸው መሆኑን ይረሱታል። በቅኔ ቤት ሕግ በትምህርት ወቅት መከባበር ብሎ ነገር የለም። እድሜውን ዐይተው መቀመጫ ይለቁለት በቀር እንጂ ካልታመመ በቀር ተኝቶ እንዲያረፍድ የቅኔ ቤት ሕግ አይፈቅድም። ሁሉም ተነሥቶ ቅኔ ሲያጠና ያድራል። ቅኔ ዘረፋ ባለቀን ደግሞ ቅኔ ሲዘረፍ ያ ሁሉ ወፈ-ሰማይ ተማሪ ቅኔውን እየሸመደደ ያረፍዳል። በደንብ ሲነጋ የዕለቱን የቅዱሳንም ሆነ የጌታን ታሪክ ከመምህሩ ሰምቶ ወደ ቅኔ ቆጠራ ይበተናል። ከማለዳው እስከ ሦስት ሰዓት መወድሱን ቆጥሮ ያ ሁሉ ወፈ-ሰማያት ወደ መምህሩ ይሰበሰባል። መምህሩ ከተዋነይ ዋርካ ሥር ካለው ታላቅ ጥፍጥፍ ድንጋይ ላይ ተገሥጠው ቅኔ ማዳመጥ ይጀምራሉ። ቅኔ ነገራ ሲጀመር የቅኔ-ዘራፊዎች እየዘረፉ ጀማሪዎች ደግሞ የቆጠሩትን ቅኔ መንገር ይጀምራሉ። የመማር ማስተማሩ ሥነ ሥርዐት ዘወትር እንዲህ ይቀጥላል። ዐራት ማእዘን ሰሌዳ ላይ የተጻፈ ቀለም ሳይሆን ከሊቁ ልብ የሚፈልቀውን ምሥጢር ያ ሁሉ ስፍር ቁጥር የሌለው ተማሪ ተካፍሎት ወደቤቱ ይገባል። የምሥጢሩ ምንጭ

አንድ ቢሆንም ምሥጢሩ ግን በየዐይነቱ ነው። ለአንዱ የደረሰው ለሌላው አይደርሰውም። ይሄ ፈጣሪ ለቅኔ መምህራን የገባው ቃል ኪዳን ስለሆነ እንደ አቡነ ሐራ የመቃብር አፈር ሁልጊዜ ቢያፍሱት ቢያፍሱት አይጎድልም።

PDF Compressor Free Version

ገሞራው ወደ ጌርማ ጎጆ ሲገባ ጌርማ ገሞራውን ሊጋበዝ ኮቸሮ ማኪቸር ጀመረ።

ጌርማ በዚህ ሳምንት ከቅኔ ጋር ተጣልቶ ነበር የሰነበተው። ባለፈው ሳምንት አንዲት ቅኔ ነግሮ ሳያሳርም ቀረ። ሊቱም ለማበረታታት ያኸል ቅኔ እየገባው እንደሆነ ሲነግሩት በደስታ ፈነጠዘ። በዚህ ሳምንት ግን ቅኔ እንደ በጋ ዝናም ሆነበት። ጠዋት ተነሥቶ ወደ ዱር ገብቶ ቅኔ ለመቁጠር ሲዘጋጅ እንቅልፍ እልም አርጎ ይወስደዋል። ሲነቃ ሊቁ የቅኔ ተማሪዎችን አስተምረው ጨርሰው ገባኤው ታጥፎ ይደርሳል።

ገሞራው ወደ ጎጆው ሲገባ ግን ቅኔ አብሮ የገባው መሰለው ዶ/ር ጌርማ።

ገሞራው ገብቶ ከመደቡ እንደ ተቀመጠ።

"ገሞራው እቀናብሃለሁ?" አለ ጌርማ።

"እንዴት?" አለ ገሞራው ዐይኑን ከጠባቧ ጎጆ ጣራ ላይ እያንከራተተ።

"ከብዙ ሊቃውንት እግር ሥር ቁጭ ብዬ የዓለምን ዝባዝንኬ ተምሬአለሁ። የነጮችን ፍልስፍና እስከ ጫፉ ባይሆንም ግንዱ ድረስ ወጥቻለሁ። በዓለም ውስጥ ያሉ የቅኔ መጻሕፍትን አንብቤአለሁ። ያገሬን ቅኔ ያኸል ይቅርና የሀገሬ ገበሬ በቀልድ በቀልድ የሚጥላቸውን ቅኔዎች ያኸል ያረካኝ ባለቅኔ በሌላው ዓለም አላየሁም። እንዳንተ ቀደም

PDF Compressor Free Version

ብዙ ነገር ይከሰታል የሚለኝ ትምርት ከዓለማዊው ትምህርት ጋር ተምሬ ቢሆን ኑሮ የምድር መልአክ ነበርሁ።" አለ ጌርማ ከማለዳው አንስቶ ሰዓት እስከ ዐራት ሰዓት ቅኔ በፈልግ ጠብ የሚል ነገር በማጣቱ ቀቢፀ ተስፋ አናውዞት።

"እንዴ! ገና ለገና በዚህ ሳምንት ቅኔ እምቢ አለኝ ብለህ ይህንን ያክል ማማረር ጀመርህ? ተው እንጂ ቅኔኮ ጥበብ ነው! ቆፍረህ የምታወጣው ወርቅ ማለት ነው። በሕርሠ ምድር ያለ የነዳጅ ድፍድፍ ማለት ነው። መኖሩ እየታወቀ ከድፍድፉ ለመድረስ አጥልቶ መቆፈር ይጠይቃል። በዚያውም ላይ የአንተ ቀቢፀ ተስፋ የጉድ ነው! ቅኔ ከጀመርህ ዓመት ከመንፈቅ እንደሆነህ አውቃለሁ። ነገር ግን ከቅኔው ይልቅ ጊዜህን ለምርምር ነው የሰጠኸው። ይህን ያክል የተማረርክለው በፈጣሪ ፊት ተቀባይነት የለውም። የግፍ ምሬት ነው።" አለ ገሞራው።

"ለማማረር ፈልጌ አይደለም። ቅኔው እየነፈሰብኝ እንደሆነ እየተጠራጠርሁ ነው። በዚህ ሳምንት ምንም ሊቆጠረኝ አልቻለም። ያለ ተሰጥዎዬ የገባሁ መሰለኝ?" አለ ጌርማ ቅኔ ቆጥሮ ለመንገር ያደረገው ሙከራ አስቸግሮት።

ጌርማ ቅኔ ወዲያው እንደ ጀመረ የመነቃቃት ስሜት ነበረው። ለሳምንት ያክል ጉባኤ ቃና የምትባለዋን ባለ ሁለት ቤት ቅኔ በፍጥነት እያሰበ ያችን እያሳመረ ሰምና ወርቅ ለመትከል እየተቃረበ ነበር። ከሳምንት በኋላ እንደገና እየደነዘዘ መጣ።

ገሞራው እንደሚገልጠው ከሆነ ቅኔ በጠባዩ እንዲህ ዐይነት አጉል ዐመል አለው። አንድ ሳምንት ብልጭ ብሎ በሁለተኛው ሳምንት

PDF Compressor Free Version

ድርግም ይላል። በውስጣቸው ሳምንት ደግሞ ቦግ ይልና ደመና እንደ ጋረዳት ጨረቃ ተመልሶ ይጠፋል። በዚህ ጊዜ ወጣቷ ተማሪ ጭንቀት ውስጥ ይወድቃል። መማር ፈጽሞ ያስጠላዋል።

በኔርማ ውስጥም ይህ ስሜት መምጣት መሄድ ጀምሯል። ዛሬ ያገኘውን በነጋው ያጣዋል። ሲገለጥለት "የቅኔ ትምህርት ጭላንጭሉ ከተገኘ ብርሃን ነው ይላል። እንበ. ሲለው ደግሞ ቅኔ ጨለማ ነው። ነፋስ ነው። ድምፁን ትሰማዋለኽ እንጂ አትጨብጠውም።" እያለ ያማርራል።

ገሞራው በዚህ መንገድ ስላለፈበት የኔርማን ስሜት በሚገባ ተረድቶታል።

"በአንድ ጀምበር ቅኔ መዝረፍ አይቻልም። የቻልኸውን ያኽል መድከም አለብህ።" አለ ገሞራው ::

"መድከምማ እየደከምሁ ነበር። እንዲያው ዛሬ ያገኘሁትን ነገ አጣዋለሁ እንጂ።" አለ ኔርማ። ዛሬ ያጣኸውን ደግሞ ነገ ታገኘዋለህ። ዋናው ወደ ፊት መቀጠል ነው።" አለ ገሞራው

"ደረቁ ስለሆነ መሰለኝ?" አለ ኔርማ እንደመለሳቸት ብሎ።

"እረ በርጥቡም ቢሆን ያንቃል።"

ከዚያም የኔርማን ተስፋ መቁረጥ ተመልክቶ ሊያጽናናው ወደደና እንዲህ ቀጠለ።

"አውቃለሁ የሚል ምሉዕ ተስፋ እንዲኖርህ አንድ ታሪክ ልነግርህ አፈልጋለሁ። ታሪኩን የምነግርህ ወደ ፊት ቅኔ የመማር ተስፋህ

PDF Compressor Free Version

አንዳይመጣ ሲል ሳሎሜ ከሚሞራው ደሞሽ ዐይኖቹን ከጣራው ወደ
ወለሉ እየወረወረ።
"እሺ ደስ ይለኛል" አለ ጌርማ።
ገሞራው እንደ ተለመደው ዐይኖቹን ገርበብ አርጎ ቀጠለ።
"ዲማ ጊዮርጊስን በታሪክ ታውቀው ይሆናል?" አለ።
"ብደንብ አውቀዋለሁ። ስለ ዲማም ከፍቅር እስከ መቃብር ይሞሮ
ተመሳሳይ ጥናቶችን አንብቤ አውቃለሁ።"
"እኔም የምንግርህ ዲማ ቅኔ ሲማሩ ስለመጡ ሦስት ሲቃውንት ግለ
ታሪክ ነው።" አለ ዐይኖቹን እንደጨፈነ።
ዐይኖቹን ሲጨፍን ሦስቱም ሲቃውንት በሐሳቡ መጡለት።
እናም ቀጠለ። "ጊዜው ረዘም ይላል። ዲማ ጊዮርጊስ በነጉዱ ካሣ
መወድስ እንደ አጓት በምትገፋበት ዘመን ነው።
"ሦስት ወንድማማቾች ወደ ዲማ መጡ። ከሦስቱ ወንድማማቾች አንዱ
እንደ ማይም ያሉ ናቸው ይሏል። ሰፌት ይሰፋሉ። የበቅሎ ዕቃ
ይሸልማሉ። የፈረስ ኮርቻ ያሳካሉ።ይህንን ሙያ ይዘው ማይሙ
ወንድሞቻቸውን ለማስተማር ወደ ጎጃም መጡ። መምህሩ አለቃ
ተጠምቆ ሦስቱን ሁሉ ቅኔ መምህር አድርገው ሰደዷቸው። እኒያ
ማይሙ ሰውም ሳያስቡት የቅኔ መምህር ሆኑ። ማን? ሦስተኛው
ማይም ልብስ ሰፊ አገራቸው ሕደው ሦስቱ ሁሉ ቅኔ መምህራን ሆኑ።
ይህ በታሪክ ተጽፏል። ማንም ያውቀዋል። አንተም እንደ ጉንዳን
ተግተህ ከተማርህ ለምርምር መጥተህ የቅኔ ሊቅ ሆነህ ትመለሳለህ።

ለጀ ገብ ትጋት ይጎርሀ። ሦስተኛውን ልብስ ሰፌ አርዐያ አርገህ መስፋቸው። ለምን ተናደድክ?
PDF Compressor Free Version
እንዴት ማይሙ ባለቅኔ ሊሆኑ ቻሉ? ተምረው? ወይስ ሌላ ነገር አግኝተው?" አለ ጎርማ።

"ለእኔም ትንሽ ግራ የሆነብኝ ማይሙ ሰውዬ የቅኔ መምር የሆኑበት መንገድ ነበር። የሁለቱ መምህር መሆን ድርም የታወቀ ጉዳይ ነው። ፊትም ቢሆን በተወሰነ መልክ ተምረዋል። ሦስተኛው ግን ፊደል ያልቆጠሩ ማይም ነበሩ። ሲጀመር አመጣጣቸው የፊረስ ዕቃ እየሰፉ ነገን እየሸጡ ወንድማማቾችን እየረዱ ሊያስተምሩ ነው። የፊረስ ኮርቻ ልጓም ዛብ ርካብ እየሰፉ እየነገዱ እያተረፉ ወንድማማቾችን በማስተማር ሥራ ቀጠሉ። ሁለቱ ሲማሩ ማይም ቢጤው ሥራቸው ተማባረ እደ ሆኑ። ቆይቶ ያላሰበት ሲሳይ ወረደላቸው። ቅኔ መምህር ሆኑ። የቅኔ መምህር የሆኑበት መንገድ ደግሞ ረቂቅ ምሥጢር ነበር።" አለ ገሞራው ትርኩቱን መልሶ እየደገመ። ከዚያም በተመስጦ ሸው እልም አለ።

ጎርማ ኮቸሮ ለመሥራት የለኩሳት እሳት ብልጭ ድርግም ትላለች። እሳቷን ቡፍ እያለ ብረት ድስቷን ማመሳሰል ጀመረ። እንደነገሩ የጣዳት ብረት ድስት እየጋመች ስትመጣ ውኃው እየፈላ ተትከነከነ። ጎርማ መልካም ሴት ይመስል የሠራው ሁሉ ይጣፍጥለታል። ያለ በርበሬ ኮቸሮ ሠርቶ ሲያቀርብ እንደ ቃና ዘገሊላ ወይን የተለወጠ ይመስል ውብ ጥፍጥና ያመጣል።

ጎርማ ቀይ ቀጫጫ ፈጣሪ ውበቱን የደፋበት ለጋ ወጣት ነው። ግብሩም መነኩሴ ቢጤ ነው። የቀረው አስኬማ ብቻ ነው። ውስጡ ከመነነ

PDF Compressor Free Version

ሰንባብታል። ጎጃም ሳይሄዱ ደግሞ አስኪማ ማጥለቱ የማይቀር ጉዳይ ነው። በፊት በዘመናዊ ትምህርት ዓለም ላለ ሰተዳር ያሰኳት ቁጠማ የመሰለች ቀንደ ነበረች። ለምርምር ሲወጣ እንደዋዛ ተለያዩ። ምርምሩን እርግፍ አድርጎ ትቶ ቅኔ ቢጀምርም አሷን ግን በቀላሉ መርሳት አልቻለም። ፊቱን ወደ ቅኔ እንዳዞረ በሕልሙ ስሟን እየጠራ ተቸገር ነበር። ዛሬ ግን እንደ እጉቱ እየቆጠራት ነው። ሳበላለም መርሳት ፈልጎ ግን አልተሳካለትም። ቀን ሲረሳት ሌሊት ትመጣበለች። ሲርቃት ትቀርባለች። በቅኔ መማረኩ ለእሱ እንጂ ለእሷ አይታያትም። ትዝ ስትሰው እንባ በእንባ ይሆናል። ወዲያው ደግሞ ለመርሳት ጥረት ያደርጋል። አትረሳውም። ልቡ ላይ በፍቅር ቀለም ተጽፋለች። ከሚያጠናው ግስ ዳር በፍቅር ብዕር የተጻፈው ስሟ ይታየዋል። ለቅኔ ተማሪዎች ምሥጢሩን ሲያካፍላቸው በማጽናናት ፈንታ "በሕልም የምትመጣ የሴት ዛር ናት። መንፈስ ናት። አትመናት።" ብሰው ያጣጥሉበታል።

ገሞራው ከኔርማ ጋር ከተገናኘ ጊዜ ጀምሮ ተርቦ አያውቅም። ኔርማ በሰዓቱ ክቾርም ሆነ ቆሎ ቆልቶ የተማሪ ጎጆ ያፈራውን ያቀርባል። ገሞራው የሚያነበውን መጽሐፍ አጥፎ እየሣቀ ይቀርብና አብሮ ይበላል። ገሞራው አንዳንድ ጊዜ በፈንታው ባለመሥራቱ ውስጡ በይሉኝታ ይታሠራል። ኔርማ ደክመኝ ባይልም ዘውትር በሰው እጅ እየተሠራ መብላቱ ነውር እንደሆነ ይረዳል። ችግሩ ሲሠራ ሲነሣ ልቡናው ተመስጦ፣ ሕሊናው ከቀለም ጋር ጦርነት ገጥመው ሲዋጉ የጣደው ብረት ድስት ውኃ ይጨርስና ባዶ ሆኖ ያገኘዋል። ጥሬ ቆልቶም

ሆነ ኮቸሮ ሠርቶ በመብላት በኩል ልፍስፍስ ነው ገሞራው። ሠርቶ
ከሚበላ ሴትን ማርያም ብሎ ቢያመጣ ይቀለዋል።
PDF Compressor Free Version
"እሺ! ጌርማ። ልቤን ምን ወሰደው? የሆነ የተደገመብኝ ነገር ሳይኖር
የሚቀር አይመስለኝም። ታሪኩን ሳልፈጽም ወደ ሰመመን ገባሁ።" አለ
ገሞራው ከተመስጦው ሲመለስ።
"ታሪኩን ጎላ ትጨርስልኛለህ። አሁን ክትፏችን ደርሷል።" ጌርማ
እንደ ነገሩ የሠራትን ኮቸሮ እስክ ብረት ድስቲ እያቀረበ።
"ይች ኮቸሮ በክተማ ቂንቂ ፍርፍር ትባላለች። ሴቶች ሲሠሯት የበለጠ
ትጣፍጣለች። ዛሬ ረሳኋት እንጂ ለትዳር ያጨዋኋት ቆንጆ ፍርፍር
ሠርታ አብልታኛለች። "ለምን እንዳበላችኝ ታውቃለህ?" አለ ጌርማ
ገሞራው ያውቅለት ይመስል።
"አሯ! አላውቅም" አለ ገሞራው።
"አባቷ ፍርፍር በጣም ይወዳሉ። እሷም የአባቷን ፍቅር ለመግለጥ
ስትፈልግ ፍርፍር ሠርታ ትሰጣቸዋለች። አባቷ በዚህ ደስ ይላቸዋል።
ታዲያልህ አንድ ቀን ወደቤቷ ወሰደችኝ። ወዲያው ፍርፍር ሠርታ
አቀረበች። አብረን በላን። ማዕዱ እንደተነሣ "ለምን ፍርፍር
እንደጋበዝኩህ ታውቃለህ? አለችኝ። እንደማላውቅ ነገርኋት። አባቴ
ፍርፍር እጅግ በጣም ይወዳል። እኔም አባቱን በጣም እወደዋለሁ።
ስለምወደው ፍርፍር ሠርቼ አሰጠዋለሁ። በጣም ይወደኛል። ለአንተም
ፍርፍር ያበላሁህ እንደ አባቱ አድርገህ እንድትወደኝ ነው አለችኝ።" አለ
ጌርማ። ገሞራው ብዙ አልደነቀውም። ስለፍቅር የት ያውቅና? አልፎ
አልፎ ተፈጥሮ ሲያቸግረውም አጥብቆ ውዳሴ ማርያም ይደግማል እንጂ

PDF Compressor Free Version

ወደ ዙሪያ ገባቸው አያውቅም። ወዲህም 'ፍትወት የሚጸናው ሠርቶ መርጎ እያየ ነው። ሲጋ ጨረቃ ብቅ ስትል ደም ይመላል። ዝሙት ይጸናል። በዚህ ሰሞን አዳሜ መፍቀሬ-እንስት ይሆናል። ጠቢብ ግን በዚህ ሰሞን ራሱን ከፍትር መሰል ዝሙት ይጠብቃል። ሰነፍ ይወድቃል' ሲል በአቡሻክር ቀመር መነሻነት ይፈላሰፋል። ከአቡሻክር ቀመር ጋር ያዛምደዋል።"

ኮቸሮው ቀረበ። ጠባሏ ጎጆ በኮቸሮው መዓዛ ታጠነች። እየበሉ ወደ ትርክቱ ተመለሰ።

"በአንቱ ነው ወይስ ውስጠ ወይራ ቢኖረው? ሦስቱም የቅኔ መምህር ሊሆኑ የበቁት?" አለ ጌርማ ኮቸሮ እየጎረሰ።

"ምሥጢር ሊኖረውም ይችላል። ነገር ግን ግምት እንጂ የተረጋገጠ ነገር አይደለም።

"ምን ነበር ግምቱ?" አለ ጌርማ።

"ተግተህ ከተማርህ ወደፊት ትደርስበት ይሆናል። መነሻውን እንጂ መድረሻውን ዛሬ ላይ አልነግርህም። የሊቃውንት ምሥጢር እንደ መሆኑ ሊቅነትህ ሊጨምር አንድ ቀን እነግርሃለሁ። ዛሬ እግረ-ተማሪ ነህ። አበው ለእግረ-ተማሪ ምሥጢር ይደብቃሉ። እኔም እንዳባቶቼ ነኝ። ለምሥጢር እንደምጨነቀው ለነፍሴ ተጨንቄ አላውቅም። መነሻውን ግን አጥብቀህ ያዝ። ምሥጢሩን ወደ ፊት እነግርሃለሁ።" አለ ገሞራው።

የቀረበችዋ ኮቸሮ እያለቀች ነበር። ኮቸዋሮን ጨርሰው ሁለቱም አሣረጉ። ጌርማ ወደ መጽሐፉ አቀረቀረ። ገሞራው ወደ ውጪ ወጣ።

PDF Compressor Free Version

ጠቢቡ ሉሬ መላ-ጎንደርን ዙሪው የሕይወትን ውኃ አሥሠው ለመጻጓው ትውልድ ለማቋደስ ያለሙት ዓላማ ግብ መትቷል። ሊቁ ሩሬስም ቅኔ በማስተማር የድርሻቸውን እየተወጡ ነው። አብነቱ እንደ አብነትነቱ ቀጥሏል። እነሆ በሕዳር መጨረሻ በጎንጅ ጽላሎ ጤፍ አጨዳው ተጀመረ። ገበሬው ውሎ አዳሩ ከጤፍ ማሳው ሆነ። ዘመቻውን የሩሬስ ተማሪዎች ቁጥር በቀን ሥራ አጀቡት። ገሞራው የቀን ሥራ እየሠራ መማሩን ቀጠለ። የጎንጅ ሰዎች የቀን ሠራተኛ ሲፈልጉ ማለዳ ተነሥተው ከሊቁ ሩሬስ ቅኔቤት በር ይቆማሉ። ተማሪዎች ጸሎት እንደ ጨረሱ ወደቀን ሥራ ይሄዳሉ። የጥቅምትን የወር መጨረሻ ተከትለዉ የጎንጅ ደብረ-ጥበብ አበቦች መቦረቅ ጀምረዋል። ንቦች በጽጌ ረዳ አበቦች ራስ ላይ ብን ብን ይላሉ። አንዱ ቀስሞ ሲሄድ ሌላው መጥቶ አበቦችን ይስማል። ከናፍራቸውን ይመጠምጣል። ከዚያም የቻለውን ቀስሞ ለሌላው ባለተራ ይለቃል።

የቅኔ ተማሪዎች የቀን ሥራ እየዋሉ ማለ ይገዛሉ። ደበሎ ይሸምታሉ። ዛላ በርበሬ ገዝተው ያንን አድርቀው ብትን ድቁስ ያስደቁሳሉ። በእንተ ማርያም ብለው ለምለም እንጀራ ሲያገኙ በድቁስ እየነከሩ ይበላሉ። ሲያጡ ጦም ያድራሉ። በዚህ ሳምንት የሊቁ ቅኔ ቤት ፈዘዝ ማለት ጀምሯል። ዘራፊዎች ሳይቀር የቀን ሥራ እየፈለጉ ከባላገር እርሻ ሂደው ጤፍ እያጨዱ ናቸው። ገሞራው በቀን ሠላሳ ብር ተቀጥሮ ለጤፍ አጨዳ እየሄደ ሳምንቱን አጭዷል። በዚህም ከመቶ ብር እስከ አምስት መቶ ብር በማግኘቱ የብር ጌታ የሆንሁ መስሎታል። ከኮቸሮ

PDF Compressor Free Version

የተረፈውን ጥቂት መሸመት ለማረግ እየሰሩ ነው። በዚህ ሂደት አንድ ወር ያክል ጉባኤው ታጠፈ። ሊቁ ፋሪስ በግላቸው መጻሕፍ ሲመለከቱ ሰነበቱ። ዛሬ ግን ቀኑ ዐርብ ነው። ገሞራው የዐርብን ቅኔ በዐጨዳ ለመጠው። አንድ ባላገር መጥቶ በሰላሳ ብር ገዘቱ ወስደ ከዐጨዳው ደፋው። ወስደ ከአጨዳው ላይ ሲደፋው አብሮኝ የሚያጭድ መስሎኝ ነበር። ባላገሩ ግን ዘበናይ ቢጤ ነው። ወጣቱን ባለቅኔ ጅምበር ሳትወጣ ዐጨዳ ሰልፎ ወደ ቤቱ ውልቅ አለ።

ገሞራው ሰበቻው ሲያጭድ ሦስት ሰዓት ሆነ። ያ ያደረው ብርድ በጠዋቷ ፀሐይ መፍታታት ጀመረ። ልክ ዐራት ሰዓት ሲሆን ደቡ አጫጆች ቁርሳቸውን በትኩስ ሽሮ ልፊው ማጭዳቸውን እየሞረዱ መጥተው ላጨዳ ተሰለፉ። ትንሽ እንዳጨዱ በገሞራው አጠገብ አንድ ምሥጢር አዋቂ ካህን መጥተው ተሰለፉ።

ትንሽ እንዳጨዱ "ተማሪ!" አሉ ካህኑ።

"አቤት" አለ ገሞራው።

"ና - ቅድድሞሽ እንግጠም።

"ደስ ይለኛል" አለ ገሞራው።

የግንባር የግንባራቸውን ጤፍ ሲያባርሩ ገሞራው ቀድሞ ወጣ። ካህኑም ትንሽ ቆይተውየግንባራቸውን ጨረሱ።

ከዚያም "ወደዚህ ሀገር ለትምህርት ነው ወይስ ለሌላ ጉዳይ መጥተህ ነው?" አሉ በግዕዝ ቋንቋ።

"እንዴት ለሌላ ጉዳይ ሊሉ?" አለ ገሞራው በዚያው በግዕዝ ቋንቋ።

"አመሰግናሀ ለቅኔ ትምህርት ነው ወይስ ለዚያች ነገር ነው ማለቱ ነው?"
አሉ ካህኑ ማጭዳቸውን አቁመው።
PDF Compressor Free Version
"ምን ማለትም ነው አባቴ?" አለ ገሞራው።
"ለታብር ብለህ መጥተህ እንደሆነ ብዬ ነው" አሉካህኑ።
"እኔ የመጣሁት ቅኔ ለመቀጸል ነው" አለ ገሞራው።
ካህኑ ዐጫጆች እንዳይሰሙ በማእዝ ቋንቋ ለገሞራው ያወሩት በአማርኛ ሲተረጎም ይህንን ይመስላል።
"ጎንጅ ደብረ-ጥበብ የቅኔ ሀገር እንደሆነ ይታወቃል። ቅኔ ለመቀጠል መምጣትህ ሸጋ ነው። ነገር ግን የቅኔ ሀገሩ ብዙ ነው። ዋሸራ ማርያም ብትሔድ መወድስ እንደ ውኃ ሲቀዳ ትሰማለህ። ዋድላ ድላንታ ብትሸገር የቅኔ ፍትፍት ይጠብቅኻል። ከዚህ ከደጋው ምጣ ቀራንዮ ብቅ ብትል የቅኔ መዓት ታገኛለህ። በመላ ጎንደር ሞልቶ ተርፏል። ደብረ መድኃኒት ፌዞዴ ሐና መፈጠሪያው ነው። በትግራይም በከፊል ለመናገር ያህል አክሱም ጽዮን ፣ ሽሬ እንዳ ሥላሴ፣ ጨለቆት ሥላሴ፣ በወሎ ላስታ-ላሊበላ፣ ዋድላ ድላንታ፣ ቦሩ ሜዳ ሥላሴ፣ በሸዋ አንኮበር መድኃኔ ዓለም፣ አንኮበር ጊዮርጊስ፣ ደብረ ብርሃን ሥላሴ፣ አዲስ ዓለም ገዳም፣በምሥራቅ ጎጃም ዲማ፣ ደብረ ኤልያስ፣ ደብረ ማርቆስና ሌሎችም ቦታ የቅኔ ትምህርት ይሰጣል። በዚህ በቅርቡ ደግሞ ሜጫ መረዳና ይልማና ዴንሳም የቅኔ ሀገሮች የምሥጢር ፈለጎች ናቸው። ቅኔውን በእነዚህ ሀገራት ተዘዋውረህ መማር ትችላለህ። ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ግን ከዘረዘርኩልህ ሀገራት ሁሉ የተለየ ነው። ዕትብቴ ስለተቀበረበት ብቻ ሳይሆን፣ ስለተቀበረው ጥበብ ማውራት ፈልጌ ነው።

PDF Compressor Free Version

ማሰትም ግድ ... አትኔው ጎን ለጎን የጥበብ ሀገር ጭምር ነው። ዳሞ የለበሰ ጥበብና ሙጃ የወረረው ምሥጢር ጭምር አለበት። ልጆቻችን ሳይንሱን በሚገባ ተምረው ተመራምረው ምልክት ያላዩናል ብለን እኛ ጥጃና በግ እየጠበቅን ወደ አስኳላ ትምህርት ላክናቸው። መጨረሻቸው ግን አላማረም። ተፈጥሮን ማጥናት ትተው በሱቲ ተምረው መጡ። እንደነፍስ አባት ያናዘዝሁህ ምን አልባት ቅኔ ጨርሰህ ለዚህ ጉዳይ መጥተህ እንደሆነ ያልሁት ከዚህ ላይ ነው።" ብለው በግእዝ ቋንቋ ሊያወሩ ቆይተው ጥቂት ፋታ ከወሰዱ በኋላ ቀጠሉ።

"እንዳንተ በትኔም በእድሜም ጠና ያሉ ተማሪዎች ወደዚህ ሀገር የሚመጡት ለቅኔ ብቻ አይደለም። የማርያም ልጅ አንድዬ እጁን ታጥቦ ከፈጠራት ውኃ ሊጠጡ ጭምር ነው። መምህር ፋሬስን መጠየቅ ትችላለህ። በደብሩ በስተመስዕ በኩል ደብር ወንዝ የሚባል ስውር ደሴት አለ። በገጽ ስታየው የገጠጠ ዋሻ ይመስላል። ከዋሻው ውስጥ ተዋነይ የሰወራት ትንሽዬ ደሴት አለች። ከደሴቷ ውስጥ የምትፈልቅ ውኃ አለች። ተዋነይ በጥበቡ ተመራምሮ ያገኛት ውኃ ናት ይባላል። ተዋነይ የቅኔ ሊቅ ሊሆን የቻለውም ያችንን ውኃ ጠጥቶ ነው የሚሉ አሉ። ዛሬ ላይ ድምጧ ይሰማል እንጂ እንደ ልብ አትገኝም። ሊቁ ፋሬስ ግን ከዓመት አንድ ጊዜ ወደወንዟ ወርደው ስዉሯን ውኃ በጥበብ ገልጠው ይጠጧታል ይባላል። ያን ጊዜ ሀገር ይጠባቸዋል። ውስጣቸው በቅኔ ይጥለቀለቃል። ከፋሬስ በቀር የማያውቃት የለም። እሱም ምሥጢር ጠባቂ ነው። ለማንም እንዳይናገር የገበዘ ማርያም አባ ዮና አውግዘውታል። የሊቁ ምላስ በአባ ዮና ግዝት ተሸብቧል። እኛም ምንም

ተጠቃሚ ባንሆንም የአባቶቻችን ጥበብ እንዳይደፈር ተግተን እየጠበቅን
ነው።" አሉ ዳዊት በማንበብ ቃኘቋቸዉ አጫጆች እንዳይሰሙ።
"ከዓመት አንድ ጊዜ ወደ ወንዟ ወርደው ስዒራን ውኃ በጥበብ ገልጠው
ሊጠጡ ያየ አለ?" አለ ገሞራው።
"ያየስ የለም። ነገር ግን ምሥጢሩ እነሆ ልጀ!።
"ውኃዋን በጥበብ ገልጠው በሚጠጡበት ቀን በዐል ያደርጋሉ። በዐሉን
የሚያከብሩት ለብቻቸው ሲሆን በዚህ ቀን ለተማሪ ቅኔ አያስነግሩም።
ማስም አይገስሱም። ጉባኤ አይዘረጉም። ሞገስ የሚባለውን ትልቁን ካባ
ለብሰው፣ ፋሬስ ተሸመ የሚባለውን ሻሻቸውን ጠምጥመው፣ ክቤታቸው
ሳይወጡ ያከብሩታል። በዚህ በዓል ላይ በተዋነይ የዋርካ አክናፎች
አምሳል ስድስት ሻማዎች ያበራሉ። ሻማውንም የሚሠሩት ራሳቸው
ናቸው። ከሻማው ዘንግ ላይ "ታብር ታብር ከሣቲተ ምሥጢር" የሚል
ጽሑፍ ይከትቡበታል። የመጀመሪያውን ትልቅ ሻማ ሲለኩሱ አንድ
መወድስ ለፈጣሪያቸው ይዘርፋሉ። ሁለተኛውን ወፍራም ሻማ ሲለኩሱ
በያሬድ ስም ሁለተኛውን መወድስ ይደግማሉ። ሦስተኛውን ቀጭን ሻማ
ሲለኩሱ መወድሱን በዮሐንስ ገብላዊ ስም ወደ ዋድላ ደላንታ ዞረው
ይሠልሳሉ። በዐራተኛው የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዐት በባለትኔው
በክፍለ ዮሐንስ ስም ቅኔ ይዘርፋሉ። አምስተኛውን ሻማ ከመለኮሳቸው
በፊት የማዕበል ፈንቴ ዘዋሸራን ስም ከሻማው ላይ ይከትቡበታል።
ከዚያም ወደ ዋሸራ ፊታቸውን አዙረው የተራራው ማሚቶ እስኪደባለቅ
መወድሱን በማዕበል ፈንቴ ስም ያንጎደጉዱታል። የመጨረሻውን ግን
ቅኔ የሚዘርፉት በ"ታብር" ና በተዋነይ ስም ነው። ስድስቱን መወድሶች

PDF Compressor Free Version

PDF Compressor Free Version

ዘርፈ ብዙ አቀራረቡ ሌላ ሰባተኛ ሽማ ለኩሰው ወደ ፈጣሪ እጁን ያደርጋሉ። ከሻማው ላይም "ልብየ ርእየት ብዙን ጥበበ" የሚለውን የጠቢቡን የሰሎሞንን ቃል ይሕትቡበታል። ይህን የሚያደርጉት "ከሩ ባዕድ አምልኮ ሆኖ ከእግዚአብሔር እንዳያስቀይሙ በማሰብ "ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጠቢቡን የሰሎሞንን ቃል መጠቀማቸውም እንደ ሰሎሞን ከፈጣሪያቸው ጋር ልብ ለልብ መገናኘታቸውንና ጠቢብ ዘምድር ላደረጋቸው የጥበብ ጌታ ምስጋና ለማቅረብ ነው። በንሱን አክብረው ሲጨርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ዐርባ ይሰግዳሉ። ሌላ አካል ሲጠይቃቸው ግን ቅንጣት ትንፍሽ አይሉም።"

ካህኑ ፋታ መስደው ቀጠሉ።

"በአርግጥ ሌላም ከተዋነይ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ አላቸው። ተዋነይ ባንድ ወቅት ታብርን ለፍየሉ አጠጥቶ ፍየሏን አርዶ አዋራደ ለሊቃውንቱ አብልቶ የታብርን ምሥጢር በመረቅ ለትውልድ ማስተላለፍ ፈልጎ ፍየሏ መወድስ እየዘራች ቅኔ እየዘረፈች በስለት ታረደች። ሥጋዋን እንቱ አደይ ወጥ እንድትሠራው ተዋነይ አዘዘ። ደቀ መዝሙሩን ጨንራዋን አጥቦ እንዲመጣ ወደ ወንዝ ላከው። አደይ ከወጡ ብትቀምስ ቅኔ ዘረፈች። ሌላም ለሴት አእምሮ የከበደ ምሥጢር ጻነሰች። ደቀ መዝሙሩም በበኩሉ ከፍየሏ ጨንራ በሸንበቆ ለንጢ ቆርጦ ቢቀምስ አእምሮው በእውቀት ተመላ።

ተዋነይ "ታብር› ፍቱን የቅኔ ውኃ እንደሆነች ሲረዳ ምን አደከመኝ ይሸውና በሁለቱ ዘመዶቹ ተረጋገጠ ብሎ ለሊቃውንቱ ሳይታበዝ መልሶ ተወው...::"

PDF Compressor Free Version

...ይህንን ምሥጢር በለቀቁ በፋራስ ልቦና ተጸንሶ እንደ ሽል ሲገላበጥ ለዘመናት ይኖር ነበር። ዛሬም ይህንን ጥንታዊ ታሪክ ለመድገም ያመጡ። ባንድ ወቅት ተዋነይን መሆን አማራቸው። ወደ ታቦር ምንጭ መረዱ። "ታቦር"ን በቅምጫና ቀድተው ተመለሱ። እንደ አያት ቅድመ-አያታቸው ተዋነይ ቂቧን ፍየል ከታሠረችበት ገመድ ፈትተው በግድ የታቦርን ውኃ ጋቷት። ቅኔ የሚያዘርፈውን ውኃ አጠጥተው ወደ ዱር ይዘዋት ፈረጠጡ። ራሳቸውን 'ተዋነይ' ፍየሏን ደሞ 'ገላንሸ' ብለው ለመጥራት ጊዜው ረዘመባቸው። ቅኔ ትዘርፋለች። ሀገር ጉድ ይላል። የቅኔ ሊቃውንት ይደመማሉ ብለው መወድስ ከአንደበቷ እስኪዘንብ መጠባበቅ ጀመሩ። ጥቂት ቆይቶ ክልግሥ-ጠሊ ቅኔ ተቀዳ። ዱሩ ግን እንደተዋነይ ልሣነ-ጠሊንና ልሳነ-ሰብእን የሚያዛምድ ጥበብ አልነበራቸውም። ልሣነ-ጠሊን በእዝነ-ሰብእ ግን መስማት ቻሉ። ወዲህም ታቦርን ለዚህ ቁም ነገር በማድረሳቸው አጥብቆ ደስ አላቸው። በዚያ ሰሞን ዳግማዊ ተዋነያ ተብለው ሊጠሩ ፈልገው ነበር። ትዕቢት ነው ብለው መልሰው ተዉት። ፍየሏን ግን አርደው አወራርደው ግጥም አደርገው በልተዋል። መረቋንም ጠጥተዋል። ይህንን መላ የጎንጅ ካህናት እናውቃለን። እስክ ተስ ብለህ ቅረባቸው። ይጸድቁብኻል። አፈለግህ ይህንን ታሪክ በቅኔ መልኩ ገልጠህ ተለማመጣቸው። በዓመት አንድ ጊዜ ውኃዋን በጥበብ ሲገልጡ ይጸድቁብኻል..." ብለው ወደ ዐጨዳው አቀረቀሩ።

ገሞራው ማጭዱን እንደጨበጠ አጨዳውን አቁሞ ለብቻው ማውጋት ጀመረ።

PDF Compressor Free Version

"ይህንን ምሥጢር እንደ ሰው ታሪክ ቁጥሬ ላልፈው አልችልም። እሰከ መጨረሻው እሄድበታለሁ። ከምንፈጂ ለመጠጣት አንጠርጠሰ ድረስ እወርዳለሁ።" እያለ በውስጡ ይለፈልፍ ጀመር።

"ለካ የኢትዮጵያ እናቶች ሊቅ ጸንሰው ሊቅ ሊወልዱ የቻሉት እንዲህ ነውኣ ነገር እየተጋቱ ነው? ጎጃሞች ባለ ቅኔ እየተባሉ የሚወደሱት ከዚች ምንጭ እየተንጨለፉ ነው? ለካ እነ ዶሪ ሀገር አቋርጠው ጎንጅ ደብረ-ጥበብ የከተሙት ታብርን ፈልገው ነው? እንዲህማ ከሆነ የሐበሻ እናቶች ከውኃዋ እየጠጡ ሊቅ ጸንሰው ሊቅ መውለድ አለባቸው! በእርግጥ ከዚህ በፊት ወልደዋል።" ሳያስበው ጮኽ ተናገረ።

"አሁንም እደግመዋለሁ የሐበሻ ሴቶች ምሁር ጸንሰው ሊቅ ይወልዳሉ። ከሐበሻ እናቶች በቀር ሊቅ የምትወልድ እናት በሌላ ሀገር የለችም፤ ሰምቼም አይቸም አላውቅም። ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በቀር ከእናቱ ማሕፀን ሊቀ-ሊቃውንት ሆኖ የተወለደ በዓለም ላይ ያለ አይመስለኝም። ሊኖርም ይችላል። በሌላው ዓለም ሊቃውንቶች ተወልደው ይሆናል። ነገር ግን ሊቅነታቸው የመጣው ከብዙ ድካም በኋላ ነው። ስለዚህ ደደቦች ናቸው። "ማለትም!" አለ ገሞራው የግእዙን ሊቅ ዲልማንን አስቦ።

"ዲልማን ከእናቱ ማሕፀን ሲወጣ በቅኔ ሳይሆን በደም ተጠቅሎ ነው የተወለደው። ኋላ ግን ሀገራችን ገብቶ ከእኛ ሊቃውንት ግእዝ አጥንቶ ግእዝ ስለጻፈ የግእዝ ሊቅ ተብሎ ስሙ በሊቃውንት መዝገብ ሰፍሯል። የኢትዮጵያ ባለቅኔዎች ግን ከእናታቸው ማሕፀን በደምና በቅኔ ተጠቅልለው ዱብ ይላሉ። ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ ዕትብቱ ሁሉ መወድስ

PDF Compressor Free Version

የሆነውን ሁኔታ ዛሬ ገና ተረዳሁ።" ብሎ ጮኸ ተናገረ። ደቡ አሚዶች ያዘደ መስሏቸው አልቢናቸውን ዘቅዝቀው ቆመው እየታዘቡት ነበር።

አሱ ግን ከንፈሮቹን እንደ ድር እያደራ ቀጠለ። በፀሐይ ሐሩር የደረቁ ከናፍሮቹ እጥፍ ዘርጋ ማለት ጀመሩ።

"ወደ ኋላ ከሄድን ኢትዮጵያዊ ባለ ቅኔ ሁሉ ከዚች ምንጭ ጠጥቷል ማለት ነው። ይች ምንጭ ከዚህ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ተነሥታ ዐባይን ትቀላቀላለች። ሁሉም ኢትዮጵያዊ የግዮንን ድፍርስ ውኃ ይጎነጫል። እንደበራ ዝቅ ብሎ ያፍስዋል። ያን ጊዜ ጥንካሬን ከሊቅነት ጋር ይይዛል። ጠንካራ ሐበሻ ሁሉ በዚህ አማካይነት የመጣ ነው ማለት ነው። ባለቅኔው ሁሉ ከዚች የተገኘ ነው ማለት እችላለሁ። በሁሉም ባለቅኔ ደም ጋር ይች ምንጭ አለችበት ብሎ አፍን መልቶ መናገር ይቻላል። ተዋነይ በዚህ ግብር አልፎበታል። የግእዝ ቅኔዋ እመቤት ገላነሽ አባቷ ከቅኔ ማኅሌት ሆነው ቅኔ ሲዘርፉ በእናቷ እቅፍ ላይ ሆና ቅኔ ነጥቃቸዋለች። ተዋነይ እንደ ፊረስ ደመና እየጋለበ መኖሩ በዚች ውኃ አማካይነት ከሆነ ተዋነይን ጠንቋይ ብሎ የዘለፉ ይፈረድበታል። 'ተዋነይን ጠንቋይ ብላችሁ የተሳደባችሁ ንስሓ ግቡ' የሚል ስብከት ያስፈልጋል። ተዋነይን ጠንቋይ ያለ ምላስ፣ የሰማ ጆሮ ራሱም ጠንቋይ ነው። ተዋነይን ጠቢብ ብሎ የተቀበለ ግን ታብርን ይጠጣ ዘንድ ተፈቅዶለታል። የቅኔዋን እመቤት ገላነሽን እንደ ተቀበልን ተዋነይንም ክፉ ስም ሳንሰጥ መቀበል አለብን።" እያለ መናገር ጀመረ።

PDF Compressor Free Version

ደቡ አሚኖች አሃሰሙ ጎንጅ ጽላሎ ቱም የመምህርት ገላነሽን የሕይወት ታሪክ ለልሥጀ መተረክ ነባ።

ማለ ሰምና ወርቅ እንዝር:ድ እመይቱ ገላነሽ የጽላሎ የሰት የቅኔ ሊቅ ነበሩ። የዘረፏቸው ቅኔዎች ዛሬ ድረስ ከለቃውንት አእምሮ በላይ ሆነው ይኖራሉ። ምሥጢራቸውን ቀርቶ የሰምና ወርቁ አጣጣል የራስ ምታት የሆኑ ቅኔዎች አሏቸው። ከአሳቸው ቅኔ-ቤት ቅኔና ሐዲስ ኪዳን እንዲ ተማሩ የሚያወሩ ሊቃውንት እንኳን ሊተረጉሟቸው አልቻሉም። ዘነፍሱ የተወራረደ ሊት ሊፈታቸው አልቻሰም። በአቅሜ የያገኳት የእመይቴ ገላነሽ ቅኔ አለች። የሚተረጉምልኝ ካጣሁ ስንት ጊዜ ሆነኝ? እያለ ሰራሁ አወጋ። በደቦ ሰብሰብ ብለው የሚያጭዱ ባላገሮች ጀሯቸውን አቆሙ። ምሳ ላይ ለአጫጆች ከመጣው ጠላ ከልክ እላፊ ጨልጦ ስለነበረ ሞቅታ ዮቱሰሃው መሰላቸው። እሱ ግን መለፍለፉን አላቆመም።

"የቅኔው ሊቅ መምህር ማዕበል ወልደ ሕይወት ደማቸው ከቅኔ እንጂ ከእናታቸው ደም ብቻ የተቀዳ አይደለም። ተዋነይንማ ከየትኛውም ሊቅ ተርታ አሰልፎ ማወዳደር እንዴት ይችላል? እንደ ስሙ ነበልባል ነው። እሳተ ነበልባል ፊለገ ቅኔያት የሚሉ ቅጽሎች መልአከ-ነበልባል ተዋነይን ሊገልፁት አይችሉም። ከቅኔው ጎን ለጎን በዚች ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ሰባት ዓመት ያገለ ሞትን የገዘተበት ጥበቡ ለዓለም ተመራማሪዎች ክፍት መሆን አለበት። ከዛሬ ጀምሮ ተመራማሪዎች ድንኳናቸውን ከዚህ አፋፉ ላይ መወጠር አለባቸው። የድንኳኖች አውታር በጎንጅ ሰማይ ሥር ይተከለላል። ድንኳኖች ይወጠሩ። እኔ በረዳት ተመራማሪነት ሳይሆን እግር እያጠብሁ ድንኳናቸውን በካስማ እወጥራለሁ። ለሰባት

PDF Compressor Free Version

ዓመት ሞት ለመሸሽ የሚደረግ ጥበብ በጥናትና ምርምር ሰንዶች መሞት አለበት። ጠቢባንን ጥሩ። ምሁራንን ጥሩ። ሊቃውንት ይምጡ። ወግ ነጋሪዎች ታሪክ አዋቂዎች አፈ ታሪኩን ሰተመራማሪዎች ይንገሩ። አዋድ ይታወጅ። የምርምር ክበሮ ይደለት። የጥበብ በገና ይደርደር። የምሥጢር ነጋሪት ይጎሰም። ኢትዮጵያ ወደጥንት ስልጣኔዋ ትመለስ። ሌሎች አገራት ሰውን የሚገድሉበት ጥይት እንጂ ሞትን የሚገሉበት ጥበብ የላቸውም። እኛ ግን አለን።" እያለ ጠበል እንደገባ ሰይጣን ይወሸክት ያዘ።

ከዚያም ማሬውን ዘሕዋ ላይ እያውለበለበ መስበኩን ቀጠለ።

"እስኪ አስቡት? ለሰባት ዓመት ያኽል ክሞት ማምለጥ ቀላል ነገር አይደለም። አዳም ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ። ማቱሳላ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ዓመት ምድርን ቆፈረ። እኒህ ሁሉ ሞትን ገዝተው ሳይሆን በተፈጥሮ ቸርነት ነው። ዛሬ ላይ በሆን ዘጠኝ መቶ ዓመት ለመኖር ይቅርና ዘጠና ዓመት መኖር አይችሉም ነበር። ፈርዖንን ያሸነፈው ጠቢቡ ሙሴ የሥጋ ሞትን የሚያሸንፍበት ጥበብ ስላልነበረው እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ። በናባው ተራራ ተቀበረ። የኛ ጠቢብ ተዋነይ ግን ያለ ፈቃዱ ሞት የማያሸንፈው ጀግና ነው። ሞት የተፈጥሮ ጉዳይ ነው እየተባለ አዳሜ በሠላሳ ዓመቱ መቃብር ሲወርድ ዝም ይባላል። ለምን ተዋነይ የተፈጥሮ ጉዳይ ነው ሳይል አወገዘው? ይጠና ያልሁት ይህንን ምሥጢር ነው። እንወያይበት ያልሁት ጥበቡን ነው። ጥበቡ እንኳ ቢቀር የሀገራችን ዐፈር ይጠና ዐፈሩ ከተጠና የሰው ባሕርይ ተጠና ማለት ነው የሚሉት የኔ መምህር ወድያው አይደለም።

PDF Compressor Free Version

ፕሰው ተፈጥሮ ከአሳት፣ ከነፋስ፣ ከውኃና ከዐፈር ነው። ውኃና ዐፈርን ማጥናት ሰውን ማጥናት ነው። ውኃው ከተሰማማው፣ዐፈሩ ከደለው፣ አንደ ተዋነይ ሰባት ዓመት መጨመር ቀርቶ መሲሕ ክርስቶስ ጸንም እስኪመጣ መኖር ይችል ይሆናል? እንዴት የሰው እድሜ ከኤሊ እድሜ ያንሳል? ኤሊ ስንትና ስንት ዓመት ኑራ እንደምትሞት አሰቡ? ኤሊን ያጠና ተመራማሪ የሰውን እድሜ በደንብ ተመራምሮ ማወቅ አለበት። የምርምሩ መነሻ ደግሞ የአዳምና የሣቱሳላ ረጅም እድሜ አንድ ሚሣያ ነው" ብሎ ሊቀጥል ሲል "አይዞህ ጎበዝ! ተማሪ! እንዲ ቁመህ ቀረህኮ! ጀሎ በል! እስኪ! ጀሎ ዘልልሉት!::" የአንድ አሜጅ ድምፅ ከሰሣቡ አናበበው።

ወዲያውኑ ከቅዠት ዓለም ወጥቶ ለዐጨዳ እንደ አጎንበሰ ሁለት ጣቶቹን አጨዳቸው። ደሙ እንደ ጉድ ፈሰሰ። ደሙ የታብር ውኃ ቢሆንለት ተመኘ። ደሙን እያዘራ ወደ ቅኔ ቤቱ ተመለሰ።

PDF Compressor Free Version



ምሽቱ ለዐይን ያዝ አድርጓል። ድንግዝግዝ ብሏል። ወፎች በክንፋቸው አየሩን ይቀዝፋሉ። በየዋርካው ቅጠል ይንጠላጠላሉ። ጢ..ር..ጢ..ር.. ሌ..ር.. ብር.ር.ር. ሸር.ር.. ብትን..። ሲ....ጥ.. ሲ....ጥ... ጸ....ው ጸ...ው ምሊል ዜማ ያዜማሉ። ገሞራው ከጢፍ አጨዳ መልስ ቅኔ ለመንገር ወደ ሊቁ ሲያመራ ለቁ የሠርክ ጸሎታቸውን ለማድረስ ወደ ደብሩ ሊያልፉ ከትልቁ ዋርካ ሥር ተገናኙ።

"ደኅና ዋልክ አካሌ?" አሉ ሊቁ።

ገሞራው በትሕትና እጅ ነሣ።

"ከዚህ ሳምንት ወደ ገባኤ ብቅ አላልህም? ምን ችግር ገጥሞህ ይሆን?" አሉ ሊቁ ፋራስ።

"በርበሬ የምገዛበት ብትን ድቁስ የማስደቁስበት ገንዘብ አጥቼ የቀን ሥራ እየሠራሁ ነው።"

"ለመሆኑ ስለት ማጭድ ጨብጠህ ታውቃለህ? ጣቶችህ እንደ ኩሚ ጣቶች ለስላሳ ናቸው። ስለት ማጭድ ቀርቶ ቅቤ ያንዳልጣቸው ነው የሚመስሉት?" አሉ ሊቁ ፋራስ።

"አዬ የኔታ! በደንብ ነው የማጭደው። በአርግጥ አጨዳ የጀመርሁ ቀን ገና ሦስት ሰዓት ሳልሠራ እጄ ቆሰለ። ቆዳዬ እንዳሮጌ እባብ ሰንኮፍ እየተላጠ መሄድ ጀመረ። በንፍር ውኃ እንደተቀቀለ የዶሮ ላባ ቆዳዬ እምሽክ አያለ በጠበጠኝ። ጥርሴን ነክሼ መከራውን አስለመድሁት። ከሳምንት በኋላ መድማት አቆመ። በዐራተኛው ቀን ቁስሉ ደረቀ። ቀስ

PDF Compressor Free Version

እያለ በሂደት አንድ ወሰን አውጥቶ መጣ። አሁን ግን ችግር የለበትም። መከራውን ለምዶታል።" አለ ገሞራው።

"ጥሩ ነው! እንደ ገብረ ጉንዳን በጋ ሰብስቦ ክረምት ከቅኔ ቤት ሳይለቁ ጀበራ ሳያበዙ መቀጸል የተማሪ ወግ ነው። የሊቅነት መገለጫ ነው። እኔም እንዳንተ ተማሪ እያለሁ መተከል ወርጄ በረኃ ገብቼ የበረኃ ዱላ እንግድ ነበር። ሱማያ ዘንግ እየነገድሁ ነው የተማርሁት። ሱማያ ዘንጉ እየጠፋ ደኑ እየተጨፈጨፈ ሲሄድ ወደ ጭራ ንግድ ዞርኩ። የፈረስ ጭራና ሱማያ ዘንግ በመነገድ የሚደርስብኝ ኑጋዴ አልነበረም። በተግባረ ዕድ መሰለፍህን ወድጀዋለሁ። ቀጥልበት። አንዳንድ ሰነፍ ተማሪ በጋ ተቀምጦ ኑሮ ክረምት ድው ሲል ቅኔውን በረሀብ ምክንያት አቋርጦ ወደ እናቱ ቤት ይፈረጥጣል። እንደሄደ ለአረም ይሰለፋል። በጋ ለፍቶ ጥሮ ያወቃት ሰምና ወርቅ ቅኔ ብንን ብላ ጠፍታ ትከርማለች። በጋው ሲወጣ እንደ ገና ይመጣና ቅኔ ሲጀምር ጥሬ ሆኖ ቁጭ ይላል። እሱን ሰማስቀኝት ልቤ ውልቅ ሲል አባሻለሁ። በጋ ሲያቆስለኝ ባጅቶ ክረምት ሲመጣ እንደ ልማዱ የውኃ ሽታ ይሆናል። አንተ ሠናይ ነገር ዝምረኻል። በጋ ሸክፍ ሸክፍ አርገህ ክረምት እንደ ልብህ ስትማር ትከርማለህ።" አሉና

"በል በደኅና እደር" አሉ ሊቁ ፋሬስ ገሞራውን እያሰናበቱ።

"የኔታ! ካሳሰቸገርሁ ቅኔ ልነግር ፈልጌ ነበር?።" ገሞራው በትሕትና ተማፀናቸው።

PDF Compressor Free Version

እንደ ቀድሞ አሞራ ሳት ተቁን ስትሙሀ እደር ብለህ ከፊረድህ አንቀጥል?" አሉና ወደ ትልቁ ዋርካ ጠጋ ብለው ተቀምጠው "በል እሺ ቀጥል::" አሉ ሊቁ::

ገሞራው እንደ ልማዱ ዐይኑን አስለምልሞ አንዱን ጅምሮ ሌላ ቅኔ አመጣ:: ደግሞ ያንን ከአፉ አድርሶ ወደ ሌላ ተነሣወረ::

"እረ አንዱን በል?" አሉ ሊቁ - ከዘያም ከዘያም ሲረግጥ ተመልከተው::

ገሞራው ሕሊናውን ሰብስቦ፤

"እንተ ፋሬስ ዘጎበብከ ክሡት::

ደምረኒ ሊተ ለዘይመጽእ ዓመት::" አለ::

"ምን ማለት ነው አሉ?" አሉ ሊቁ ግእዝ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሙ ይመስል::

"መወድስ ስትዘርፍ ከታብር ስትጋት::

"እኔንም ጨምረኝ በሚመጣው ዓመት::" ማለት ነው አለ ገሞራው::

ትልቁ ሰው ፋሬስ ገጻቸው ተሰዋወጠ:: አንገታቸውን አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ ሌላ ጊዜ ወደ ግራ እያቅለሰለሱ ቆይተው ከዘራቸውን አንሥተው ሲንደረደሩ ገሞራ የማጭድ ሲሳይ የሆነ ጣቱን እያውለበለበ ተፈተለከ:: ሊቁ እንደ አመለጣቸው ሲያውቁ እየተራገሙ ወደ ቤታቸው ተመለሱ:: ገሞራው እያቃሰተ ጎጆው በር ሲደርስ ታሪኩ ኮቸሮ አኪችሮ ተቀበለው:: በተለመደው ፍቅረ ቢጽ ትክሻ ለትክሻ ተሳስመው እግሩን እንዲታጠብ ሰብ ያለ ውኃ አቀረበለት:: ገሞራው ቀጫጫ እግሩን በቀጫጫ እጁ እያጠበ የቅኔ ክርክር ተነሣ::

"እስኪ ዛሬ የዘረፍከውን ቅኔ ባክህ አብራራልኝ" አለ ታሪኩ::

PDF Compressor Free Version

"ዛሬ ግን ያቺ ቅኔ ድንቅ አይደለም። የኔታን በጣም አሰቆጥቷቸዋል። እኔንም አሳፍሮኛል። በቀረብኝ ቡትሻለኝ ነበር።" አለ ገሞራው፤

"እንዴት ቅኔህ ሊያሳፍርህ ቻለ?"

"የቅኔ ዐመጣጤ ልክ አልነበረም።"

"እንዴት ልክ አልነበረም ስትል?" አለ ታሪኩ

ገሞራው እግሩን እያደረቀ በርበሬ የተረጨዬ በመሰሉ ዐይኖቹ በጎንጅ ጽላሎ ሰማይ ሥር ጨረቃን እየተመለከተ ማብራራት ቀጠለ።

እነሆ ከባዱ የጎንጅ ጽላሎ ጨለማ በጨረቃዋ ብርሃን ከምድረ ገጽ ጠፍቷል። የዋርካው አክናፎች በጨረቃ ብርሃን ተንቦግቡገዋል። ኩልል ብሎ የሚታየው የጨረቃ ብርሃን ለጎንጅ ባላገሮች ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ነው። በጨርቃ ብርሃን ተጠቅመው ሌሊት ሌሊት ለዐጨዳ ይሰለፋሉ። በጨረቃ ብርሃን ያጨዱትን በፀሐይ ብርሃን ይወቃሉ። ራሱም በጨረቃ አጭዷል። ዛሬ ግን ቀን አጨዳ ላይ ከባላገሮች የማይወረወሩ አፈ ታሪኮች መስጠውታል። በደቦ ዐጨዳ ላይ የሰማውን የተዋነይን ገድል የፋራሽን ጥበብ መነሻ አድርጎ የዘረፈው ቅኔ በሊቁ ዘንድ አልተወደደለትም።

ታሪኩ ያኳቸረውን ኮቸሮ ከነድስቱ አቀረበ። ጸሎት አድርሰው መጎራረስ ጀመሩ። እየተጎራረሱ በቅኔው ጭብጥ ይወያዩ ጀመር።

"አየህ ወንድሜ?" አለ ገሞራው በጨረቃዋ ፍዝ ብርሃን ታሪኩን እየፈለገ። እግሩን በጨረቃ ብርሃን እያደረቀ ኮቸራዋን እየጎረሰ ቀጠለ።

"አየህ ወንድሜ! አጨዳ ላይ ሳለሁ ማለዳ ላይ አእምሮዬ ፍዝዝ ብሎ ነበር። እስከ ሦስት ሰዓት ድረስ ብቻዬን ካሮጌ ባድማ ከጤፍ ማሳ

PDF Compressor Free Version

ተሰልፎ ሳጭድ የሕይወቱ ዘይቤ እያስጠላኝ መጣ። ከወደ ዐራት ሰዓት አካባቢ ብዙ ባላገር ለዐጨዳ ሲመጣ ትንሽ እንደ መንቃት አልሁ። ስድስት ሰዓት ሲሆን የጤፉ ባለቤት ሦስት እንስራ ጠላ፣ ሁለት ወራንታ እንጀራ፣ ሦስት ሰታቴ ድስት ሽሮ ይዞ ብቅ አሰ። ቀትሩ ሲበረታ ለምሳ ተቀመጥን። ጠላው እንደኦት አይነት ጠላ መሰለህ። አንዱ ራስ ፈጥርቆ ይጥላል። ሁለት ጽዋ ፉት ብዬ ባላቆም ኑሮ ጎርው አርጎ ገደል እንደ ሚጥለኝ አንዳች ጥርጥር የለውም። አብሽ ማለት ነው። ሽታው ብቻ ያሰክራል። በተለይ እንደኔ ያለ ባዶ ሆድ ተማሪ አይችለውም። ከመጣው ጥቁር ጠላ አንዳንድ እንዳልን ምድረ-ገበሬ ሞቅ እያለ ሄደ። ሞቅታው ሲበዛ ብዙ ነገር ተነገረ። ብዙ ታሪክ ተወራ። በመኻል ጎንጅ ለምን መጥተህ ነው የሚል ጥያቄ ተጠየቅሁ። ለቅኔ ትምህርት እንደመጣሁ ብናገር ያመነኝ አልነበረም። በሀገር የታወቁ ካህን ያልጠበቅሁትን ነገር ነገሩኝ።" አለ ገሞራው ወደቀን ትዝታው እየተመለሰ።

"ምን አሉህ?" አለ ታሪኩ ለመስማት ጓጉቶ።

"የነገሩኝስ ብዙ ምሥጢር ነበር። ነገር ግን አፈ ታሪክ ስለሆነ ፍሬ አልባ ይመስለኛል። ስለ ታብር የነገሩኝ ምሥጢር ግን ልቤን ነክቶታል።"

"ምን ምሥጢር አወሩህ?" አለ ታሪኩ።

"ወጉን የገፖመሩት እንደተለመደው ተዋነይ በስወራት ውኃ ነበር። ስለታብር። እንደምታውቀው የጎንጅ ካህናት ባለቅኔው ተዋነይን እምላክ አሳክሎ መተረክ ልማዳቸው ነው። እንደቄስ አደፍርስ ያለው ማን ፈጠረህ? ቢሉት ተዋነይ ማለቱ አይቀርም።

PDF Compressor Free Version

ካህኑ በገጻሙ በስተመስዕ በሕል በጥበብ የተሰመረ ደሴት እንዲሁ ጠቁመው ስሙ ደብር ወንዝ ይባላል። ድሮ ከዋሻው ውስጥ ሳውሰጥ የምትፈልቅ ምሥጢራዊት ውኃ ነበረች። ተዋነይ ሱባኤ ገብቶ ያገኛት ቅኔ የምታዘርፍ ውኃ ናት። ሴትም ሆነ ወንድ ሲጠጣት ግጨው የቅኔ ሊቅ ሆኖ አርፍ ይላል። ምሥጢራዊት ውኃ ናት። ሊቁ ፋሬስ ከዓመት አንድ ጊዜ ወደወንዟ ወርደው ከውኃ ይጎነጫሉ። ተዋነይ የቅኔ ሊቅ ሊሆን የቻለው ያችንን ውኃ ጠጥቶ ነው። ከተዋነይ ለጥቆ የተነሡ የቅኔ ሊቃውንት ከውኃው እየጠጡ ሊቀ ሊቃውንት ሆኑ። ከዚች ጉደኛ ውኃ ከጠጡ ሊቃውንት መካከል አልፎ አልፎ ዋና ዋናዎቹን በስም አንሥተው ጠቃቀሱልኝ። ያንን ስሰማ ስሜቱ አይሉ ስለ ነበር በተመስጠ ውስጥ ሁኜ ሳጭድ ጣቶቼን ቆርጬ ቆርቈዙ ጣልኳቸው።" ብሎ በደበሎው የደበቀውን ሊቆረጥ የተቃረበ ጣት አውጥቶ ለታሪኩ አሳየው። ሁለት ጣቶቹ የአልቢን ሲሳይ ሆነዋል። ታሪኩ ስቅስቅ ብሎ አልቅሶ ገሞራውን ኮቸሮ እያጎረሰ አናዘዘው።

ገሞራው ቀጠለ።

"እናም ሊቁ ፋሬስ በዓመት አንድ ጊዜ ውኃዋን ሲጠጡ ቅኔ ይዘርፋሉ የሚለውን ዝክረ ታሪክ መነሻ አድርጌ፦

"አንተ ፋሬስ ዘጥበብከ ክሡት።

ደምረኒ ሊተ ለዘይመጽእ ዓመት።" ብዬ በቅኔዬ ውስጥ የልብ መሻቴን ተናገርኩ።"

"ምን ማለት ነው?" አለ ታሪኩ።

"መወድስ ስትዘርፍ ከታብር ስትጋት፤

PDF Compressor Free Version

አእንም ጨምረኝ በሚመጣው ዓመት" ማለት ነበር ብሎ ትርጉሙን ተናገረ።

"አየይዘም እውነት ለመናገር ቅኔው ልብ አንጠልጣይ እንዳልሆነ ለእኔም ጭምር ገብቶኛል። የኔታን ያስቆጣቸው ሰጊዜው የቅኔው መድከም መስሎኝ ነበር፣ እንደምታውቀው ሊቁ ውትፍትፍ ቅኔ ልል መወድስ አይወዱም። መወድሱ እንደ ጥቁር ቡን ደበልበል ብሎ ሲወርድ ነው እንደበሽር ጊደር የሚቁነጠነጡት። እኔም የቅኔው ቅለት ያስቆጣቸው መስሎኝ ነበር። ነገር ግን የቅኔው መወናገር እንዳላስቆጣቸው ተረዳሁ። የቅኔው ውንግርግርነት ቢቀፋቸው ኑሮ እንደ ተለመደው ሞሽልቀው ያርሙት ነበር እንጂ ተቆጥተው ባዶ ሜዳ ጥለውኝ አይሄዱም ነበር።" አለ ገሞራው።

"ታዲያ የኔታን ምን አስቆጣቸው?" አለ ታሪኩ።

ክህሎ የሰማሁትን የታብርን ምሥጢር በቅኔዬ ውስጥ አስገብቼ ማምጣቴን እንደ ጠሉት ተረዳሁ። ገና ቅኔው ከአንደበቴ ሲወጣ ድንገት ዘራፍ አሉ። ተበሳጩ። የውስጣቸውን ምሥጢር ማወቅ ባልችልም የኔታ በዓመት አንድ ጊዜ ከዚች ምሥጢራዊት ወንዝ እንደሚጎነጩ ማወቄን የወደዱት አይመስለኝም። የጥንት መምህራን አንዳንድ ውስጠ-ወይራ ነገር እንደሚጠቀሙ የታወቀ ነገር ነው። ነገር ግን እንዲህ ያለውን ውስጠ ምሥጢር ማንም እንዲያውቅባቸው አይፈልጉም። የሊቁም ፍርሐት ይህ ይመስለኛል። ከዓመትም ሆነ ከሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ከውኃዋ ይጠጣሉ እየተባሉ እንደሚታሙ ማንም ያውቀዋል። ነገር ግን ይህ ውስብስብ ምሥጢር ከአሳቸው አልፎ ከኔ መድረሱ

PDF Compressor Free Version

የደስታ ስሜት አልሰጣቸውም። አንደ ሽንፈት የቆጠሩት ይመስሳሉ። በእርግጥ የኒታ የተዋንይን ምሥጢር ሰመጠበት ወይም የሀገርን ምሥጢር አደባባይ ማውጣት እንደማይገባ ዘወትር ይሰፈልፋሉ። በኩል ግን ያለውኃዋም ቢሆን የተዋጣሳቸው ባለ ቅኔ ናቸው። ሊፈጥራቸው የቅኔና የምሥጢር ሰው ናቸው። ውኃዋን ቢጎነጨም ባይጎነጨም ቅኔው የተፈጥሮና የድካም ሀብታቸው ይመስለኛል። ምን አልባት ያስቆጣቸው ሀገራዊ ምሥጢር ተደብቆ መኖር ሲገባው የጠፋ አጨዳ ማድመቂያ ሆነ ብለው ይመስለኛል።" አለ ገሞራው ግምቱን እያስቀመጠ።

"ታዲያ ይህ ምን ያስቆጣል?" አለ ታሪኩ ነገሩን ቀለል አድርጎ።

"ታዲያ ይህ ያስቆጣል! በጎንደርም እንዲህ ዐይነት ተመሳሳይ ታሪክ እንዳለ ይነገራል።" አለ ታሪኩ።

"እንዴት?" አለ ገሞራው በፈንታው የጎንደርን ምሥጢር ለመስማት ጓጉቶ።

"ሊቁ ፋሬስን ጨምሮ የጎንደር ዐይናማ ሊቃውንት እንደሚናገሩት ከሆነ በጎንደር ውስጥ ጎልቶ ያልተነገረ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ አለ። ያም ማለት በጎንደር ዐርባ ዐራቱ አድባራት መካከል ባንዱ ደብር ጉያ ውስጥ የሕይወት ምንጭ እንዳለች ይወራል።

"ቢጫዋን ከተማ ጎንደርን ታውቃት የለ?" አለው ታሪኩ ገሞራውን ጠልቆ እየተመለከተ።

"በደንብ እንጂ። ኧረ እንዲያውም ጎንደር በዓታ ለማርያም አቋቋም ልቀጽል ሄጄ ላለ በልደታ ማርያም ታች ባሉ መንደሮች ዘወትር በእንቶ

PDF Compressor Free Version

ማርያም ለማለት፣ ለንበት ሲመጣ ደግሞ ለአገልግሎት ልደታ ማርያም
ብቻ እል ነበር። ትዝ ይለኛል ማጎሌት ሲቆም ቁጭ ብዬ ከበሮ
እቈረቍራለሁ፣ ከበሮ በመቈርቈር የሚተካከለኝ ባለ ከበሮ ያለ
አይመስለኝም። ወረብ ሲወረብ ከበሮ ሲመታ ነፍሴ በፍሥሓ ስልምልም
ትላለች። የደብሩ የአቋቋም መሪጌታ ወረቡን ሲቃኘው አካሉ ምድራዊ፣
ድምፁ ሰማያዊ፣ ይመስለኝና እኔን ብቻ ሳይሆን የሚሰሙትን ሁሉ
በድምፁ ሠረገላ አሳፍሮ ሰማየ-ሰማያት ያሳርገናል። ከድምፁ ጣዕም
የተነሣ ጨርሶ ዝም ሲል ነው እንጅ ምናውቀው መጨረሱን ማን
ያውቃል! ሁሉም በተመስጦ ነው ሚያዳምጠው! በቅኔ-ማኅሌት
እየተጐማለልሁ የልደታ ማርያምን የአለቃ ገብረ ሐናን ትልቁን ከበሮም
የማዘርጠው (የምደልቀው) እኔ ነበርሁ። የአለቃ ገብረ ሐና እንደሆነ
የሚነገርለትን ትልቁን ከበሮ በወገቤ አንገድፌ ማኅሌቱን እንቧለሌ
እየዞርሁ አኖጋው ነበር። ማኅሌቱ ተፈጽሞ ቅዳሴ ሲገቡ ደግሞ
የለንበቱ ክብር ይእቲ ቅኔ ይሰጠኛል። እቀኛለሁ። ልደታ ማርያም
የተቀኘሁት ቅኔ ብዙ ነበር። ዛሬ ጠፋብኝ። ሲፈጥረኝ ተመልሶ የራሴን
ቅኔ እንዳስታውስ አድርጎ የፈጠረኝ አይመስለኝም። የራስህን ቅኔ መልሶ
በማስታወስና የጎንደርን ውስጠ-ምሥጢር በማወቅ በኩል አንተን
አደንቃለሁ። የቀለም ሠረገላ የታሪክ ሽርፍራፊ በአንተ ዘንድ የተሟሉ
ናቸው። ከከንፈርህ ጠብ አይሉም። በእኔ በኩል ያደረ ቅኔ ቋንጣነው
የሚለው ብሒል ጭንቅላቴ ላይ ወጥቶ የራሴን ቅኔ ያደረ ቋንጣ ቅኔ
ነው እያልሁ ስገድፍ እኖራለሁ። የስንት ሊቃውንት መወድስ በውስጤ
ሲሰርፅ የራሴ ቅኔ ግን ብንን ብሎ ይጠፋብኛል። በወቅቱ ብጽፈው ኑሮ

PDF Compressor Free Version

ዛሬ ላይ ዳንስ ያለ የቅኔ መጽሐፍ ይወጣው ነበር። ጎንደርን ይህንን በመሰለ መንፈሳዊ አገልግሎት አውቃታለሁ፤ ታዲያ ለምለሚ ጎንደር ከዚህ ታሪክ ጋር ምን ተመሳሳይ ታሪክ አላት።" አለ ንጭራው።

ታሪኩ ተመቻችቶ ተቀምጦ ስለ ጎንደር ምሥጢራዊት ውኃ ማብራራት ጀመረ።

"ስፍራውን ለይቼ አላወቅኩትም። ነገር ግን ጎንደር ውስጥ ድንቅ ውኃ እንዳለች ይነገራል። ውኃዋም የጥበብ ውኃ ናት ይላሉ ውስጥ አዋቂዎች። ስሟንም የሕይወት ውኃ ሲሉ ሊቃውንቱ ይጠሯታል። ይች የሕይወት ውኃ ስሊቃውንቱ የተገለጠችበት ዘመን እምብዛም ግልጥ አይደለም።ብቻ በዓለም ሰገድ ፋሲለደስ መናገሻ በጎንደር ውስጥ ብዙ የተቀበረ ታሪክ አለ። ጎንደርም የሊቃውንት መካነ ጥበብ ነበረች። ዛሬም ርዝራዡ አልጠፋም። ክምሥጢር ባለቤቶች ሊቃውንት ክፈሶቹን ለመጥቀስ ያኽል መምህር ኤስድሮስ አንዱ ነበሩ።

መምህር ኤስድሮስ በመጽሐፍ ትርጓሜ በኩል ከፍ ያለ ቦታ አላቸው። ሊቃ ሊቃውንት ብቻ ሳይሆኑ ርእሰ ሊቀ ሊቃውንት ጭምር ነበሩ። ሊቁ ከማስተማር ጎን ለጎን የትርጉም ሥራ በመሥራት ጊዜያቸውን ያሳልፉም ነበር። ለብዙ ዘመናት ገባኤ አስፍተው ካስተማሩ በኋላ ድጋሜ ወደ ገዳም ሂደው በመቶ የሚቆጠሩ ብራና መጻሕፍትን አንብበው ከጥንቱ አስበልጠው ተርጉመዋል። በዚህ ጊዜ የጎንደር ውኃ ምሥጢር ጭምር ተገልጠላቸዋል ይባላል። ከዛ ወዲህም እሳት የላሱ ሊቃውንት ተፈጥረዋል። ፀሐየ-ልዳ ሮብዐም ዘጐጃምን ጨምሮ በሃይማኖተ አበው ትርጓሜ አንቱ የተባሉት "ጌታዬ ምህርካ" በዚህ

PDF Compressor Free Version

ታሪክ ውስጥ ይጠቃለላሉ። እኒህ ዐራት ዐይና ሊቃውንት በጎንደር ከተማ ጉባኤ አስፍተው ሊቃውንቱን ካራቱ ማዕዘን ሰብስበው አስተምረዋል። ተርጉመዋል። ተራቀዋል። ተፈላሰፈዋል። ነገሩን በጎሁኤ አርገውት እንጂ ደመና እየጋለቡ ግብፅ ድረስ ወርደው ከግብፅ ጠቢባን ጭምር ግንኙነት ነበራቸው። ይህን የሚያወቁ ግብጻውያን አድናቆት ጭምር ይቸሯቸው ነበር...።" አለ ታሪኩ።

"እሺ ከዚያስ?"... ገሞራው በጉጉት ጠየቀ።

"ጎንደር ደብረ ጥበብ ጋር የሚያመሳስላቸው ምሥጢር አንዱ ይህ በደመና የመጫን ጥበብ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በጎንደር ከተማ ውስጥ ክዓመት አንድ ቀን ብቻ ቡልቅ ቡልቅ ብላ ሊቃውንቱ ይጠሟት የነበረችዋ የጎንደር ውኃ ታመሳስላቸዋለች። ውኃዋ የሞት መድኃኒት ናት ይባላል። ይችንን ምሥጢራዊት ውኃ በጣት የሚቆጠሩ ሊቃውንት ጠጥተዋታል። ተጠቅመዋታል። አሁንም አንዳንድ ውስጥ አዋቂ ሊቃውንት በዓመት አንድ ጊዜ ከውኃዋ ይጎነጫሉ። በውኃዋ ምክንያት እድሜአቸው እንደማቴሳላ ይጎተታል። ሙሉ ጤናቸው ይጠበቃል። ምሥጢር ይገለጥላቸዋል። ምን አለፋህ? ሁሉ ነገር ይስተካከልላቸዋል ይባላል።" አለ ታሪኩ።

"እንዴት ያለ ምሥጢር አመጣህ? እስኪ በደንብ አውጋኝ?" አለ ገሞራው በምሥጠት።

"የጎንደር ነገር ይህ ብቻ አይደለም! እኒህ አበው የተሰወረው የሚገለጥላቸው የተደመሰሰው የሚብራራላቸው ከምንጫ ሊጎነጩ ነው። አለቃ ገብረ ሐና በራሱ ይችንን ምንጭ ለማፈላለግ ጎንደርን ደጅ

PDF Compressor Free Version

ጠንተዋል ይባላል። እንዳንኋት ግን የተጻፈ መረጃ የለም። በአፈ ታሪክ እንደሚወራው ከሆነ አለቃ ሊሞቱ ጥቂት ቀን ሲቀራቸው ሱባኤ ላይ ነበሩ። ሱባኤው ዐርባ ቀናትን የፈጀ ነበር። መጀመሪያው ንስሓ ለመግባት፣ ጻግመኛ ሒናቸውን ለመጠበቅ፣ ሦስተኛ ከዚች ታሪካዊት ውኃ ተንንጭተው እድሜ ጠግበው ለመሞት ነበር። ውኃዋ እንደ ዕፁ ሕይወት አሮጌውን መልሶ የማደስ ኃይል እንዳላት የሚያውቁት የቅኔው ሰው አለቃ ገብረ ሐና ለዐርባ ቀን ያኽል ተንበርክከው ዐመድ ቅመው ተማፅነዋል። ፈጣሪ ግን አልገለጠላቸውም። አለቃም ዐጻፋውን በቅኔ መልሰዋል። ጌታን ተጣርተው 'ድሮ ሙሴ ሙሴ እያልክ በረሃ ለበረሃ ትንከራተት እንደ ነበር ማላውቅ እንዳይመስልህ። አውቃለሁ። ለኔ ግን ለዐርባ ቀን ሙሉ ድምዕህን ነፈግከኝ ሲሉ ከሱባኤ ቡኋላ አምላክን ወቅሰዋል።

ኋላም ንስሓቸውን እንዳልተቀበላቸው ቆጥረው ይመስላል፦

ኮንኖ ኃጥአን አምላክ ኢይረብሐከ ምንተ።

አፍቅሩ ጸላዕተክሙ እንዘ ትብል አንተ።" ብለው ከፈጣሪ ጋር ሙግት ገጥመው በቃሉ ከሰውታል። የቅኔ ምሥጢርም 'አንተ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ትላለህ። አንተ ግን ጠላትህን በእሳት ትቀጣለህ' ማለት ነው። ለአለቃ ገብረ ሐና ጎቡአ የቅኔ አምላክ ለሌሎች ቅርብ ነበር። ከውኃዋ ሲጠጡ ሰማይ ተከፍቶ ይታያቸዋል። የገደፉት ቀለም ቁልጭ ብሎ ይመጣላቸዋል። የገደፉትን ያስተካክላሉ፣ የረሱትን ያስታውሳሉ። በጤናም በሕል እንደ ዛሬው ሕክምና ሳይኖር ከውኃዋ ተጠቃሚዎች

ነበር። ዓመቱን ሲታመሙ ኑረው ከዚች ውኃ ሲጠጡ እንደ ንስር
ይታደሱ ነበር ይባላል።" አለ ታሪኩ።
PDF Compressor Free Version
"እውነት?" አለው ገሞራው።
"ወላዲቴን! ይህ ታሪክ ትክክል ነው። በጎንደር ያሉ ቀደምት ሊቃውንት
አፋቸውን መልተው የሚናገሩት ነው። ዛሬም ጠቢብ ከተገኘ ይህንን
ታሪክ ቢመረምረው ሊደርስበት ይችላል። በጎንደር ብዙ የሚጠኑ መካነ
ጥበባት እንዳሉ ለአንተ መንገር ለቀባሪ እንደማርዳት ይቆጠራል።
ከወርባዕቱ እንስሳ እስተ-ደብረ ብርሃን ሥላሴ ያሉ ውስጣዊ ዋሻዎች
በሙሉ የውስጥ ታሪካቸው ገና አልተጠናም። በአፈ ታሪክ ግን ብዙ
ይባልላቸዋል። አፈ-ታሪክ ደግሞ ባጋጣሚ የሚፈጠር ነገር አይደለም።
አፈ ታሪክ በሚነገርበት አካባቢ ከዘመናት በፊት እውነታው ነበር ማለት
ነው። አፈ ታሪክ ከነበረን የቀደመ ማንነት የጠፋ እውነት መኖሩ ግልጽ
ነው። ትንሽ መናገር የሚከብደው ያች ውኃ የምሥጢር ምንጭ ስለ
ሆነች የሊቃውንቱን ጭንቅላት ትሞርዳለች የሚለው ነው። ከደቂ ዳኛ
ከአልጋ ቁራኛ ትገላግላቸው እንደነበር ግን በጊዜው የነበሩ ሊቃውንትም
በትርጓሜአቸው ጠቁመውናል።" አለ ታሪኩ።
ገሞራው የአብነቱን ትርጓሜ አንድ ባንድ በሕሊናው ቃኘው።
ታሪኩ ግን ቀጠለ።
"በአብነታችን ትርጓሜ ውስጥ ስለ ጎንደር ውኃ ሲተረጉሙ ሊቃውንቱ
እንዲህ ብለዋል።" ብሎ ወደ ዋናው ፍሬ ሐሳብ ሊሄድ ሲል
"አንተ ወሸከሬ ሁላ! ምን እንደምትል ሰምቻለሁ! ተነሣ! ጥፋኝ።" አሉ
ሊቁ ፉሬስ ድንገት ደርሰው አጭር ከዘራቸውን ከገሞራው እናት

PDF Compressor Free Version

አንጣጥረው ውኃ ሊያደርጉት። ገሞራው ማዕዱን ረግጠ ተሰመጠ። ታሪኩ በሊቱ ጉልበት መንፈስ ተሸልኮ ቁልቁል ፈረጠጠ። ሊቱ ፋሬስ ላረ ገሞራውን ለመግደል በሚመስል መልኩ እየተፈላሰጉት ነበር። ምሥጢር በማውጣቱ የለቅነት ደማቸው መውረዱ።

PDF Compressor Free Version

# ሰኟ

የቅኔ ጊዜ። የሊቁ ቅኔ ቤት እንደ ሞቀ ነው። ቅኔ ሲዘረፍ ክርክሩ ይደራል። መወድሱ ሲፈፋም ዓለም ትረሳለች። ተፈጥራ እንዳልተፈጠረች ትሆናለች። ታሪኩና ገሞራው ከታብር ውኃ ፍለጋ ጎን ለጎን የቅኔው ተማታሬ ሆነው ቀጥለዋል። ታብር ወደፊት ለማንኛው ተማሪ እንደምትገለጥ የታወቀ ነገር የለም። እድለኛውን ትፈልጋለች። ሰውና እድል ሲፈላለጉ እንዲኖሩ ሁሉ ተማሪና ታብርም ሲፈላለጉ ይኖራሉ። የቅኔ ዘራፊዎችም ታብርን በልባቸው እየፈለጉ ለጊዜው በቅኔ ትምህርት መቆየቱን እንዳማራጭ ወስደውታል። የዛሬውን ጉባኤ ገሞራው እንዲጀምር ሊቁ ምልክት ሰጡት። ያንን ለለማላጋ አንገቱን እንደቀትር እባብ ወደ ሕዋ ሲመዝዘው ከረጅመ· ተዋነይ ዋርካ ሊደርስ ምንም አልቀረው።

ወደ ላይ ተዝለጠ፤

"አንክርኩ አንሰ ምሥጢረ- ፋሬስ ማዕምር

ሕሰመ ኢይሰቲ ወይነ ወስቴ እንበለ አሐቲ ታብር።" አለ ገሞራው።

ፋ...ሬ...ስ.. ያለውን ቃል ለማውጣት እያንዳንዷን ቀለም ሲረግጥ ለማይ ምድሩ ተጨነቀ። ከተዋነይ ዋርካ ላይ ተሰግስገው የሚያንጎላጁ አዕዋፍ ጭንነው ተነሡ። ፋ..ሬ..ስ.. ላይ "ስ" ን ይባስ ብሎ ረገጠው። ሦስተኛውን ቃደል በከናፍሩ ሲረግጥ ሌላ "ስ" አልጠራም። ያለው ግን ውበት ፈጠረበት። ቅኔነቱን አሠመረበት። አንግግር ዘይቤ አወጣው። ሰማየ-ሰማያት ሰቀለው።

PDF Compressor Free Version

ሊቁ ዐይናቸውን ወደ ተልቁ ዋርካ ወረወሩ። ዋርካው ላይ የተቡሃኑ ወፍች በወፍ ቋንቋ ይሰላታሉ። ሁሉቱ የወፍ ጥንዶች ርስ በርሳቸው ይጎራረላሉ። ወንዱ ወፍ ሰሌቷ አጉርሶ ቀሪውን ለራሱ ይበላል። ክናፍሮቻቸው እንደሮማን ፍሬ ቀይሃን ናቸው። የእግሮቻቸው ጥፍር እንሰሰላ የሞቁ ይመስል። በቀይ ተከትበዋል። ያማምራሉ። ከፊሎቹ አዕዋፍ ቀትሩን ለማሳለፍ ከቅጠሉ ጫፍ ላይ ተንጠልጥለው ያንጎላጃሉ። ሊቁ ዐይናቸውን ከተልቁ ዋርካ መልሰው ወደ ገሞራው ወረወሩት።

ከዚያም "በል እስኪ ተርጉመው?" አሉ ወደ ገሞራው እየተመለከቱ። ግእዙን ወደ አማርኛ ቋንቋ አምጣው ማለታቸው ነው።

"የፋሪስን ምሥጢር አደንቃለሁ እኔ።
በሕልሜ በውኔ፣
ደግሞም በአጭር ቅኔ
ወይን ጠጅ ተቀድቶ ሲሰጠው በክብር፣
የድንቁ ልጅ ሊቁ ፋሪስ የኔ መምህር
ሴላ አይጎነጭም ከታብሯ በቀር።" ብሎ ግእዙን ወደ አማርኛው ገልብጦ በቃሉ አነበበው።

ሊቁ ከእግር እስከራሱ በአንክሮ ተመለከቱት። ገሞራው በቅኔ ወግ ተርጉሞ እንደጨረሰ ሊቁ በሻሻቸው አፋቸውን ደብቀው ተኩተመተሙ። ቀጥሎም

"ለመሆኑ ከትናንትና ጀምሮ የታብርን ምሥጢር የዘከዘክልህ ማን ነው?" አሉ።

PDF Compressor Free Version

ጎኔ የኔታ! ይህ ሀገር ያወቀው ፀሓይ የሞቀው ጉዳይ ነው። ምሥጢር አድርገው ያየዙት እርስዎ ብቻ ነዎት። በጎንጅ ጽላሎ ውስጥ "ቅኔ የምታዘርፍ ታብር" የምትባል ውኃ ትገኛለች ብሎ ሀገር ያወራዋል። ከእኔ ጆሮ እንኳ የደረሰው ገና "አ..ቡ..ጊ..ዳ" መቁጠር ስጀምር፣ የፊደል ገበታ ስነካ ነው። በዐራቱ ማዕዘን ወጣ ብሰው ቢጠይቁ ይህንን ወሬ ከአልፎ ሂያጅ አንደበት ሊሰሙት ይችላሉ። በእርግጥ ምሥጢርነት ግን አለው።" አለ ገሞራው ወደ ፊት ለመቀጠል ፈልጎ።

"ደግሞ ምን ቀረ?" አሉ ሊቁ።

"ምሥጢሩማ! 'ታብር' በጎንጅ ደብረ-ጥበብ እንደምትኖር እንጂ ለማን እንደምትገለጥ አለመታወቁ ነው። ጎቡአ ሆና ተሰውራ መኖሯ ነው።" አለ ገሞራው በፍርሐትና በድፍረት ውስጥ ሆኖ። ፍርሐቱ ታብርን ለልጠጣ ከቅኔ ቤት እባረራለሁ ብሎ ሲሆን ደፍሮ መናገሩ ደግሞ መፍትሔ እንደሚያመጣ እያመነ።

"ቅኔ ማስተማር ከጀመርክ ብዙ ጊዜ ነው!" አሉ ሊቁ ፋሬስ በከዘራቸው መሬቱን እየቆረቆሩ።

ያ ሁሉ ወፈ-ሰማያት ተማሪ ጆሮውን ወደሊቁ ቀሰረ።

"ቅኔ ማስተማር ከጀመርሁ ጀምሮ እስከ ዛሬ ብዙ ሊቃውንት ጎንጅ ገዳምን ተሳልመዋል። ከፊቴ ቁመዋል። መወድስ ዘርፈዋል። እስከ ዛሬ ያስተማርኋቸው በጠቅላላ በትሕትና የታነጹ ናቸው። እንደ አንተ ያለ ደፋር ግን አጋጥሞኝ አያውቅም። ሲበዛ ወሬኛና ባለ-ቅኔ ሳትሆን አትቀርም። ትናንትና መጥተህ ይህን ታኽል መወሸከትህ ተደፋፋሪ እንደሆንክ ነገረኝ?" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

PDF Compressor Free Version

ታሪክ ሳይሰሙ ቀን እኔን ሁነው ዓለም ስምምን ሲያደንት በሰመ. የኔታ
አለ ገሞራው ንግግራቸውን ሳይፈጽሙ መኻል ገብቱ።
"እንዴት?" አሉ ሊቁ።
"አቡጊዳ ስቃጥር ጀምሮ እንደሰማሁት ታብር በዚህ ሀገር አለች። እናንተ
ጎንጅች ግን ትውልዱ እንዳይጠቀምባት የዋሻውን በር በዕፀ መሰውር
ዘጋችሁት። ትውልዱ መክሥቱን አጥቶ ጥበብ አልባ ሆኖ ሲባዝን ዝም
ብላችሁ አያችሁት። ይባስ ብሎ ተዋነይ በጥበቡ ሰውሯት ተሰወረ
ብላችሁ ትውልዱን ተስፋ አስቆረጣችሁት። ቅኔውን የማትችሁ
አደረጋችሁት። አዲሱ ትውልድ በሀገሩ ጥበብ እንዳይኮራ በሩን
ከረቸማችሁበት። ለምርምር ክፍት ማድረግ ሲገባችሁ ፊት ነሣችሁት።
ሁሉንም ቅርስ ነው እያላችሁ የትውልዱን ዕድል አጠበባችሁበት።
ቅርስና ተፈጥሮን መለየት አልቻላችሁም።" አለ ገሞራው በድፍረት።
ሊቁ ገጻቸው እሳተ-ነበልባል ለበሰ። ፊታቸው የበለለ ሸላ መሰለ።
በንዴት ጦፉ። ጥቂት ቀዘቀዝ ብለው
"የአድሜ ዘልዛላነት ገና ብዙ ያሰማኛል። በዚህ ከዘራ ገርልጩ ሳላባርህ
ወደቅኔው ተመለስ። በል! በል! ከታብር በቀር ሌላ ውኃ አይቀምስም
ያልኸውን አፍታታው?" አሉ ሊቁ ፋሬስ ብስጭታቸውን እንደምንም
ተቆጣጥረው። የቅኔ ሊቃውንት በቅኔ ቤታቸው ከዚህ በላይ ምሥጢር
ይሰማሉ። ነገር ግን በትእግስታቸው ምድር ማለት ናቸው። ተማሪ
ከዚያም ከዚያም የለቃቀመውን ሁሉ ቅኔ አድርጎ ሲፈጥረው
ተበሳጭተው ከተማሪ ጋር ግጭት ውስጥ አይገቡም። ሊቁም
የገሞራውን ትንታኔ በዚህ መልኩ ተረዱት።

PDF Compressor Free Version

ገሞራው ቀጠለ።
"ታብር በቀር ሌላ ውኃ አይቀምሱም የሚለውን እንኳ ከስሚ ስሚ የሰማሁት ወሬ ነው። ማረጋገጥ አልችልም።" አለ ገሞራው።
"እንዴት?" አሉ ሊቁ።
"ወደ ርስዎ ቅኔ ቤት ከመምጣቱ በፊት ብዙ አድባራትን ዙሬያለሁ። በተልሚድነት ተሸክርክሬያለሁ። ከሀገር ሀገር ስዞር እንደ ሰማሁት ከተዋነይ ሐረገ-ተውልድ ጀምሮ እስከርስዎ ድረስ በሳንጅ ደብረ-ጥበብ ያሰፉ የቅኔ ሊቃውንት ጠጅ አይጨልጡም። አረቂ በዞረበት አይዞሩም። እየተባለ ይወራል!።" አለ ገሞራው የራሳቸውን ገድል እየተረተረ።
"ወይ አዛኜቱ! ሰው እንዴት ባላወቀው ገብቶ ይፈተፍታል? በፈጣሪ! የማይኖም ወሬ እኮ ነው።" ብለው ትንሽ ተመናጨቁ።
"ምክንያቱን ታውቃለህ?" ሊቁ ጠየቁ።
"ያው በቅኔዬ አሳምሬ እንደገለጥሁት በተዋነይ ሐረገ መምህራን የተፈለፈሉ የቅኔ-ሊቃውንት የወይን ጠጅ አይቀምሱም። ጠላ አይጠጡም። በወይኑ ፈንታ ቀዝቀዛ ውኃ በጠላው ፈንታ 'ታብርን' እየጠጡ ቅኔ ይዘርፋሉ እየተባለ በሀገር ሲወራ ሰምቻለሁ። በቅኔ ያመጣሁትም ይህን ምሥጢር ነው። ደግሞ ይህንን ምሉዕ ታሪክ ከእኔ አንደበት መስማት አይጠበቅብዎትም። ከእርስዎ ብሰማ የተሻለ ነገር ይሆናል። እውነታውን እረዳለሁ።" ብሎ በትሕትና ወደ መሬት አቀረቀረ።
"አንተ ደፊ ሀገር አጥፊ የሚሉት አበው እንዳንተ ያለው ነው።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

PDF Compressor Free Version

'አንገት ደፊ ቅኔ ዘራፊ' የሚለው ደግሞ እንደርስም ያሰውን 'ነው ሊላቸው ፊልን መደፋፈር ስለመሰለው መልሶ ተወው።

ሊቁ ፋሬስ በፈንታቸው ቀጠሉ።

"እኛ ባለቅኔዎች በንብረተ ሰቡ ዘንድ ብዙ ብዙ እንደምንባል አውቃለሁ። የስድብ ስም ቢያጡልን የተለያየ ነገር እየወሰዱ ቅኔ ቢዘርፉም ፍትወት ይጠናወታቸዋል የሚል እኩይ ስም ይሰጡናል። የቅኔ ሊቃውንትን አስማተኛና መተተኛ አድርገው የሚቆጥሩ ሰነፎችም እንዳሉ አውቃለሁ።" አሉና ዐይኖቻቸውን መልሰው ወደ ተዋነይ ዋርካ ወረወሩ። የደረቁ ቅጠሎች ከግንዳቸው ተነቅለው በግንዱ ላይ ተረብርበዋል። ቀደም ሲል በሕገ-ወፍ ሲንሾራረሱ የነበሩ ወፎች ይዘምራሉ። ጀምበር እየተዘቀዘቀች ነው። ፊቷ ፍም መስሏል። ሊቁ ዐይናቸውን መልሰው ወደመሬት ወረወሩት። ከፊታቸው የቆመው ገሞራው በቅኔው ወኔ እንደተመሰጠ ነው። ጓደኛው ታሪኩ ደግሞ ወረፋውን ይጠባበቃል።

ከዚያም ሊቁ ቀጠሉ።

"በእርግጥ ማንኛውም የመጠጥ ዘር በአብነት መምህራን ዘንድ እንደ ሰይጣን የተወገዘ ነው። በቅኔ ሊቃውንት ዘንዳ ደግሞ ግዝቱ ይጠናል። ሲጀመር ባለ ቅኔ ለስፍሳፋና በየመሸታ ቤቱ ዙክ ዙክ ማለት የለበትም። ቁጥብና ምጥን ሰው መሆን አለበት። ጥበብ ጽሙና ትወዳለች። ብሕትውና አድባሯ ነው። ቅኔም ከኪነጥበብ አንዱ እንደመሆኑ የሥጋ ምኞት ጠላቱ ነው። እውነተኛ ባለቅኔ ብዙ የማያወራ አርምሞን የሚመርጥ መሆን አለበት። ለፍላፊ ባለቅኔ ቀስ በቀስ ሰባኪ ወደመሆን

PDF Compressor Free Version

ዝቅ ይላል። ባለ-ቅኔ ሊሆን አይችልም። ቀባጣሪ ቁስ እንኳን የሀገር ምሥጢር የሚተነፍስ አይጠብቅም።" ሲቱ ፋሪስ ትንሽ ሆመጠጡ። ከዚያም "ለኔም የቀደመ ትዝታዬን አሳሰብከኝ። ምን መሰለህ? ድሮ የቅኔ ጉባኤ እንደዘረጋሁ አንድ ቀላዋጭ እንግዳ መጣ። ከወዴት እንደመጣ ዛሬ ላይ ይረሳኛል።"

ያ ሁሉ ተማሪ ዐይኑን ተክለባቸው።

"አሞ! ቀላዋጩ እንግዳ ያደረገው ነገር ለኔ እንግዳ ነበር" አሉ ሲቱ፤

"እንዴት?" አለ ገሞራው።

"እንግዳው የተዋነይን ፍልስፍና የሚያጠና መስሎ ሊፈታተነኝ ነበር የመጣው። ይህንን ጉዱን የተረዳሁት ቆይቼ ነው። ሲመጣ በሁለት ጠርሙስ የሚጠጣ ነገር ይዞ መጣ። እንደመጣ ቀጥታ እንግድነቱን ተቀበልሁት። ደርቤን ጠርቼ እግሩን እንዲያጥበው አደረግሁ። እግሩን ታጥቦ እንደጨረሰ ቤት ያፈራውን ቀማመስን። ጥቂት ቆይቶ ከሻንጣው ውስጥ ሁለት ጠርሙሶች አወጣ። ዝም ብዬ አየሁት። የኔታ ድንቡጭ ብርሌ ይኖርዎት ይሆን? ሲል ጠየቀኝ። ፋጋ ሰጠሁት። አንድ ፋጋ ሙሉ ጠጅ አንደቅድቆ ቀድቶ ይችን ይቅመሱ ብሎ ሰጠኝ። አልጠጣም አልሁት። ወደ ራሱ መለሰና ሁለተኛውን ጠርሙስ በፋጋ ቀድቶ ይህን እነሆአለኝ። ይህንንም ቢሆን አልጠጣም አልሁት። ለራሱ ፉት ብሎ ፈገግ ፈገግ ማለት ጀመረ።" አሉ ሲቱ እላቸውም በፈንታቸው ፈገግ እያሉ።

"እሺ?" አለ ገሞራው።

ያ ሁሉ ወፈ ሰማያት ተማሪ ፍጻሜውን ለመስማት ቋመጠ።

PDF Compressor Free Version

ሊቁ ቀጠሉ።

"በሩቅ በሩቅ ስለ ጎንደሮች የሰማሁት ሁሉ እውነታ አለው" ብሎ አንባቢን ነቀነቀ። ምን ሊል ነው ብዬ እንዲቀጥል ገፋፋሁት። ቀሳየዉ የመጣበትን መዘክዘክ ጀመረ። በውጭ የሚሰማው አፈ ታሪክ ቀመስ በጎንደር ሊቃውንት ዘንድ እሙን መሆኑን አረጋገጥሁ። ሐሜቱ ጥሩት ይመስለኝ ነበር። ግን እውነት ነው አለኝ እንዴት እኮ? ብለው ጎንደር ደብረ ጥበብን የቅኔ ውኃ የጠጣ ቀዝቃዛ ውኃም ሆነ ጠጅ አይቀምስም ሲባል ሰምቼ ላረጋግጥ መጣሁ። እውነታውን ከእርስዎ ተረዳሁ ሊል ፈዝዤ ቀረሁ።" ብለው ጭራቸውን ሽው አድርገው ወደ ግራ በኩል ዘመም አሉ።

ያ ሁሉ ተማሪ አንድ ጊዜ ሳቀ። ከፊሉ ጭብጨባ ጨመረበት። ሳቁ ጋብ ሲል ሊቁ ወደቅኔው ጭብጥ ተመለሱና

"ታብር ታብር እያላችሁ ቅኔ አትዝረፉ። መወድሱን አትንገሩ ብዬ ብዙ ቀን ለፍልፌአለሁ። ሕገ ደንብ አውጥቻለሁ። ክልክላ ጥያለሁ። ታብር የሀገር ሀብት እንጂ የጎንደር ደብረ-ጥበብ ቁሶች ብቻ አይደሉትም። ወደፊት አንድ ቀን ይህን ምሥጢር የኢትዮጵያ ሊቃውንት ውሳኔ ይሰጡበት ይሆናል። እስከዚያ ግን ምሥጢር ናት። ደግሞ እስከ ዛሬ ድረስ በመዳፋችን ውስጥ ልትቆዩ የቻለችው አውቀን ደብቀናት ነው። አርቀን ቀብረናት ነው። እንደ ጨረቃ ሰማይ ላይ ሰቅለናት ነው። አማረልን ብለን ለራሳችን ውዳሴ ከንቱ ሽተን በገበያው በደንጊያው ብንለፈልፍ ኑሮ እስካሁን አንዱ ባለጉልበት ይነጥቀን ነበር። ምንም ቀርቶ ሐይቅ እየነጠፈ አንድ ዋሻ ቀርቶ ሕንጻ የሚጠፋበት ዘመን ላይ

መሆናችንን ያወቅህ አልመሰለኝም። በዚያውም ላይ የሀገሬ ሰው 'ታብር ታብር' ሲጮህ ሰምተህ ዐይንህ እስኪበርር በጅንፍ ዱላ ያበርካል። በጣም አለንጋ አፈዳይቶ ነው ወደ ገደል የሚጥልህ። ደሙ ከልብ ሆነህ ትቀራለህ። የጎንጅ ባላገር ከሰማህ አንተን አያርገኝ። አይተጡ ቅጣት ይቀጣኻል። ልትቀስጥ እንጂ ልትማር እንዳልመጣህ አይቶ ምሕረት አልባ ነው። ዋ! ዋ! ተናግሬአለሁ። በዚች ውኃ ምክንያት የብዙ ሰው ሕይወት አልፏል። ውኃዋ መኖሯ ሸጋ ቢሆንም መዘዟ ጎያል ነው። ውኃዋ እንዲህ እንደዋዛ ማንም አልፎ ሄጅ እግረ-ተማሪ በቅኔ ስም የሚቀልድባት ውኃ አይደለችም። ይችን ውኃ ለመቅመስ ጎንጅ ደብረ ጥበብን ያልተሳለመ ሊቅ የለም። ዛሬ በሕይወት የሌሉ በርካታ ሊቃውንት ወደዚህ ጎርፈው ታብርን በማሠሥ ተጠምደው ነበር። ዛሬም ከጎንደር፣ ከሸዋ፣ ከትግራይ፣ ከወሎ፣ እንዲሁም ከዐራቱ ማዕዘን ብዙ ሊቃውንት ብቅ እያሉ አንዳንድ ምሥጢር ይጠይቁኛል። ዓለም ለምኔ ያሉ መነኰሳት ሳይቀር በዚህ ስሜት ተለክፈዋል። ብዙ ጊዜ ወደዚህ እየመጡ ተለማምጠውኛል። ከጳጳሳት በቀር ደጁን ያልረገጠው የመነኩሴ ዘር የለም። በእርግጥ አቡኖችም ቢሆኑ ተራ መነኩሴ መስለው፣ ተራ ቆብ ደፍተው፣ አልባሌ ሰው መስለው፣ መጥተው ለምነውኝ ይሆናል። ነገር ግን የታብር ጥበብ የሚገለጥበት ጊዜው ገና ነው። አሁን ዘመኑ የጠቢባን ሳይሆን የግልቦች ዘመን ነው።" አሉ ሊቁ ገሞራው ቅኔውን መልሶ እንዲያነበው ምልክት እየሰጡ።

ገሞራው "አንከርኩ አንሰ" ብሎ የዘረፈውን ቅኔ በድጋሜ አነበበው።

ሊቁ እንደተለመደው ሌላ "በል" አሉ።

PDF Compressor Free Version

PDF Compressor Free Version

ገሞራው እጅ ነሥቶ ተቀመጠ።

ሊቁ ግን ትንሽ ወግ ተጠሉ።

"ለመጀመሪያ ጊዜ ስትመጣ ስምህ ከብዶኝ ነበር። ከዛሬ ጀምሮ ገሞራው በሚለው ገናና ስም እንድትጠራ ፈቃዴ ነው። ተጠራበት! ጥንቱንም በሆን ስሙ የባለ ቅኔዎች ስም ነው። ሩቅ ሳንሄድ የሞጣው ሊቅ ጌሤ ገሞራውን ማንሣት እንችላለን። ጌቱ ገሞራው የቅርብ ዘመን የቅኔ ሊቃ ናቸው። የቀደመ ስማቸው ጌቱ ብቻ ነበር። ገሞራው ሊቃውንቱ ያወጡላቸው የሙገሳ ስማቸው ነው። ያንን ስም ሸልሚኻለሁ።" አሉ ሊቁ። ገሞራው እጅ ነሥቶ ጉልበት ለመሳም ተንደረደረ። ስሙ በጉባኤ ጸደቀ።

ሊቁ ቀና ብለው የፀሐይን መቆልቆል ከተመለከቱ በኋላ

"በል! በል! አንተን ደግሞ እንስማ?" አሉ ወደ ታሪኩ እየጠቆሙ። ታሪኩ ቅኔውን ሊወቃው ትክሻውን ሰበቀ። ገሞራው ከታሪኩ እንደበት የሚዘንሙ ቅኔዎችን ለመስማት ከትልቁ ከተዋነይ ዋርካ ሥር ተሸራሹ ተቀመጠ። ታሪኩስ ምን ያመጣ ይሆን?

PDF Compressor Free Version

እነሆ በጎንጅ ደብረጥበብ ነጩ ጤፍ በሥርዐት ተሸክፎ ተከምሯል። አረኞች ዋሽንታቸውን እያንቆረቆሩ በየግጦሹ እየዘሩ ላሞችን ግጦሽ ያስግጣሉ። የሊቁ ቅኔ ቤት በመወድስ እየተናጠች ናት። ያ ሁሉ ተማሪ የታጎሣሥን ብርድ እየተቀበለ ከቅኔው ጋር ተፋጧል። ታጎሣሥ ወር በቅኔ ቤት የተለየ ወር ነው። ያም ማለት መስከረም ሲጠባ በቅኔ ቤት ምንዳቤው ይጠናል። መስከረም ውሽንፍርና ምንዳቤ አዝሎ ይመጣል። የቅኔ ተማሪዎች ደመራን ተጠግተው ወደ ባሕርዳር ይሄዳሉ። የመስከረም ምንዳቤ ተግ እስኪልላቸው ባሕር ዳር ውስጥ ይመለጋሉ። ሁለቱን ወራት ከተማው ያፈራውን እየቀማመሱ ይቆያሉ። ሕዳር ሲታጠን ወደ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ተመልሰው ጤፍ አጨዳ ይውላሉ። በቀን ሥራ ይፈጋሉ። ሕዳር ወርና ጤፍ አጨዳው እያከተመ ሲሄድ ወደ ቅኔ ቤታቸው ተመልሰው ይከትማሉ። ልክ ታጎሣሥ አሌፍ ብሎ ሲጀምር ተማሪዎችም እንደ ቀደመው አሌፍ ብለው መወድስ ማንጎድጎድ ይጀምራሉ። ቅኔ ቤቷ በመወድስ ትወረራለች። ተማሪዎች እንደ ጉንዳን ይርመሰመሱባታል። በዚህ ዓመት ግን በቅኔ ቤቱ ውስጥ ሌላም ክስተት ተጀምሯል። የሸረሪት ወረራ ተፈጥሯል። ቅኔ ቤቱ በሸረሪት ተወረረ። የተማሪዎች ጎጆዎች በሸረሪት ድር ተተበተቡ። በጎንጅ ደብረ ጥበብ ሣሮች መክሰም ጀመሩ። ሣሮች ሲከስሙ በሣሮች ፋንታ የሸረሪት ድር እየበዛ ሄደ። ሣር ቅጠሉ የሸረሪት መዋለጃ ሆነ። ጥቂት ቆይቶ መንጋ ሸረሪቶች ገመዳቸውን እየሸረቡ ወደ ታሪኩ ጎጆ መዝመት ጀመሩ። እንደ

PDF Compressor Free Version

ንብ ሰፈፍ እንደ ጠቃጠቆ እንጆራ ተጠጋግተው የተሠሩት የቅኔ ቤት ጎጆዎችን የሸረሪት ሐረግ ተበተበባቸው። የታሪኩ ጎጆም በሸረሪት ድር ተወረረች። ታሪኩ ማለዳ ተነሥቶ ብዙ ሸረሪቶችን ገድሎ ለቅኔ ዘረፋ ይሄዳል። ሲመለስ ሸረሪቶች በድጋሜ ረብተው ይጠብቁታል። ዐመዳም የታሪኩ ጎጆ ከሸረሪት ድር እንጂ ከቃላ ልጥ፣ ከደጋ ፍልጥ የተሠራች አትመስልም። በዐመድ መለቅለቋ ሳያንስ የሸረሪቶች ዝሃ ዐመዳምነቷን አጎላው።

ከታሪኩ ጎጆ ፊት ለፊት ያለው የቅኔ መቀጸያ ጠፍጣፋውና ልሙጡ ድንጋይ በሸረሪት ዝሃ ተወረረ። ይህ ድንጋይ የታሪኩ መቀለጃ ነው። ስምም አውጥቶለታል። አፍጉ ይለዋል። "አፍጉ ሰፍጉ" እያለ በጥፍጥፉ ድንጋይ ይቀልድበታል። ዐመድ ያጠለቀው፣ ጉልቻ የላቀው፣ ድሃ የድሃ ልጅ እንደ ማለት ነው። በቅኔ ቤት ወግ አፍጉ ማለት ድሃ ሰፍጉ ማለት ደሞ የድሃ ልጅ ተብሎ ይተረጎማል። ትርጓሜውን የወሰደው ከዚህ ብሒል ነው። ድንጋዩን በድሀ ልጅ፣ ራሱን በድሀ አባት መስሎ ሲቀልድ ያምርበታል።

ወዲህም ማለዳ ተነሥቶ ፀሐይ የሚሞቅበትን ልመጥ ድንጋይ ጤና ይስጥልኝ አያ አፍጉ? ይለዋል እንደ ጓደኛው። ባለንጀሮቹ ለምን? ሲሉት እናንተ የዚህን ድንጋይ ምሥጢር ምን ታውቃላችሁ?። ተዋነይ በዚህ ድንጋይ ላይ ተቀፍጦ ቅኔ ዘርፎበታል። ከዛሬ ዘመን ጎጠኛ ልሒቅ በሙት በሙቱ ይህ ድንጋይ ይሻላል።" ሲል ከተማሪዎች ጋር ይሟገታል።

PDF Compressor Free Version

ታሪክ መስተፋቅር የተቀቡ የሚመስሉ ጥርሶቹን ፈግግ እያደረገ ሲቃልድ በጣም ያምርበታል። ቀልዱን የሚያነጣጥረው ደግሞ ራሱን ላይ ነው። "እኔ ጅሉ" ሲል ራሱን ጅል አድርጎ ይገልጠዋል። ሕይወቱን ደግሞ ሰፍጉ ይለዋል። ሙልጭ ያልሁ ድሃ ማለቱ ነው። ጣዕመ ተውኔቱ ጥዑም የሆነው ታሪኩ በጨዋታ ጨዋታ በጎጆው ሲቀልድ "አመዳሚ ቤቴ" ሲል ቀልድ ይጀምራል።

የታሪኩ ጎጆ ከሦስት መቶ ሐምሳው የቅኔ ቤት ጎጆ አንዲ ስትሆን ከዚያ ሁሉ ደቃቃ ጎጆ በዳር በኩል ነው የተሠራቸው። ታሪኩ ግስ ሲጽፍ የሚጠቀምባቸው የቀለም ቀንዶች ሳይቀር በሸረሪት ከመወረር አላመለጡም። ድቡልቡሏ የታሪኩ ጎጆ ዘመን ባመጣው ሸረሪት ውስጧም ውጯም ተወሯል። ውበቷ ዐመድ መስሏል። እንደገሞራው ጥርስ አሻቦ የቃመች ትመስላለች።

እንዲያም ሆኖ መዓዛዋ ይማርካል። የዕጣንና የጽጌ ረዳ መዓዛ አድምቋታል። ታቦት አይኑርባት እንጂ ቤተ-መቅደስ ማለት ናት። እንደ ጎንጅ ደብረ ጥበብ የባላገር ቤቶች ድስት የላትም። ሴት አልረገጣትም። ትኩስ እንጀራ አልሸተተባትም። ማሳሻ አልዞረባትም። የጤፍ ጭጋዶ፣ የበቆሎ እሸት፣ የሰመሪታ በሶ ቀምሳ አታውቅም-ምስኪኗ ቤቱ። ጭጋዶዋ የሸረሪት ድር ነው። ኩለንተናዋ የሸረሪት ድርና የሸረሪት አመድ ብቻ ነው።

ለታሪኩ ግን የቤቱ ውበት እንጂ የሸረሪቱ ድር የተከለተለት አይመስልም። በሸረሪት ድር ብትወረር ቅሉ "ኩለንታኪ ሠናይት እንተ ጎቤየ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ" ሲል በሰሎሞን ቅኔ ዐመጿን

PDF Compressor Free Version

የውበት መለኪያ አድርጎ ይገልጻታል። "ቤቱ ሆይ! ሁለመናሽ ውብ ነው፤ ሙሪያ የለብሽ ግሩም ነው።" ታሪኩ ድስት-ና ሚስት በሌሉት ደሳሳ ጎጆ እየኖረ ፍሥሓው ምሉዕ ነው።

ዐርብ ዐርብ መወድስ ሲዘርፍ ይውላል። ሌላ ቀን እንደገሞራው ድርሰት ቢጤ ይሞነጫጭራል። ብዕር ጨብጦ ሲጽፍ አንግዳ ድርሰት ይፈጥራል። ለጥበብ ስስ የሆነ ገላ አለው። ሲቆዝምም ሆነ ሲደሰትም ቅኔ የመፍጠር ክሕሎቱ ኃያል ነው። ከገሞራው ጋር በቅኔና በድርሰት ሲመሳሰሉ በጠባይ ግን ልዩ ልዩ ናቸው። ገሞራው ጠባዩም የገሞራ እሳት ማለት ነው። ቶሎ ቶሎ ይገነፍላል። ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ ይበሳጫል። ሦስት ጊዜ ደግሞ በደስታ ይነከራል። ሰውነቱን በጥበብ መርፌ ሲነቀስ በፍሥሓ ማዕበል ይገፋል። ደግሞ ሌላ ጊዜ ጥበብ ከአእምሮ ስትነጥፍ ሰውነቱ ይበሳጫል። የሠራ አካላቱን የብስጭት መርፌ ይዘረምጠዋል። የብስጭት መድኃኒት በሰውነቱ ተሰራጭቱ ቀቢፀ-ተስፋ ውስጥ ይዶለዋል። ወጪ ወራጅ ጠባዩ ለራሱም ግራ ያጋባዋል። ለመቀነስ ታግሎ አልተሳካለትም። ያልሰከነ ቡን ይመስል ጠባዩ ይስረከረካል። ምን አልባት ያለ እናት ማደጉ ያሳደረበት ተፅዕኖ ሳይሆን አይቀርም። ገሞራው ከታሪኩ በዚህ ይለያል።

እነሆ ዛሬ የቅኔ ቀን ነው።

ታሪኩ ሸረሪቶቹን ሲገድል ቆይቶ ቅኔ ለመዝረፍ ወደ ዋርካው ሲሄድ ሊቁ ፋሬስ በቅኔ ዙፋናቸው ተገስጠው ጠበቁት። እንደ ተለመደው ከሊቁ ፊት ሲደርስ እጅ ነሣ። በሊቁ እንቢለሌ የተጠመጠመው ወፈ-ሰማያት

PDF Compressor Free Version

ተማሪዎቻቸዉ ታሪኩ አፈጠጡ። ቅኔ ለመዝረፍ ጥቂት ሲቀረው እንደ
ልማዱ መላ አካላቱን እያሰሰ በእግሩ መሬቱን መጫር ጀመረ።
ሊቁ ፋሬስ እንደ ተለመደው ጉሮሯቸውን አጽድተው፡-
"ዘል እስቲ አያ?" አሉ በእጃቸው ምልክት እየሰጡ።
ታሪኩ በእግሩ መሬቱን እየጫረ ወደ ቅኔው ተመሰጠ።
ቃል ከማውጣቱ ቀደም ብሎ ከመሬት የወደቀ ሥጋ በጥፍሩ እንደሚልፍ
ቄልፌት ወደ መሬት ዝቅ አለ። ከዚያም አንጥቱን ጠርንቆ ታሕታይ
ከንፈሩን በላዕላይ ከንፈሩ ንክስ አድርጎ እንደ ሰንደቅ መስቀያ ቀጥ ብሎ
ቆመ። ፊቱ ሦስት ጊዜ ተለዋወጠ። ግንባሩ ኩስትር አለ። ተመልሶ
ደግሞ ብሩህ ገጽ አመጣ። ላዕላይ ከንፈሩን ከታሕታይ ከንፈሩ አነሣና
እንዲህ ሲል ቀጠለ፡-

"እመኒ ሐተትኩ ተፈጥሮትየ ምስኪነ
በሞትየ ወበሕይወትየ ከመሣሬት አነ።
ምስሌሃ ለሣሬት እስመ ፩ዱ አቡነ።"

"እንዲያ በልማ!" አሉ ሊቁ ፋሬስ አይተውት እንደማያውቁ በመደመም
እየተመለከቱ ገጻቸው ፈክቶ።
ታሪኩ ቀና ብሎ አያቸው።
ገጻቸው በሐሴት ፈክቷል። ደግሞ ዛሬ በጣም ሕጻን ሁነዋል። በእርግጥ
ፋሬስ አንድ ቀን አረጋዊ፣ ሌላ ጊዜ ጎልማሳ፣ መስለው ይታያሉ። በዚህ
ነገረ ሥራቸው በተማሪዎች ዘንድ በብዙ ነገር ይታማሉ። "አንዳንዱ ወር
በገባ በመጀመሪያው ቀን ዕፀ-ሕይወትን እየታጠኑ እንደ ጌኖክ
ይታደሳሉ። ወጣት ይሆናሉ ሲል ያማቸዋል። ሌላው ደግሞ ከታቦር

PDF Compressor Free Version

እየጠቡ ነው ልጅ የሚሆኑት ሲል ያሚርትባቸዋል። ገሚሉ ተማሪ ደግሞ እንደ ተዋነይ ሞትን የመዝት ሥልጣን አላቸው። ሲሞቱ ሲል ታብርን ይጠጣሉ። መልአከ ሞት በመጣበት እግሩ ተመልሶ ሲሄድ ደስተኛ ይሆናሉ። ያን ጊዜ ልጅነት መጥቶ ያስውባቸዋል።" ሲሉ ይገልጧቸዋል። መገመት የማይቻለው የተዋነይ ጥበብ ከሄት መጣ የሚለውን ነው። ያም ቢሆን ከፈጣሪ የተሰጠ ልዩ ጥበብ ነው ሲባል መልስ አለው። አጨቃጫቂው ተዋነይ ጥበቡን ከወዴት እንደ ሰወረው አለመታወቁ ነበር። ምንም ለጊዜው በገቢር ምሥጢሩን ለማንም ባያሳዩ ለነገው ግን አይመረመሬው ፋሬስ አሉ። ታሪኩ ቅኔውን ሁለት ሦስት ጊዜ እንደ መላለሰው፤

"በል በደንብ ተርጉመው! ፍችውን አሰማን! የሸረሪቷን ጉዳይ እንዴት አድርገህ ቅኔው ውስጥ እንደደነጎርኸው ተናዘዝ። በቀር እመደምደዋለሁ" አሉ ሊቁ ፋሬስ እንደ ተለመደው ከወንበራቸው ተነሥተው እየተንጐራደዱ።

ታሪኩ ሰከን ብሎ ቅኔውን ማብራራት ጀመረ።

"ውስጤን ሳገላብጥ ስመረምር እኔን።

እንዲህ መባሉን፣

ተፈጥሮ ነገረኝ ሸረሪት መሆኔን።

ለምን ቢሉ?

ቀላል ነው ባሉ።

እኔ ብኩኑና ምስኪኗ ሸረሪት፣

PDF Compressor Free Version

አንድ ነን በድካም አንድ ነኝ በሥጋ ወልዶናል አንድ አባት።" አለ
ሃሉን ወደ አማርኛ እየተረጎመ።
ምሥጢሩስ?" አሉ ሊቁ ፋራስ ድንቁ ተደንቀው።
ሥራዋን ስንመረምር ሁላችን አንድ ሀላፊ አለን። ሽረሪት ሳትቀር
በኑር ትሳመደናለች። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን
ፈጠረ። ከዚያ ጨለማንና ብርሃን ጨመረበት። የፈጠረው ሁሉ መልካም
እንደሆነ ተመለከተ። ሰውን ፈጠረ። የሁሉ ጌታ አድርጎ ሾመው።
ከሕተት በኋላ ጥሪህ ግረህ ብላ የሚል መርገም ጨመረለት።
የመጽሐፉ ቃሉ ሽረሪትን አያካትትም ነበር። በኋላ ግን የሰውን ልጅ
ጥረህ ግረህ ብላ ብሎ እንደ ረገመው ሽረሪትንም ጥረሽ ግረሽ ብዪ ብሎ
የረገማት ይመስል ትጥራለች። ትግራለች። ዕረፍት የላትም። ለዚች ሆዳ
የሰውን ልጅ ያክል ትማስናለች። በደንብ ስመለከተው በእኔና በሽረሪቷ
መኸል ያለው የኑሮ ልዩነት ይምታታብኛል። ቢምታታብኝ እኔ ሽረሪት
ነኝ፤ ሽረሪትም የኔ የሕይወት አጋር ትመስለኛለች።" ስል በቅኔዬ
አመጣኋት አለ።

ሊቁ በፍልስፍናው ቢደመሙም ራሱን ከሽረሪት እኩል መቁጠሩ ትንሽ
ቅር አሰኛቸው። ይሁን እንጂ ታሪኩን ያክል ጎበዝ የቅኔ ሊቅ መገሰጽ
አልፈለጉም። በዚያውም ላይ ቅኔውን ከጻድቃን ከሰማዕት ተጋድሉ ጎን
ለጎን ከሰው ነባራዊ የኑሮ ዘይቤ ጋር ማቆራኘቱ የአእምሮውን ልዕልና
ነገራቸው። በውስጣቸው ይበል ነው! ይበል ነው! ካሉ በኋላ ድምፃቸውን
ጮላ አድርገው
"ጥሩ ብለሃል! ነገር ግን በቅኔው ውስጥ

PDF Compressor Free Version

"እስመ ኢይሬስዮ አቡሁ ወኢይትሀሳሰር ምስሌሁ" ያለበት ይመስለኛል። ሰውና ሸረሪት ዝምድናቸው የድካም እንጂ የሥጋ ዝምድና አይደለም። በአባትም ቢሆን አይመሳሰሉም። አንተ ግን "እስመ ፈዳዩ አቡነ" ብለህ በአባት በኩል አንድ ነን እያልህ ነው። በዚህም አምሳለ-ፈጣሪ የሆነውን የሰው ልጅና ሸረሪቷን የአንድ አባት ልጅ ማድረግህ ከሃይማኖት አንጻር ድንቅ አይደለም።" አሉ።

"ለምን?" አለ ታሪኩ።

ሲቁ ቀጠሉ።

"ሰው የተቀረፀው በፈጣሪ አምሳል ነው። ከፍጥረታት ሁሉ ክቡር ሰው እንደሆነ ግልጥ ነው። ክቡርነቱም በእግዚአብሔር አምሳል ስለተቀረፀ ነው። አሁንም ሸረሪትን እጎቴ ስትላት ሸረሪቷ እግዚአብሔር አቡቴ መንግሥተ-ሰማይ ርስቴ ብላ እንዳትመጻደቅ እፈራለሁ። ነገር ግን ቀድሜ የቅኔውን ሙሉ ይዘት ከአንተ አንደበት መስማት እፈልጋለሁ። አበው ያልፈጠሩትን ቅኔ ማራቀቅ ያላሳደጉትን የውሻ ጆሮ እንደ መቁረጥ ነው ይላሉ። ከአንደበትህ ልስማ። "እስመ አሐዱ አቡነ" ያልኸውን በደንብ አብራራልኝ።"

ታሪኩ ጆሮውን አቀርቅሮ ሲሰማ ቆይቶ ቀና አለና፦

"አዎ እኔና ምስኪኗ ሸረሪት በአባትና በእናትም አንድ ነን። በመጽሐፍ ስንመለከተው የሰው አባቱም ሆነ እናቱ አፈር ነው። መሬት ነው። ከመሬት አፈር ተፈጥሯል። 'አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ' በተባለው ቃል መሠረት የሰው ልጅ ካፈር ማጎፀን ይመጣል። ወደ አፈር ይመለሳል። ስለዚህ እኔና ሸረሪት ከአንድ አፈር ተፈጥረናል። በአንድ

PDF Compressor Free Version

አፈር አንናፍስ አባታችን ነው። በግእዝ መሬት ያለው ቃል አፈር አንናፍስ ትክክለኛ ትርጉሙ 'አፈር' ማለት ነው። ስለዚህ "አቡነ ያለሁት አባታችን አፈር ሲሆን አፈር የጋራ አባታችን ነው። ምድርም የጋራ እናታችን ናት። ሰውና ሸረሪት በድካምም ሆነ በተፈጥሮ በአፈር በኩል ተዛምዶ አላቸው።" አለ ታሪኩ።

ሊቁ ፋሬስ በቀላል የቅኔ መንገድ የተፈጥሮን ሕግ በደንብ እንደ መረመረው ተመልክተው

ካሁን በኋላ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ የለም። ቅኔ ክፍልህ ነው። በደንብ ግፋበት። ተራቀቅበት። ውዳሴው ከፊትህ ሲሆን ትዕቢት እንዳይጥልህ እንጂ በቅኔው በኩል ታላቁን ባለ ቅኔ ክፍለ ዮሐንስ ዘንደርን እያክልክ ነው። ያች ታላቂ ጎንደር ጥሩ ባለ ቅኔ እየወለደች ነው። የጥንት የጥዋቷ ጎንደር ዛሬም እንደ ጥንቱ ሲቅ እየወጣላት ነው። ማሕፀኗ አልጠወለገም። የቅኔ ደሟ አልደረቀም። የቀለም አባታችን ታላቁ ባለ ቅኔ ክፍለ ዮሐንስ እንዲህ ከነገረ መለኮት ውጣ ያለ ፍልስፍና ቀመስ ቅኔ ይቀኝ እንደ ነበር ቅኔዎች ይናገራሉ። ቅኔዎች አያሌ ቢሆኑም ባንድ ወቅት የራሱን ሕይወት የገለጠበት ቅኔ ግሩም ፍልፍና አለው።" ብለው

"ቅኔው ምን ነበር አያ?" አሉ የክፍለ ዮሐንስን ቅኔ ከውስጣቸው እየፈለጉ።

"አዎ ክፍለ ዮሐንስ ብዙ ብዙ ብሏል። ውብ አድርጎ ተቀኝቷል። በሊቃውንቱ ዘንድ ግን

"በአስጢፋኖስ አእባን እመ የሐልቱ።

PDF Compressor Free Version

ዘበጠኒ ኢያሱ በወርቱ" ብሎ ለአድያም ሰገድ ኢያሱ ከዘረፈው መወድስ በቀር ሎሌች ቅኔዎች ተረስተዋል። ሲወርዱ ሲወራረዱ ከእኛ በደንብ አልደረሱም።" አለ ታሪኩ።

ሊቁ ምንም መልስ ሳይሰጡ ቆይተው "ይኸውና! ቅኔው መጣ" አሉ።

ክብ ሠርቶ በማዳመጥ ላይ ያለው ያ ሁሉ ተማሪ ለመሰማት ተቅበዘበዘ።

ሊቁ ፋሬስ ግን ወደ ተማሪዎች ዞረው ዐይኖቻቸውን ገርበብ አድርገው የክፍለ ዮሐንስን መወድስ ማንጎድጎድ ቀጠሉ።

"ጥቀ ኄር እግዚአብሔር ለሐዋርያ ግብፅ ዮሴፍ ዘበደዌ ሞቅሕ ሐንካስ።

ወለዘፈተኖ ዳንኤል በጸመ ዕለታት ሠላስ።

በጥቃ መዓቱስ እንዘ ሀሎ።

ማዕረረ ምንዳቤ ምሕረቱ ሐዲስ።

እስመ ያሜክረነ በተጽናስ ወአርዌ ረጎብ ይነቱ ውስተ ጸላዕትየ ከርሥ።

መብልዕየሂ ጼና መብልእ ዘያመጽአ ነፋስ።

ወስቴ አንብዕየ ተረፈ አንብዑ ለኤርምያስ።

ወልብስየኒ ምንንት መንጦላዕተ ርኅቅት ነፍስ።

እስመ አነ ከመ ዶርሆ ላዕለ አብራክየ እሰብስ።" በሚለው መወድስ አስደምሞናል። እግረ መንገዱንም ነገሥታቱን ሸርድዷቸዋል። የጎንደርን ሊቃውንት አስጨብጭቧል። ትልቁ ባለ ቅኔ ክፍለ ዮሐንስ ዘጎንደርና ታናሹ ባለ ቅኔ ታሪኩ ዘጎንደር ድሮ በደም ነበር ዝምድናቸው። ዛሬ ግን በመወድስ ቅኔ ጭምር ሆነ። በእኔ እይታ የመምህሩና የደቀ መዝሙሩ መወድስ የሥነ ፍጥረትን ሕግ በመቃኘት ተመሳሳይ ምሥጢር አለው።

PDF Compressor Free Version

ደራሲ ከመወድሱ እንደሚገልጠው በጎንደር ዘመነ-መንግሥት ጊዜ ባለ ታሪኩ ከፍሉ-ዮሐንስ በደንብ ተገርፈዋል። ሠርክ ጎብስታቸው ነፋስ ከቤተ መንግሥት የሚያመጣው የምግብ መዓዛ እንደነበር አልደበቁም። ስለሙም በቅቡ ምግበ-ሥጋ እንዳልነበራቸው ቁልጭ አድርጎ ያስረዳል። መወድሱ የሚነግረን ይህንን እውነታ ነው። መወድሱ በወቅቱ ሊቁ ጠም ሙሰው ጠም አድረው ሰብዙ ሊቃውንት እውቀት መትረፋቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ተጋድሏቸውን ያብራራል። ልፋታቸውን ይለካል። የእንቱም ቅኔ ሰው እንደሸረሪት ይለፋል፤ እንደሸረሪት ያልፋል የሚል አንደምታ አለው።" አሉ ሊቁ በአጭር ከዘራቸው መሬቱን እየጫሩ።

"አሞ የኔታ ምሥጢሩ እሱ ነው" አለ ታሪኩ።

"ቀዳማዊ ታሪኩ ቢሞት ደኃራዊ ታሪኩ ታሪክ እየሠራ ነው። ወደእኔ ቅኔ ቤት ስትመጣ ስምህ በጣም ደስ ብሎኝ ነበር። ደስታዬ ያለ ምክንያት አልነበረም። በአመክንዮ ነው። በወቅቱ መናገር አልፈለግሁም። መንገርም አልነበረብኝም። ዛሬ ግን ሥራህ ገለጠህ። ታሪኩ ያለውን ስም የወደድሁት ከተሰጥዎህ ጋር መዝኜ ነው። ድሮም ስመ በሊቃውንት መዝገብ ያልተመዘገበ ታሪኩ የሚባል ድንግል ወንጹሕ ባለ ቅኔ የጎንደር ልጅ ነበር። ስመ ግን ከሊቃውንት ውስጥ የተካተተ አይመስለኝም። በትልልቅ ገዳማት ውስጥ ያሉ ረቂቃን መጻሕፍትን የደረሰ እሱ ነው። ግን ስመ ከመጽሐፉ ርእስም ሆነ ከመጨረሻው አልሰፈረም። ባብዛኛው ትልልቅ ድርሰቶች የእጁ ሥራዎች ናቸው። የተጠቀመው ግን የብዕር ስም ነው። በእሱ ብዕር የተጻፉ መጻሕፍት መደምደሚያ መደምደሚያቸው ላይ "እነ ጎጥዕ ጸሐፍኩ ዘንተ" እያለ በምልክት

PDF Compressor Free Version

አስፍሯቸዋል። ጽፎ ሲፈጽም ደግሞ በምዕራፉ በምዕራፉ መጨረሻ "አ
እግዚአ አደጎና ሰነፍሰ ፍቁርየ ክህብ ብሩህ ዘኢትዮጵያ" የሚል ቃለ
ተማኅፅኖ አስፍሮበታል። የአባቱን ነፍስ በገነት አኑርልኝ ማለት ነው።
ክህብ ብሩህ ዘኢትዮጵያ የሚላቸው ንጉሡ ዓለም ሰገድ ፋሲል ናቸው።
"ክህብ ብሩህ ዘኢትዮጵያ" የማኅተማቸው ስም ቄምር ነው። ይህንን
አንተም ታውቃለህ። ይህ ሊቅ በዐጤ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የነበረ
ሊቅ ሲሆን ኂሳ ገዳም ገብቶ በትቶ እንደ ተሰወረ 'ታሪኩ ክህብ ዘምድራ
ጎንደር' ብሎ ራዳኤ የሚባል መጽሐፍ ጽፎታል። መጽሐፉ ጎንጅ ደብረ
ጥበብ ውስጥ ይገኛል። የተያዘው በምሥጢር ስለሆነ አስኩላሬ ድረስ
ወጥቶ ሲነበብ አይችው አላውቅም። ግድ የለም ወደ ፊት ጊዜ ሲኖረን
መጻሕፍትን መፈተሽ እንችላለን። ያን ጊዜ ምሥጢሩ ግልጽ
ይሆንልኻል።" ብለው "በል እንግዲህ ሌላ በል" አሉ።
ከዚያም ሽረሪት እንዳትሸናብህ ተጠንቀቅ። ክፋ አውሬ ናት። ዐይን
ታጠፋለች።"

"አዩ የኔታ ዘንድሮ የመጣብን ነገር ማለቂያ የለውም። ከሸረሪቱ እኩል
ያስመረረችኝ ደግሞ መጅሌዋ ናት። ትኂኑ ሌሊት ቢመጠምጠኝም ቀን
አርፈዋለሁ። ከሰው ፊት እንዳልቆም በእንኩትቴ የሰደደችን ግን
መጅሌዋ ናት።" አለ ሌላኛው ተማሪ ደርቤ በመኻል ገብቶ።
ሊቁ ወደ ደርቤ ዘወር ብለው
"መጅሌማ መቼም ያልለከፈቸው የቆላ ሰው የለም። ሊቅ ሳይቀር
አታከብርም። እኔንም ያለጥፍር ያስቀረችን መጅሌዋ ናት። መጅሌዋ
በኔ እግር ተንሰራፍታ ጎጆ ሠርታ ትኖር ነበር። ፈጣሪ የፈጠራትን ነፍስ

PDF Compressor Free Version

እንዴት አነቅላታለሁ ብዬ ተመከሜያት እኖር ነበር። ኋላ ግን መሬት
የፈራት እንጂ ፈጣሪ የፈጠራት እንዳልሆነች አውቄ መንግዬ ጣልኋት።"
አሉ ሊቁ ፋሬስ።
"ሽሬሪቷን ነው?" አለ ደርቤ።
"ቡጀሌዋን እንጂ" አሉ ሊቁ።
"ቡጀሌ ነው ወይስ መጁሌ ነው ስሟ?" አላቸው።
"እኔ ቡጀሌ እላታለሁ የክርስትና ስሟን ከቁስ አደፍርስ ሂደህ ጠይቅ"
አሉ እየሳቁ።
ቁስ አደፍርስ የድሮ የቅኔቤት ጓዳቸው ነበር። ቡጀሌ ጎጆ ሠርታበት ቆላ
ወርዶ፣ ደጋ ወጥቶ፣ መለመን እንዳይችል አድርጋው በእንኩትት
ሰድዳው ነበር። ቁስ አደፍርስ ዛሬም ድረስ ፋሬስን በቅኔ እኔ አበልጠው
ነበር። እንደ እድል ሆኖ እሱ እንደ ነጭ በራ በሀገሩ ሲጠራ እኔ ትዳር
አንኳሶኝ ቀረ እያለ ሊቁን የሚገዳደር ነውጸኛ ቁስ ነው።
ሊቁ ስለ ቡጀሌዋ ማብራራት ቀጠሉ።
"በመጀመሪያ የጠብ መነሻ የሆነችው ቡጀሌዋ ናት። እንዳንተ ተማሪ
ሳለሁ ስስ ሰውነቴን ቀድዳ ከእግሬ ውስጥ ወልዳ አገኘኋት። መንቅዬ
ጣልኋት። ፈጣሪ ነፍስ በማጥፋት ይፈርድብኛል እንዳልል እሷ
መጣችብኝ እንጂ እኔ አልሄድሁባትም። ስለዚህ መርፌ ቁልፍ ፈለጌ
መንቅዬ ጥያታለሁ።" አሉ ሊቁ።
"ቅኔስ አልዘረፋባትም?" አለ ደርቤ።
"ባላገሩ መወድስ የሚዘርፈው በእሷ ነው። እኔ ግን ንቄ ትቻታለሁ።
መወድሴን በእሷ ማባከን የለብኝም ብዬ አልፈአታለሁ።"

PDF Compressor Free Version

"እስኪ ባላገሩ ስለ ሙያሌ የዘረፈውን መወድስ ይንገሩኝ?" አለ ደርቤ።
"እመይቱ በ-ጀሊት ነፍስሽን አይማረው፣
አማሬ ቁሞ ቀረ መሄድ እያማረው።" ብሎላታል። የባላገር ቅኔ ይበቃታል። ለሷ መርፌ ቁልፍ አንጂ የሲቅ መወድስ አይገባትም።" ሲሉ ደርቤ ትንሽ ፍግግ ብሎ "የታሪኩን ሽረራትስ? እንዴት ይመለከቷታል?" አለ።
"በእርግጥ ሽረራት ግሩም ፍጥረት ናት። የድሮ ሊቃውንትም ሽረራቷን በቅኔ የመነሻ ሐሳብ አድርገው ቅኔ ዘርፈውባታል።" ብለው ትንሽ አሰቡ። ጥቂት ቆይተው አንድ የመወድስ መደምደሚያ ተከሰተላቸው፣
"ይኸውና ቅድም ታሪኩ የሽረራት ድር የሰው ሕይወት የውላ ውረዱ የጉሮ ዘይቤ ተምሳሌት አድርገህ ስታመጣው አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነበር።" አሉ ከደርቤ ወደ ታሪኩ ፊታቸውን መልሰው።
"ይኸውና! የቅኔ አባታችን የምሥጢር አብነታችን ባለ ቅኔው ተዋነይም ዛሬ አንተ ያልከውን ቅኔ በመወድሱ አስፍሮት ነበር።" አሉ።
"ምንድን ነበር እሱ?" አለ ታሪኩ ለመስማት ጓጉቶ።
ሊቁ ጥቂት ተቁነጥንጠው እንደተመለሱ የተዋነይ መወድስ ትዝ አላቸውና ወደ ቅኔው አመሩ። "የቅኔው ጫፍ እንዲህ ነበር።
"ወለአመ ይፈትል ሣሬት እንበለ አልቦቱ አእርፎ።
ለሣሬት ፈትለ አዱ እምነ ዕርቃን ኢያነግፎ።" ብሏታል ተዋነይ።
ትርጉሙም
ሽረራት ቢደክም ቢሸምን በእግሩ።
ምን መጫኛ ቢያክል የሽረራት ክሩ።

PDF Compressor Free Version

ሰርቃን አይጋርድም የሸመነው ድሩ።" ማለት ነው። "በተዋነይ ቅኔ አማለጥ ሸማኔ ጋቢውን ሸረሪት ድሯን ማስነው ይሠራሉ እንጂ ራሳቸው ለብሰው አምሮባቸው አያውቁም የሚል ሰምና ወርቅ አለው። ሸማኔ የለው ጋቢ ሲሠራ እየዋለ የራሱ ጋቢ ኑሮት አያውቅም። ሸረሪትም ድር ስታደራ ትውላለች እንጂ ያደራችው ድር አንድ ቀን ጋቢ ሆኖ ከብርድ ከልሏት አያውቅም።" ብለው

"በል አንተና ባለእንጀራህ ገሞራው ወደ ሬት ትልቅ ሰው ትሆናለችሁ። ትልቅ ራእይ ይኑራችሁ። ተግታችሁ ቀጽሉ። ተግታችሁ ተመራመሩ። ከአንቅልፋችሁ ቀንሳችሁ አንበቡ።" ብለው

"በል ሂድ" አሉ ሲቁ። ታሪኩ እጅ ነሥቶ ተሰናብቶ ሄደ።

PDF Compressor Free Version

# ፵፭

በጎንደሯ የሕይወት ውኃ አንጻር የሚፍሰቀሰቀው ኮከብ በሰማይ ጨረቃን በምድር ውቢቱ ጎንደርን ከድሮው በላይ አድምቋታል። በሲቋ ቅኔ-ቤት ከገሞራው በቀር ሁሉም የሊቁ የቀለም ልጆች በእንቅልፍ ዓለም ሰጥመዋል። ገሞራው እንዳስለመደው ቀን በቃሉ የሸመደደውን ግስ ሲሰልስ ሲመልስ ቆይቶ በቅኔ ቤቱ ዙሪያ የአገር ጎዞ እያደረገ ጥቃትን ኮከቦችን በደፈረሱ ዐይኖቹ እየተመለከተ ይቆዝማል።

"ገሞራው ነህ? እንዴት አመሸህ አካሌ?" አሉ ከኋላው ደርሰው።

"ጤና ይስጥልኝ የኔታ" አለ ገሞራው።

"እንዴት እስካሁን አልተኛህም?" አሉ ሊቁ ፋሬስ የሊሊቱን መገባደድ በአቡሻክር ስፍረ-ሌሊት ለክተውና ሰፍረው ሌሊቱ በጣም እየተገፋ እንደሆነ ተመልክተው።

"ቀን የሸመደድኩትን ግስ ስክልስና ሳለሰልስ ቆይቼ በዚያው እግረ መንገዴን ስለክርታታ ኮከቦች ሳሰላስል የእንቅልፍ ጊዜዬ አለፈ።" አለ ገሞራው።

"ደግ ነው። ጥሩ ጊዜ አገኘሁህ። የተኛህ መስሎኝ ልቀሰቅስህ ነበር።" ብለው "በል -ና- ወዲህ?" አሉ ሊቁ ፋሬስ ወደትልቁ የተዋነይ ዋርካ እያለፉ።

ገሞራው በተመስጦ ከርታታ ኮከቦችን ቀና እያለ እያየ ተከተላቸው። እነሆ በጎጃም ሰማይ ሥር አልፈው አልፈው ብን ብን የሚሉ የጉም ጭራዎች እንደ ፍየል ጅና ውን ውን ይላሉ። አልፎ አልፎ በጥቁር ደመና የተገነጋረገረው ልሙጥ ሰማይ በከፊል የተሟሸ ምጣድ

PDF Compressor Free Version

ይመስላል። ከመኻሉ ላይ የሚታየው የማርያም መቀነት ተጀምሮ የቀረ የጣበብ ትፍትፍ ቀሚስ ይመስላል። በጉሙ የተዋጠችው ለጋ ጨረቃ የአብርሂ ትል ያክል ብርሃን ትረጫለች። የባለ ቅኔው ተዋነይ ትልቅ ዋርካ የጨለማ በርኖሱን ደፍቶ ተገትሯል። በስድስት ማእዘን የተዘረጉ አክናፎቹ እንደ ዘንዶ ተጅመልምለው ተጅመልምለው በስድስቱ ማእዘን አማድም አማድም ተጋድመዋል። ቅጠሎቻቸው ክብ ክብ እየሠሩ በያንዳንዱ ጉማጅ በትዕምርተ መስቀል አምሳል ከወዲያ ወዲህ፣ ከወዲህ ወዲያ ተረጭተዋል። ከስድስቱ የትልቁ ዋርካ አክናፍ ላይ የጨለማ ጥላ ተጨምሮባቸው ራቁቱን የቆመ መልአኩ-ሞት መስለው ይታያሉ። የሰቁ ፋሬስ ጎጆ አዲስ እንግዳ ለመቀበል አፏን እንደ ከፈተች ናት።

ሊቁ ፋሬስ እንደ ድሮው መጽሐፍ ዘርግተው አይመለከቱም። ለወትሮው ከዐይናቸው የማይለየው መጽሐፍ ከወዴት እንደ ወደቀ እግዚአብሔር ይወቀው። ፋሬስ ግን ረስተውታል። ቀና ሲሉ ዐይናቸውን ሰማይ ዳርቻ ላይ ይሰቅላሉ። ሲያቀረቅሩ እንጦርጦስ ድረስ ይመለከታሉ። ግራ መጋባታቸውን የተመለከተው ገሞራው ደጋግሞ ቢያናገዛቸውም ለመናገር ፈቃደኛ አልነበሩም። ከዓመታት በፊት የዘረፏት መወድስ ቅኔ ምን ምሥጢር እንዳላት ለማስረዳት ለማዩን ቀና እያሉ በመመልከት ተጠምደዋል። ቅኔው ሰማይ ላይ የተንሳፈፈ ይመስል የጉሙን ነጠብጣብ ይቆጥራሉ። ገሞራው ውስጣቸው የተረበሸበትን ምሥጢር ለማግኘት ዳክሮ ዳክሮ አልፈለጠው ሲል ተመው። ዐይናቸውን እያፈጠጡ ለማዩን እያዩ ሲቁነጠነጡ ቆይተው፤

PDF Compressor Free Version

"አ! አምላኬ አ! የሠራዊት ጌታ የጠቢቧ የሳባ አምላክ የኢትዮጵያ ፈጣሪ የተዋነይ ጌታ ተመስገን! ተመስገን ተመስገን!። የጥንት የጣኒ የኢትዮጵያ ምሥጢር በእኛ በደካሞች እጅ እንዲኖር ፈቃድህ ስለሆነ እናመሰግንሃለን።" አሉ

"አሜን" አለ ገሞራው ሳያስበው።

"ከተዋነይ ጥበብ ያልነሳኸን ሆይ! ክብርህ በጸባዖት፣ ጥበብህ በኢትዮጵያ ይንገሥ። ከሰሎሞን በላይ ጠቢብ አድርገህ ስለፈጠርከንም ሰጠቢው አምላክ እጅ እንነሣለን።" አሉ እጃቸውን ወደ ሕዋ ዘርግተው እጅ እየነሡ።

"አሜን! አሜን!" አለ ገሞራው እሱም እጅ እንደ መንሣት ብሎ።

ከዚያም

"ልጄ! ከዚኽ ቅጽበት ጀምሮ ማውራት የተከለከለ ነው። ዝም ብለህ ተከተለኝ ብለው።" ብለው ወደ ትልቁ ዋርካ በደንብ ተጠጉ። ገሞራውን ከዋርካው ሥር የወደቀውን መሰላል እንዲያነሣ አዘዙት። በጭንቅ ተውጠርጥሮ መሰላሉን እንዳቆመው ሊቁ እንደ ጦጣ ተንጫዋለው ከትልቁ ዋርካ ቁንጮ ላይ ወጥተው ጉብ ብለው የሚሆነውን ይመለከቱ ጀመር። ገሞራው እንደ ሊቁ እወጣለሁ ሲል ከመሰላሉ አፈትልኮ ከሻፎ ድንጋይ ላይ ተከሰከሰ። መኻል ናላውን ሻፎ ድንጋይ ተረተረው። ከዕቁብ ሳይቆጥረው እንደምንም ተነሥቶ በድጋሚ ከመሰላሉ ጋር ግብግብ ገጠመ። እንደገና ለመውጣት ሞክሮ ነበር። ከትልቁ ዋርካ ጫፍ ሲደርስ ስንዝር ሲቀረው በመሰላሉ ቀዳዳ ሾልኮ ወደገደሉ ገቦው ሲል ሊቁ ከትልቁ ዋርካ ወደ እንጦርጦስ የተወረወርሁ መስሏቸው አብረው

PDF Compressor Free Version

ለመድቀ ተንገዳግደው ቀኝ እግሩ ከሄደም ቀስ ብለው ከትልቁ ዋርካ ወርደው
ምራውን አንሥተው በእጅ ባትሪያቸው ተመለከቱት። አንድ ጥርሱ
ደዱ አፈትልካ ከወጣች በኋላ በቀጭን ሥጋ ተይዛ ትንዘላዘላለች።
ስትወድቅ የተንዘላለዘለችውን የፊት ጥርስ ቀስ አድርገው ወደ ድዱ
ሰኩለት። ተመልሳ እንደ ምትጸድቅ ከተለምዶ ያውቁታል። በናላው
ሚወርደው ደም አፍንጫውን እንዳልተፈጠረ አድርጎታል። አፍንጫው
የተነደለ ጉሽጉሻ መስሎ ደም እየተቀበለ ወደ ውስጥ የሚውጥ
መስላቸው። ሻሻቸውን ከራሳቸው ፈትተው ልምጥ አድርገው ዐሥረው
ጎጀው ውስጥ አስተኝተው ሲመለሱ ፊቱን እያሻሸ ተመልሶ ተከተላቸው።
ጎተመልስህ መጣህ እንዴ?" አሉ በጆሮ ጥላው ሥር የሚንዥቀዥቀውን
ደም እየተመለከቱ።

"ርስዎ ያዩትን ምሥጢር ገሃነም ድረስ ወርጄም ቢሆን የማየት ጉጉት
አለኝ። ገና እንደ ቅዱስ ያሬድ ትል ሰባት ጊዜ ወድቄ ሰባት ጊዜ
እነሣለሁ። በሰባተኛው የማየውን አያለሁ።" አለ ገሞራው ቅዠት
በሚመስል ድምፅ።

ከዚያም ደሙን እያዘራ ሲከተላቸው እንደቀደመው ሊቁ በመስላሉ ላይ
ተንጨዋለው ወደ ትልቁ ዋርካ ወጡ። እሱም በደም የታጠበ ገጹን
በዋርካው ቅጠል እያበሰ ወጥቶ ከአንደኛው የትልቅ ዋርካ ክንፍ ላይ ጉብ
አለ።

"ተመልከት!" አሉ ሊቁ ፋሬስ በጎንደር ሰማይ ሥር ቀጭን ክር መስላ
ወደ ጎጃም አፍዛዣ ሰማዩን እንደ ጀልባ በግንባሯ እየሰነጠቀች ወደ ጎንጅ

PDF Compressor Free Version

ያን ጊዜ ያልተናገርኩት አብዛኛው ተማሪ ወጣኒ ስለነበረ አታምኑኝም
ብዙ ነው።" አሉ ሊቁ።
እንዴት?" አለ ገሞራው።
ሰውዬው ውስጥ "ደመና በቅሎ ተብሎ ተገልጧል። ጢስ ደግሞ ሮቢላ?
በዚያ ላይ አባቶቻችን ይጋልቡታል የሚል እንደነበር ትዝ ይለኛል።"
አሉ ሊቁ ፋሬስ ከዓመታት በፊት የዘረፉትን ቅኔ አስታውሰው።
ትክክል እሱ ነበር። ነገር ግን ያን ጊዜ ሰሙና ወርቁን ነግረው
ምሥጢሩን ነፈጉን።" አለ ገሞራ።
ትክክል ነው ሰውሬአችኋለሁ። ጊዜ ይግለጠው ብዬ እንደሰወርኋችሁ
አውቃለሁ።"
"ታዲያ ዛሬስ?"
"እንደምታውቀው ደመና በነፋስ እየተጅመለመለ ወደ ላይ ይወጣል።
ዝናምም ይሸከማል። ከሰው ዘር ከኤልያስ በቀር በደመና ወደሰማይ
የወጣ የለም። ኤልያስም ቢሆን ደመናን የጋለበው በእምነቱ እንጂ
በጥበቡ አይደለም። የሀገራችን ጠቢባን ግን በጢስ ተሣፍረው በደመና
ጋልበው ወደፈለጉት ይነጉዱ ነበር። ነገር ግን ምሥጢሩንና ጥበቡን
ከባዕዳን ለመሰወር ሲሉ ከዚህ ትውልድ ደብቀውታል። ይህንን የተደበቀ
ነገር የሚያውቁ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ከጥንቶች ስንጀምር ሊቁ ኖላዊ
አንዱ ነበሩ። ጀርመን ሀገር ሂደው ግእዝ አስተምረው የዚህን ምሥጢር
ሲጠየቁ ደበቁ። በዚህ ምክንያት ጀርመን አርዳ በላቻቸው። ከእሳቸው
ቀጥሎ የዚህ ብርቅ ምሥጢርና ጥበብ ዐቃቤ መልአክ በጎንደር የሚኖሩ
ሊቅ ዐፅቁ ናቸው። ዛሬ ደግሞ የቀለም ጓዴ የዚህ ምሥጢር ባለቤት

PDF Compressor Free Version

ጽላሉ የምትበረዋን ቀጭን የጢስ ጭራ የጢስ ገመድ በጣታቸው እየጠቀሙ።

"ምንድን ነው አሉ?" አለ ገሞራው።

"በደንብ ተመልከት። እንደ ተለመደው አስማት ነው። ምትሐት ነው። ጋኔን ነው ከማለት የአበውን ጥበብ ልብ ብለህ ተመልከት።" አሉ።

ገሞራው በደም የታጠበ ዐይኑን በቅጠል እያበሰ ያሮልቅ ጀመር። ሊቁ ቀጠሉ።

"ከዓመታት በፊት ቅኔ ማስተማር ስጀምር
ጠቢባን አበው ዘጥበቦሙ ሐዲስ፤
ፈረሰሙ ኮነ ደመና ወመንኰራኩሮሙ ጢስ።"
የቀደሙ አባቶች ጥበባቸው ሐዲስ፤
በቅሎቸው ደመና ሩቢላቸው ጢስ፤
አዳሜ ይሮጣል ከጥላቸው ላይደርስ።" ስል ቅኔ ዘርፌ እንደነበር ታስታውሳለህ?" አሉ።

"በደንብ እንጂ" አለ ገሞራው ደሙን በቅጠል እየጠረገ።

"በደንብ እንጂ ከዘመናት በፊት ቅኔ ማስተማር ሲጀምሩ እንደዘረፉት ቅኔውም ታሪኩም ደርሶኛል። በእርግጥ በወቅቱ እኔ ወደዚህ ቅኔ ቤት ልማር አልመጣሁም ነበር። ዲማ ጊዮርጊስ መጽሐፍ በመማር ላይ ነበርሁ። ነገር ግን በወቅቱ የቅኔውን ምሥጢር ምን እንደሆነ ለመረዳት መጥቼ ስንብቻለሁ። ምሥጢሩን ግን አልተናገሩም ነበር።" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

ሆኑ። በል እኔን ለተመልከት። የወደፊቱ ታሪክ ተናጋሪ አንተ ነህ። እኔ ወደ አባቶቼ እመለሳለሁ። ነገ ታሪክ የምትነግር ለሀገር ባለ አደራ አንተ ነህ! በደንብ ተመልከት።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"በዐራቱ ማዕዘን ተመለከትኩ። ዐራቱን ማዕዘን መረመርሁ። ከጢስ በቀር ያየሁት ነገር የለም።" አለ ገሞራው ግራ ገብቶት።

ሊቁ እንደ ብረት በጠነከረ ክንዳቸው አንገቱን ቆልምመው ወደ ጉነደር አዞሩት።

"ዘዚህ በኩል ነው እንዴ?" አለ ገሞራው ጢስ የምትመስል ቀጭን ደመና በዳበሳው እየፈለገ።

"በንርኅራኄ ሰማይ ሥር ከጣና ሐይቅ አንጻር!" አሉ ሊቁ አንገቱን ወደ ጣና ሐይቅ አንጻር ቆልምመው እያዞሩ።

"በደቅ-ደሴት በኩል?" አለ።

"አዎ!" አሉ

ገሞራው በደም የተሠረቡ ዐይኖቹን ወደጣና ሰማይ ወረወራቸው። ፊት ለፊቱ በጢስ አምሳል የሚወረወር የሰው ምስል ሲመለከት ዐይኑን ማመን አቃተው። ከትልቁ ዋርካለምለም ቅጠል በጥሶ በደም የተትረከረከ አፍንጫውን እያበሰ ዐይኖቹን በልግዶ በደንብ ተመለከተ። ደመናው ከቀጭን ጢስ ወደሰው እየተቀየረ ሲመጣ ምትሐት መሰለው። ጢሱ በደንብ እየቀረበ እየቀረበ ሲመጣ የቀይ ዳማ ሰውዬ በደመናው ውስጥ ጉብ ያሉ መሰለውና ዐይኑን ማመን አቅቶት ተርበተበተ። ፈጣን አንደበቱ ተከላተፈበት።

ሊቁ ማብራራት ቀጠሉ።

PDF Compressor Free Version
ፈረሰሙ ኮነ ደመና ወመንኰራኵሮሙ ጢስ" በሚለው ቅኔ ውስጥ ከንመታት በፊት ያሰፈርሁት ምሥጢርና ጥበብ ይህ ነበር። በመወድሴ የዘራሁት ምሥጢር አሁን በደሞሽ ዐይንህ የምታየውን ረቂቅ ጥበብ ነው። ይህንን ነቅዐ-ጥበብ ከጥቂት መፍቀርያነ-ሀገር ሊቃውንት በቀር ማንም አውታታ አያውቀውም። ለተካኑትና ለተቀቡት ብቻ የተሰጠ በረከት ነው።

ባለ ቅኔው ተዋነይ፤

ተዋነይ በጣና።

"ይመስላል ደመና።" ተብሎ የተዘፈነለት አሁን ዐይንህ በሚያየው ጥበብ ደመናውን ሲጋልብ በመታየቱ ነው።

"ከዚህ ነቅዐ-ጥበብ በከፊል ከጻድቁ ካሌብ ጀምሮ የሀገራችን ነገሥታት ከቅበዐ መንግሥቱ ኃን ለኃን ይቀቡት ነበር ይባላል። በግብጻዊ አቡን ቡራኬ ቅብዐ-መንግሥት ተቀብተው በቂስ ዐጤው ደግሞ ግሩም የሆነውን የሀገራችንን የጥበብ ቅብዐት ይቀቡ እንደ ነበር አንዳንድ ድርሳናት ያወሳሉ። በጋሻና በጦር ብቻ ሱዳንን አልፈው ሕንድ ዉቅያኖስ ድረስ የገዙበት ሥርወ-ምሥጢር ይህ የአባቶቻችን ጥበብ ነበር።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ለመሆኑ ማን ነበር የሚቀባቸው?" አለ ገሞራው።

"ቅብዐ-ክህነቱንና ቅብዐ መንግሥቱን ግብጻዊ አቡን ይቀባቸዋል።

PDF Compressor Free Version

ከዚህ ቅብዕ በክፉል የሚቀባቸው ቂስ አጼው ነው። አየህ ልጄ አባቶቻችን በጣም ምሥጢር ጠባቂዎች ነበሩ...።" ካሉ በኋላ ፋታ ወስደው ቀጠሉ።

"በወቅቱ ነገሥታትን የሚቀቡ ጳጳሳቱ ግብጻውያን ስለነበሩ ቅብዐ-ክህነቱንና ቅብዐ-መንግሥቱን እንጂ ቅብዐ-ጥበቡን እንዲቀቡ ሰግብጽ ምሥጢር አይነገራቸውም ነበር። ሲጀመር ከግብዕ የሚመጡ አቡኖች በቋንቋ ዲዳ፣ ሰሰዉ ባዳ፣ ስለነበሩ የሀገራችን ሰዎች እምነት አይጥሉባቸውም። አቡኖች ምሥጢሩን ሳያውቁ ቂስ አጼው በምሥጢር ይቀባቸዋል። ቂስ አፄው ኢትዮጵያዊ ስለሆነ የቅብዐ-ጥበቡ ማሠር የነበረው በእሱ እጅ ብቻ ነበር። ወዲህም ያ ጊዜ አባቶቻችን ጥበባቸውን ለጎረቤት አሳልፈው የሚሰጡ የዋዛ ሰዎች አልነበሩም። ስለዚህ ግብጻውያንን በዝሆን ጥርስ ገጸ በረከት እያባበሉ አቡን ያስመጣሉ እንጂ ጥበባቸውን አላቀመሷቸውም ነበር። አየህ! ልጄ! ሰነፍን ሰው በወርቅና በብር በአልማዝና በስበሩ ድንጋዮች ገጸ-በረከት ማታለል ይቻላል። የጥበብ ፍቅር ያለበትን ሰው ግን እነዚህ ሁሉ ሊማኙት አይችሉም። እንዲያውም ወደ ጎንደር ሄደህ ታሪክ ብታጠና የዐጤ ፋሲልን ቤተ መንግሥት የከበቡት እጨጌዎች ብቻ ነበሩ። ዛሬ ድረስ በአባ-ጃሌ ተክለ ሃይማኖት በኩል እጨጌ ቤቱ አለ። ድሮ የጥበቡን ምሥጢር እጅ አድርገው የሀገራችንን ነገሥታት በንግሥና ስም የጥበቡን ቅብዐት ይቀቡ የነበሩ እጨጌዎች ብቻ የሚኖሩበት ምሥጢራዊ ቤት ነው። የግብፅን አቡኖች አይጨምርም። ዛሬ ድረስ ከዐጤ ፋሲል ቤተ-መንግሥት ወረድ ብለህ አባ ጃሌው አካባቢ ብትጠይቅ አብዛኛው መንደር እጨጌ ቤት

PDF Compressor Free Version

ሥሙ ይጠራል። ነገሥታቱ ጠቢባኑን አንድ ላይ አስቀምጠው በጥበብ እንዲፈላሰፉ ያደረገበት መነኑ-ጠቢባን ነው። ነገሥታቱ በሀገራቸው የበዛ ነግሠው ይባጁና ነሐሴ ጾም ሲመጣ ወደ ገዳም ይሄዳሉ።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ለምን?" አለ ገሞራው።

"ለሱባኤ ነዋ። ይህንን ጥበብ የሰጣቸውን አምላክ በጽሞና ሆነው ለማመስገን ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም እየወረዱ ባመት ባመት ሱባኤ ይገቡ ነበር። ሱባኤውን እንደ ጨረሱ ድጋሜ በቂስ ዐጠው ተቀብተው ወደ ዙፋናቸው ብቅ ይላሉ። ጠላት ሲነሣባቸው ከመስክረም እስከ-ሦስት ክተት ሠራዊት ያውጃሉ። በየክተት ወርደው ይገዮማሉ። ድል አድርገው ይመለሳሉ። ኃላም ሲያርፉ አጽማቸው በጀልባ እየተጫነ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የተቀመጠበት ምሥጢር ይህንን ይመስላል። ገዳመ-ም ለሁለት ነገር ይፈለግ ነበር። በነፍሳቸው ለጸድቁበት፣ በሕይወት ሳሉ ደግሞ አምላክን ሊያመሰግኑበት። ዛሬ ግን ሀገራችን ከጥበብ ምድረ-በዳ የሆነች ትመስላለች። ይህንን ድንቅ ጥበብ ሊያወርሱን የሚችሉ ሊቃውንት እኩይ ስም ተሰጥቷቸው ከአብዛኛው ሰው ተገልለው እንደ ሌሊት ወፍ ብቸኞች ሆነዋል። ትልቅ ጥበብ አዘለው ትንሽ ዋሻ ውስጥ ይኖራሉ። እንደ ፍልፈል ከመሬት ውስጥ ሆነው ዐፈር ይገፋሉ። በእልፍ ከሚቆጠሩ ሊቃውንት የዚህ ጥበብ ተካፋይ የነበረ ባለ-ቅኔ ተዋነይ ነበር። ተዋነይ በጥበቡ ተራቅቆበታል። ሞትን ለሳት ዓመት ድረስ ገትሮታል። ሞትን የገዘተ ሊቅ እየተባለ በታሪክ የሚነገርለት ተዋነይ ከጠቢባን አንዱ ነበር።" ሊቁ ፋሬስ ስለተዋነይ ካልተረኩ ቀኑ አይመሽላቸውም።

PDF Compressor Free Version

ከዚያም "ጠቢብ ለመሆን ከፈለግህ ወደኋላ ተመለስ። ዛሬ ባለው ትውልድ አእምሮ አታስብ። አሁን በምድር ላይ ያለው ትውልድ ከፊሉ የወንድማማቾች ኢትዮ-ኤርትራ ግጭትና የአድዋ የጀግኖች ታሪክ የተምታታበት ነዘሕላል ቢጤ ትውልድ እየመጣ ነው። ለጥቂት ዓመታት በተበከለ ትምህርት ተመርዞ በከፊልም ቢሆን የእሱ የሆነዉን ለባዕድ እየሰጠ ያለ ትውልድ ነው። እናም አላቶታችን ጥንት ወዳደረጉት ታሪክ እናምራ።

"ምን መሰለህ? ይህ ጥበብ ከስመ-ሰይጣንም ሆነ ከድግምት ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው። ለቀደምት አበው የተገለጠ ጥበብ ነው። እንዲያውም አንዳንዶች ተዋነይ ከፈጣሪው ያገኘው ጥበብ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ ነው ይላሉ።" ብለው ቀጠሉ።

"ሌላው ዓለም ቢፈልገው ያላገኘው በኢትዮጵያም ገና ግልጥ ሆኖ መነገር ያልጀመረ ለጥቂት ሰዎች ብቻ የተሰጠ ጸጋ ነው። እነሱም ዋሻ ገብተው የጥበብ መንደር መንድረው ይኖራሉ።"

"እኔ አላምንም?"

"ይገባኛል" አሉ ሊቁ በሽሙጥ ድምፅ።

"ይገባኛል የዚህ የልብልቡ ትውልድ አካል ስለሆንህ በግልቡ ሥልጣኔ እንጂ በጥንቱ የኢትዮጵያ ጥበብ አታምንም። እኔ ግን አሁንም በድጋሚ እነግርኻለሁ። ጥበብና ሥልጣኔ ይለያያሉ። የሠለጠነ ሕዝብ ሁሉ ጥበብ የለውም። ሥልጣኔ ዘመኑን መምሰል ነው። ጥበብ ግን ዘመኑን መቅደምና መብለጥ ነው። ወደ ፊት ድድብናህን እንደ ለምድ አውልቀህ

PDF Compressor Free Version

ሃለሠ ከመሪመርከው ለዕንግም ምሥጢራን አካፍልኻለሁ።" ብለው
ሥልጣን ዋርካ ግንድ ተደግፈው ቀጠሉ።
ነበ ቅኔው ተዋነይ ከቅኔው ባሻገር የጎበዛት ባለቤት ነበር። ደቀ
መዛሙሮቹም እንደ መምህራቸው ጥበብ ተገልጦላቸው ነበር።
ያልተጻፉና በጥናት ያልተረጋገጡ ወደ ፊት ግን ሊረጋገጡ የሚገባቸው
አፈ ታሪኮች እንደሚነግሩን ተዋነይ በደመና እየጋለበ በደመና መጋረጃ
ታጋርዶ ከጎጃመ አበያ በረሃ ተነሥቶ በልያ ቤተ-ንጉሥ ዳሞት አልፎ
ደመና እየጋለበ ደቅ አስጢፋኖስ ገዳም እንደገባ ይተረካል። ምንም
ሳይኾው በደመና እየተንሸራሸረ ሂዶ ከሸናሻ አልፎ ከአገው ምድር ዝቅ
ብሎ የዳንጉርን አየር እየማገ የበልያን አርዘ ሊባኖሶች መጠለያው
አደረገ። እየቆየ ነገዶቹን መሳብ ጀመረ። እኛ ግን ይህን ሁሉ ዕውብ
ድንቅ ጥበብ በአስማት የሠራው መስሎን እንጃላለን። ለበቡ ሲፈላሰፍ
ለነሱ ጠልፎ ይጥለዋል። በዚህ ክፋታችን ሀገራችን በድኅነት መዘገብ
ኮላተች። ቁንጫ መፈንጫ አድርጎን ቀረ።" ብለው ሳይጨርሱ ከአፈ-
ታሪኩ ተፈትልከው ወጡ።
ለጥቀውም "ታሪኩ ምን ያረጋል ልጄ?" ቀናው ጥበቡ ነው።
"እዩህ ልጄ! ፈጣሪ በቃሉ "ለታብቁል ምድር" ብሎ ሲናገር ጉልቁ
መሳፍርት የሌላቸው ዕፀዋት ተፈጥረዋል። በዚህ ዓለም የተፈጠሩ አሉ።
በኀትም የበቀሉ አሉ። ከተቀምጥህበት ዋርካ ጀምሮ የተፈጠሩ ዕፀዋት
በሙሉ የጥበብ ምንጮች ናቸው። ሌላው ዓለም አጥብቆ
እየተፈላሰፈባቸው ይገኛል። በኢትዮጵያ ግን ለዳቦ መጋገሪያና ለግብጦ
መንከሪያ የተፈጠሩ ይመስል የብቅል መርገጫ ሆነው ቀርተዋል። ሌቶች

PDF Compressor Free Version

የዋርካ ቅጠል የሚፈልጉ የምሽምሽ ዳቦ መጥበሻ ብቻ ነው። ወይም የገና ብቅል በቀርሜት ሲረግፉ ከላይ ለማልበሻ የዋርካ ቅጠል ይፈልጋሉ። እናንተ የቅኔ ተማሪዎችም የዚህ ምድር ታላቅ ዕፅ የሚመስላችሁ አእምሮ አስቶ የሚያንቀዠቅዠው ዕፀ-ፋርስ ወይም የቆላ አብሽ ብቻ ነው። ሌሎች የጥበባት እንጨቶች ተሰውረውባችኋል። ዝዚም ከድቷችኋል። ልብ በል። እንደ ሀገሬ ሚርተኞች ሥር ማስ ቅጠል በጥሰ እያልክ አይደለም። እበው አብነት ነሥተህ ወደጥልቁ የአበው ጥበባ መድረስ ትችላለህ። ዘወትር ከሌላ ሀገር የተቀመመ መድኃኒት እያነሡ መዋጥ አግባብ አይደለም። በዘሽታ ላይ በሽታ መደመር ነው። የሀገራችንን ዕፀዋትም ወደ ክኒን መለወጥ ትችላለህ። ጠልቀህ ተመራመር እያልክ ነው።" ብለው አሁንም ጪሷን ወደ ዐየቡት ተመለሱ።

ቀጭኗ ደመና በባህር ላይ እንደ ወደቀ ኩበት በሰፈው ሰማይ ትንሣፈፋለች።

ሲቋ ፋሬስ ግን ቀጠሉ።

"በእጅህ ከጨበጥከው ዋርካ ብንነሣ የዋርካው ደም የሸረሪት መድኃኒት ሆኖ ተፈጥሯል። ሸረሪት ሲሸናብህ ደሙን አፍሰህ የቆሰለውን ክፍል ብትቀባው ወደ ሌላኛው አካል አይራመድም። ቁስሉ ከሰውነት ይርቃል። ወደሌላው አካል አይሸጋገርም። አይረማመድም። እንደ በጋ ሰርዶ ባለበት ክሽም ይላል። ነገር ግን ዕፀዋት ያለ አግባብ ለመድኃኒትነት ሲውሉ አእምሮ ይቀንሳሉ። ወይም ያሳብዳሉ። ጨርቅ አስጥለው ይሰዳሉ...ክፍ ሲል ይገላሉ። በአንጻሩ ቅኔ የሚያዘርፉም እንደ ነበሩ ይነገራል። ነገር

PDF Compressor Free Version

ግን ቃለ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ መሆን አለበት። ቅኔ ያዘርፉሉ ስለተባሉ ብቻ ዕፅ መጋት አግባብ አይደለም። ይህ ቁጥሩ ከጥበብ ነክ ቢሆንም ቅሉ ደቀ መዝሙር መድከም መምህሩ ተግቶ ማስተማር አለበት። ምሥጢር መግለጥ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ዘአንበሩ አበው ይህ ነው። መምህር ለተማሪው ቀለም ይነግረዋል። ዕፅ እንዲግተው ግን አይገደደም። ዘንበሩ አበው ይህ ነው። ይህን እመን።" አሉ ሊቁ ፋሬስ ጸጉሩን እያሻሹ።

ጣና ሐይቅን አቋርጠው ወደ ጎንጅ ሰማይ ሲጠጉ "በል አስወርደኝ ልቀበላችው። መስተንግዶው የእኔ ነው። እንደ ተዋነይ በደመና እየጋለቡ እየመጡ ነው። አዬ ልጅ ጦቢያ የምትባል ሀገር ከጥንት ጀምራ ምሥጢር ናት ያልኩህ ወድጄ አይደለም። በጢስ እስተማምለጥ የሚያደርስ ጥበብ ሥጋዊ ወጥበብ መንፈሳዊ ስላለን ነው። ጢስ እንደ መንኮራኩር ሆኖ ያገለግለን ዘንድ በጥበብ ይገደዳል። ነገር ግን ጢስ ለብቻው ዐይን ያጠፋል። በነዳጅ ነው የሚነደው።" ብለው ሊቁ ፋሬስ ሻሻቸውን ከራሳቸው ፈትተው ገሞራውን ከዋርካው ግንድ ጋር ለምጠው አሥረው ቸ·ተው ወረዱ።

ከጎንደር አቅጣጫ የተወነጨፈው ደመና ከጸባያት እንደ ወረደ መልአክ እየተጥበረበረ ወርዶ ሊቁ ፋሬስን ጨመጨማቸው። የደስ ደስ ያላቸው ሽበታም አረጋዊ ሽማግሌ ናቸው። ከዚያም በወገባቸው ሻጥ ካደረጓቸው መጻሕፍት መኻል የውኃ ኮዳ ቢጤ መዘልጠው ወደ ፋሬስ ሊዘረጉ ሊቁ ፋሬስ የተቋጠረ ገጻቸው በደስታ ፈካ።

PDF Compressor Free Version



ስንብት

ጠቢቡ ሐረ ከደመና እንደ ወረዱ ሁሉንም ገልጠው አወሯቸው። ጎንደር ሲደርሱ ሊት ዐፅቁ ተቀብለው ሐሸማል በሚባለው መጽሐፍ እየተመሩ የሕይወት ውኃን መፈለግ እንደጀመሩ አወጓቸው። ቀሃ ወንዝ ላይ ምንም ፍንጭ እንዳላገኙ ደገሟቸው። አንገረብ ላይ ውኃው ቡግ ብሎ ነድዶ ምልክት ካዩ በኋላ ድርግም ማለቱን ሠለፏቸው። ከዚያም ሌሊት ሲሊት በመጽሐፉ ተይ ብርሃን እየተመሩ መላ ጎንደርን ካሠሡ በኋላ ከልደታ ውኃ ላይ ምሥጢሩ እንደ ተገለጠ ከዚያም መልሶ እንደ ተሰወረ ካብራሩላቸው በኋላ፤

"ሐሩ ውተደመር ቤተ አቡከ" አሉ ሊቁ ፋሬስ። ወደ አባትህ ቤት ሄደህ ኑር ማለት ነበር።

"መሄድማ እሄዳለሁ። ነገር ግን አንተን ትቼ አልሄድም።" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"እኔ እንኳን ባልሄድ ይሻላል?" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ምን ነካህ? በሕይወት መኖር እየቻልን? እንዴት መቃብር እንወርዳለን? መቃብሩን የኋላ ኋላ መቼ እናጠዋለን? ተዋነይስ ቢሆን መቃብሩን መቼ አጣውና? ኑሮ ኑሮ በሕይወት መኖር ሲለለቸው ሞቶ አይደል? መቃብርማ ለአፍስ ቢሆን መቼ ይቀርልናል? አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ተብለን አንድ ጊዜ ተረግመን አይደል እንዴ? እንደርስበታል።" አሉ ጠቢቡ ሐረ

PDF Compressor Free Version

ኃጢአት ነው። ነገር ግን እኔ ጉባኤ ፈትቼ ይህንን ሁላ ወፈ
ለማየት ተማሪ ሜዳ ላይ ብቻዬን ከገመሬድ ከዚሁ ሞቱ ይሻለኛል ብዬ
ነው።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።
ሃሰም! የለም! መቼም አብረን እንሄዳለን ብዬ ከሕይወት ውኃ ለአንድ
ለው ብቻ የምትሆን ይገዜ መጥቻለሁ። እንካ። ይቺን ጠጣና ወደ
አባቶቻችን የጥበብ ዓለም ጐራ እንበል። ከጠቢባኑ ጋር በሕይወት
እንኑር። ይህንን እድል ማሳለፍ የለብንም። እድሉን መጠቀም አለብን።
ሞት ሳይቀድመን መቅደም አለብን። የዐባይን ሽለቆ ጨምሮ ገዳም
ለገዳም ተንከራትቼ ውኃዋን አምጥቻለሁ።" አሉ ጠቢቡ ሐረ ከጎንደር
የሕይወት ውኃ በኮዳ ቀድተው ለፋሬስ እየሰጡ።
"እረ ለመሆኑ ዐባይ ሽለቆ ምን ወሰደህ። ለአንድ ሳምንት የቅኔ
ዘራፊዎች ዐባይ ውስጥ እንዳለህ እያነሡ ቅኔ ሲዘርፉ ሰነበቱ።" አሉ
ፋሬስ።
"ያችንን የሕይወት ፍሬ ፍለጋ ነበር። ወታደሮች በቁጥጥር ሥር
አዋሉኝ። እንዲፈቱኝ ነገርኳቸው። እንደገና ሥራዐት አጸኑብኝ።
ሊገድሉኝም ቃጣቸው። በመጨረሻ በተዋነይ ጥበብ ተሰወርኳቸው።"
ብለው በአጭሩ ነገሯቸው።
ከዚያም ሊቁ ፋሬስ ቀጠሉ።
"ውኃዋን ማምጣትህ ሽጋ ነው። በደመና ስትመጣ ሳይህ ውኃውን ይዘህ
እንደመጣህ ገምቼ ነበር። ለኢትዮጵያ ብለህ የከፈልከውን መሥዋዕትነት
አረሳውም። እኔ ግን ወደ ጠቢባኑ ሰፈር መሄዱን አላሰብኩበትም።

PDF Compressor Free Version

ፈጣሪዬ ሀሳቧን እይሚ ሰላጆቹ ቀለም አውርሻቸው -ና- ስባል ብሄድ ይሻለኛል።" አሉ ሲቱ ፋሬስ።

"አያ! ፋሬስ! ጥንቱንም አንተ ወላዋይ ነህ!። ውሳኔ ላይ ዳተኛ ነህ። ጥንት ገና ቅኔቤትሳለን ጀምሮ ቁርጥ ያለ ሐሳብ አልነበረህም። ኃያላን ሀገራት ጨረቃን ገዝተው በላይኛው ሰማይ ሀገር ገንብተው ሲያበቁ የሞት መድኃኒት ለማግኘት ሀገራችንን መበርቀስ እንደ ጀመሩ ለአንተ መንገር ለቀላሪ ማርዳት ነው። ከጠቢቡ ሰሎሞን ጀምሮ የሀገራችንን የክርሠ ምድር አልማዞች አግዘው ጨርሰው ዛሬ ደግሞ ይችንን የሕይወት ውኃ ለማግኘት ድኃሜ ኢትዮጵያን እየበረበሩ ናቸው። ያንን አንድ ቀን ካገኙ መጀመሪያ የሚጨርሱት የሀገሬው ሰው ነው። ይህ ትውልድ ደግሞ ይህን ከማመን በኋላ ነው። ተረት ተረት ብሎ አልፎታል። መመርመር ሲችል መመርመር ተስኖታል። በቅርቡ ደግሞ ሳይንሳዊ ጥበብ አድርጎ ለዓለም ማቅረብ ሲችል ለሳይንስ አልታደለም። ከሳይንሱ ቀድሞ ቦለቲካው የገባው ስለመሰለው ከማይወጣው እንጦርጦስ ውስጥ ተቀብሯል። ነገ ከነገ ወዲያ የዚች ፍልቅልቅ ሀገር ባለውለታ እኔና አንተ በጥበብ የወለድናቸው ጥቂት ልጆች ብቻ ናቸው። እነሱን ፈጣሪ እስኪሰጠን ግን መሞት የለብንም። መኖር አለብን። ደግሞ አንተና እኔ እንደ አድል ሆኖ ይህንን ምሥጢር ከቀደሙ አባቶቻችን ወረስን። የወረስነውኮ ለጊዜውም ቢሆን ከሞት ልንደበቅበት ነው። ኋላም ሀገራዊ ሀብት ስለሆነ ለትውልድ ልናደርሰው ነው። እንዴት ይህን የመሰለ እድል ይሰፈኝ ትላለህ? ነገ አንተ ከሞትክ ለዚህ በኩና ትውልድ ማን ይህንን ምሥጢር ያስተምራል።" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

PDF Compressor Free Version

ይገባኛል! ይገባኛል። ነገር ግን ይቺንን የኔዋን ታቦርን ለማን አደራ አለሁ? እድሜ ዘመኔን ስጠብቃት ኑሬ ዛሬ መክስተ-ጥበቡን ለማንም አውታታ ሰጥቼ ብዬድ ነገ ይህ ትውልድ ምሥጢሩን ለባዕድ አሳልፎ ይሰጥብኛል። ወይም እንደ አረቂ በፍንጃል ይክፈላታል። ስለዚህ ይቺንን ምሥጢራዊት ውኃ አደራ የምሰጠው ሁነኛ ሰው ሳልፈጥር ከዚች ነቅነቅ አልልም። በዚያ ላይ ይህንን ምሥጢር የሚጠብቅ ጥብቅ ሰው እስካገኝ ድረስ ለማንም ላልናገር አባ ዮና ገዝተውኛል።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

ጠቢቡ ሐረ ተስፋ ሲቆርጡ "በል እንካ ኮዳዋን ተቀበለኝ። ምን አልባት ነገሰንገ ወዲያ ሐሳብን ቀይረህ ወደ-አባቶች መንደር ለመምጣት ዘፈልግህ ውኃዋን ጠጥተህ በደመና ተጭነህ መምጣት ትችላለህ።" ብለው በውስጣቸው የያዙትን ቋጠሮ ለፋሬስ ሰጥተው ወደ ትልቁ ወደ ተዋነይ ዋርካ ሲወጡ ቀጭን ደመና መጥታ ሸፈነቻቸው። ደመናው ተመልሶ ወደ ሰማይ መጠቅለል ሲጀምር ጠቢቡ ሐረ እጃቸውን በመስቀል አምላል ሠርተው ጸሎት ጀመሩ። ከዚያም ወደ ሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል ፊታቸውን ሲያዞሩ ከመስዕ በኩል ዐውሎ ነፋስ ደመናውን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ መታው። ጠቢቡ ሐረ ለመጨረሻ ጊዜ ሊቁ ፋሬስን በእንባ ተሰናበታቸው።

ከዚያም "ካሁን በኋላ እኔና ሊቁ ሊቅ ዐፅቁ ሐሽማሎች ነን። ሐሽማል ማለት የመላእክት ጉባኤ ማለት ሲሆን እንደ መላእክት ሕያዋን ሆነን እስከ ፈለግነው ዘመን በሕይወት እንኖራለን። በዚህ ዓለም ደግሞ እንደ ተዋነይ መልአክ ሞትን ገዝተን ለኢትዮጵያ እንሠራለን። ሐሽማል

PDF Compressor Free Version

መላእክት ቋንቋ ጉባኤ ማለት እንደሆነ በአብራይስጥ ደግሞ የጠቢባን ማኅበር ማለት ነው። ወደፊት ይህ ትውልድ ወደ ልቡ ሲመለስ ሐሽማሎች ለኢትዮጵያ ተግተው ይሠራሉ። የሕይወትም ውኃ በኢትዮጵያ ትገለጣለች። ያን ጊዜ ኃላ ቀሯ ሀገራችን ዓለምን በጥበብ ትቀድማታለች። ጥበብና ሥልጣኔም ይለያያሉ። የሠለጠነ ሕዝብ ሁሉ ጥበብ የለውም። ሥልጣኔ ዘመኑን መምሰል ነው። ጥበብ ግን ዘመኑን መቅደምና መብለጥ ነው። የቀደመ አባቶቻችን ክዛሬው ትውልድ በጥበብ ይበልጡ ነበር። "በል ቸር ዋል!"። ድምፃቸው እየራቀ ሄደ።

PDF Compressor Free Version

# ሻፎ

ሰጋዋ ጨረቃ ጠቢቡ ሖረን ሸኝታ ወደ መስኮቷ ተሸኝታለች። በጽልማሞት የተዋጠው ሌሊት መገላደድ ጀምሯል። ገሞራው የዋርካውን ቅጠሎች ጉዝጉዞ ለሽ ብሏል። ሊቁ ፋሬስ ገሞራውን ዐሥረው ከዋርካ ወርደው ጠቢቡ ሖረን በናፍቆት እንባ ተቀበሏቸው። ጥቂት ተጨዋውተው አሰናበቷቸው። ገሞራው ይፈቱኛል ብሎ ሲጠብቅ እግራመንገዳቸውን ጸሎት ቤታቸውን ከፍተው ገቡ። እንደማይፈቱት ተሰፋ ቆርጦ በቅጠሎች ተጠቅልሎ ተኛ። ጠቢቡ እንደ ተዋነይ በደመና መንኮራኩር ተጭነው ከነጓዱ በኋላ ሊቁ ፋሬስ ትንሽ ትንፋሽ ወስደው ኩራዛቸውን አያይዘው "በስመ አብ" ብለው የዕለቱን ጸሎት ይሰልቱት ጀመር። ገሞራውን እንዳሰሩት ትዝ ያላቸው ጸሎታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ነበር። ዳዊታቸውን በማእዝ፣ ሙሉ የዮሐንስን ራእይ በዕብራይስጥ ቋንቋ ጸልየው አስኪጨርሱ ገሞራውም እንቅልፉን ጨረሰ። ብቻ ያየውን ምሥጢር በማመንና ባለማመን እንደሰጠመ እንቅልፍ ስለወሰደው እንቅልፉ ቅዠት የተመላበት ነበር።

ሊቁ እንደ ተለመደው ጸሎታቸውን በአቡነ ዘበሰማያት ዐሥረው በመስቀላቸው ዐራቱን ማዕዘን ባርከው "ታዎርያን" ይዘው ወደ ቅኔ ቤት ሂደው ታሪኩን ተጣሩ። ታሪኩ ከእንቅልፉ ባኖ እየተጭፈነፈነ ተከተላቸው። ክትልቁ የተዋነይ ዋርካ ሲደርሱ ሌሊቱ ሊነጋ የአኽያ ሆድ መስሎ ነበር። መለሳሉ ላይ ሲወጡ ገሞራው ባንኖ ተነሣ። "ይቅርታ ልጄ!" የታሰረበት ሻሻቸውን እየፈቱ ሥርየት አልባ የመለሳቸውን ንሥሓቸውን መናዘዝ ጀመሩ።

PDF Compressor Free Version

"ለምን እንዳሰርኩህ ሰፊ ጊዜ ወስጄ አጫውትኻለሁ። አሁን በደሊን ይቅር በለኝ።" አሉ ፋሬስ ከትልቁ ዋርካ ግንድ ላይ በግንባራቸው ተደፍተው።

ገሞራው ወደ ዋርካው ሲወጣ በደረሰበት የመውደቅ አደጋ ገጹ በደም ተጨማልቆ ደሙ ከፊቱ ላይ ገማሮ ይታያል። መውደቁ ሳያንሰው ባላወቀው አበሳ መታሰሩ ቢያበሳጨውም በሁለቱ ጠቢባን መካከል ያየው ድንቅ ምሥጢር አእምሮውን ዐሥሮ ይዞታል። ሕሊናው ሰባቱ ሰማያት ድረስ ተሰቅሏል።

"የታሰርክበትን ምክንያት ሳልረዳ ዓመት ተዘቅዝቀው ቢለምኑኝ እንኳ ይቅርታ አላደርግም።"

"ስለ ተዋነይ ብለህ ይቅር በለኝ።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ራሱ ተዋነይ ቢማልደኝ አልማለድም። ለምን እንዳሠሩኝ ይንገሩኝ።"

"ሖረ ይባላሉ። የቀለምም የምሥጢርም ጓዴ ናቸው። አንተም በአንድ ዘመን አጥብቀህ ትፈልጋቸው እንደ ነበር አውቃለሁ። ባለንጀራህ ታሪኩም እንዲሁ። መዋቲው ሊቅ ነበልባል ግን ዐባይ ሸለቆ ወርዶ በዐይኑ አይታቸው ተመልሷል። ከጥበባቸው ግን አልተቋደሰም።" አሉ ሊቁ ወደ ታሪኩ ዙረው።

"አዎ። ሰምቻለሁ።" አለ ታሪኩ።

"አንተ ደክመህ ደክመህ ለዐይነ-ሥጋ እንዳልበቃህ ነግረኸኛል። ይኸውና ዛሬ አያኻቸው። የሐሸማሎች ዘር ናቸው። ከተዋነይ የጥበብ ድግስ አብረን ተቃምሰዋል። ከቅበዐ ጥበቡ የተቀቡት ከእኔ ቀደም ብለው ነው..." ካሉ በኋላ ወደ ፊት ለመቀጠል አልፈለጉም።

PDF Compressor Free Version

ምዕራፍ ማስተማር ስጀምር

ገጠሪያን አበው ዘጥበቦሙ ሐዲስ፤

ፈረሰሙ ኮነ ደመና ወመንኮራኩሮሙ ጢስ።

የቀደሙ አባቶች ጥበባቸው ሐዲስ፣

በቅሷቸው ደመና ሩብላቸው ጢስ፤

አዳሜ ይሮጣል ከጥላቸው ላይደርስ።" ብዬ የዘረፍኩት ቅኔ ዛሬ ገቢራዊ ሆነ። ያን ጊዜ ጠቢባን በደመና ይሄዳሉ። በሕይወት ይኖራሉ" የሚል ቅኔ ዘርፌ ሳስተምር በቅኔ ቤቱ ያሉ መኖ ያኽል ቅኔ ዘራፊዎች ቅኔዬን ንቀውት ነበር። በተለይ ያ ትንኩሽቱ ነበልባል "ቅኔክ የውሻ ቡችላ አከሰተ ዐይና" ብሎ ቅኔዬን አቃልሎት ነበር። በመደፋፈሩ ቆሎ ተቀሰፈ። አንተ ግን ይኸውና ለማየት በቃህ! ጠቢባን ደመናውን እንደ በቅሎ ሲያስግሩት ተመለከትህ። ቅኔውም ተፈታ።" ብለው ቀስ ብለው ከትልቁ ዋርካ ሲወርዱ፤

"በደንብ ዐየኻቸው አይደል?" አሉ ታሪኩን አቋርጠው።

"ፈረንጅ መሰሉኝ በቅጠሉ ተከልዬ እያየኋቸው ነበር።" አለ ገሞራው።

"ፈረንጅ በብረት እንጂ በደመና መሄድ መቼ ይችልና? የዓለም ጠቡበት! ከበሮ የሚመቱት ራሳቸው በደመና ሂደው አይደለም። ሮቢላ ነድተው ነው። ዐየህ ግዙፍ ብረት ከማብረር ራስ መብረር ይበልጣል። ነጮች ብረት ቀጥቅጠው ያበራሉ። አባቶቻችን ደግሞ ራሳቸው ይበራሉ። ነጮች በብረት ሲበሩ ካደናቀፋቸው ዕመቀ እመቃት ይወርዳሉ። አንዲት ዐጥንት እንኳን ማግኘት አይቻልም። አባቶቻችን ግን የደመና ፈረስ ነበራቸው። ነገር ግን የድሮ ጠቢባን በደመና መጫን ሲጀምሩ ጠንቋይ

PDF Compressor Free Version

ተባሉ። ተናደው ጥበቡን ሰወሩት። ቢሆንም "በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል" ነውና ብሒሉ በመጽሐፍ ጽፈው ማንደር አበጅተው አሰፉ። በአጭ ጊዜ እኒህን መጻሕፍት ንያላን ሀገራት በየጊዜው ወደ ሀገራቸው ጫኗቸው። በሀገራችን የቀረው አንዱ መጽሐፍ ብቻ ነው። ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከፊሉን እኔና ወንድሜ ሐረ ወርሰን ተጠበብንበት። ተፈላሰፍንበት። ሌላኛው መጽሐፍ በማንደር ከአንድ ሊቅ እጅ ይገኛል። ብዙ ወጥተን ወርደን ከማንደር ውስጥ አንድ ጠቢብ ምሥጢር አዋቂ አገኘን።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ምን ነበር እሱ?" አለ ገሞራው።

ሊቁ ያልሰሙ መስለው ትርክታቸውን ቀጠሉ።

"እስክ ዛሬ ድረስ ይህ ጥበብ ያለው በኢትዮጵያ ጠቢባን እጅ ብቻ ነው። ፈረንጆች ጠቢባን ሲባሉ የቻሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ሰርቀው በወሰዷቸው መጻሕፍት እየተመራመሩ ነው።

"ቀለማቸውን በደንብ ተመለከትኸ አይደል?" አሉ በድጋሚ።

"በቅጠሉ ቀዳዳ እያየኋቸው ነበር። በደንብ ባይሆንም በከፊል።" አለ ገሞራው።

"መዚዳቸው ነው።

"ወዴት?" አለ ገሞራው።

"ወደ ሐሽማሎች። ወደ ጠቢባኑ መንደር። ሞት በጥበብ ወደሚገዘትበት ሰፈር...።"

"ሐሽማሎች እነማን ናቸው? ሰዎች ናቸው?" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

"አዎ! እንደኛ ለታሪክ ይቆርባቸዋል። ይጠማቸዋል። ይወልዳሉ። ፍቅር ያውቃሉ። ከዚህ ዓለም ሰዎች ልዩ የሚያደርጋቸው እስከ ፊለንት ዘመናት ድረስ በሕይወት መኖራቸው ብቻ ነው። መልአከ-ሞትን በጥበብ መዘነታቸው። ወዲህም ሕላዌአቸው በስዋሬ መሆኑ ነው። ለዚህ ደግሞ ያቺ የሕይወት ውኃ አለችልን። ለቅኔና ለጠቢብነት ታብር ታበራልናለች። ሞትን አሸንፈን በሕይወት እንኖራለን። በዚህ በክሡቱ ዓለም መኖር ይቀራል። ወደ ስዋሬ እንመለጣለን። ሐሸማል ከሚባል ጉባኤ ጠቢባን ጋር እናራለን። ሐሸማል ማለት "ጉባኤ መላእክት" ማለት እንደሆነ እኛም ሐሸማል ሆነን ጉባኤ ጠቢባን መሥረትን እናራለን..."

"በል ይቅር በለኝ? ይቅር በለኝ?" አሉ የታሰሩ እግሮቹን ፈትተው እየጨረሱ።

"ይቅር ብያለሁ።" አለ ገሞራው።

"በደንብ ይቅር ካልኸኝ ለአንተና ለታሪኩ ታብር ትገባችኋለች።" ብለው ቁልቁል ወደ መስዕ በኩል ወደታብር ወረዱ። ተዋነይ ከለወራት ደሴት ሊደርሱ "ታሪያ" የሚባለውን የተዋነይ መጽሐፍ አወጡ። መጽሐፉን በዋሻው አንጻር ሲገልጡት ስውሩ ዋሻ በብርሃን ተጥለቀለቀ። ጥቂት ቆይታ ተዋነይ የለወራት ደሴት ስትከሠት ታብር ተፍለቀለቀች። ገሞራውና ታሪኩ ዘለው ተቀላቀሉ። ሊቁም ተከተሉ። የጥበብ ሴሊት ሲነጋ ጎሕ እየቀደደ ነበር።

ተፈጸመ

# እንኳን ደና መጡ

PDF Compressor Free Version

## ማንበብ ለህይወት @worldbook0

pdf መፅሐፍትን በቀላሉ የሚያገኙበት የቴሌግራም ቻናል

እንዲሁም ምርጥ ምርጥ ትረካዎችን ያገኛሉ

ይቀላቀሉን ቤተሰብ እንሁን የሚፈልጉትን መፅሐፍ በቀላሉ ያግኙ

